መንደርደሪያ

ታህሳስ/1999 ዓ.ም.
አዳማ (ናዝሬት)

በገልማ አባጉዳ አዳራሽ ከሚገኙት አንዱ የምግብ ክፍል ውስጥ ራት እየበላን እናወጋለን። የአሁኑ "ጠቅላይ ሚኒስትር" ሐይለማሪያም፣ "ሚኒስትር" ሬድዋን ሁሴን፣ የኢቲቪ ምክትል ስራ አስኪያጅ ሰለሞን ተስፋዬ እና የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ከንፍ አባላት የሆነው ካሚል አህመድ፣ ፀጋዬ ሐምማሪያም እና እኔ ነበርን። በገልማ አባጉዳ አዳራሽ የተገኘነው ለወራት በአቶ መለስ በሚሰጠው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ኢንዶክትሪኔሽን ስልጠና ላይ ለመሳተፍ ነው። የዛሬው ኢንዶክትሪኔሽን ስልጠና ያጠነጠነው በፓርቲው "የኢኮኖሚ አውታሮች" ላይ በመሆኑ እያነሳን የምንጥልው ወግ በዚሁ ነጥብ ላይ ሆኗል። የህወሓት ኩባንያ የሆነው ኤፈርት የውይይታችን ማዕከል ሆኗል።

1

ጨዋታና ከርከሩ እየደራ ሲሄድ ታጋይ ካሚል አህመድ ሁላችንንም ተራ በተራ እየተመለከተን "በዚህ ጉዳይ ላይ ፍርሃትና ሲጋት አለኝ። በየቡድኑ ካድሬው ለጠየቀው ጥያቄ በቂ ምላሽ የተሰጠው አይመስለኝም" በማለት ተናገረ። "እንዴት?" የሚል ጥያቄ ከሁላችንም ተከታትሎ ቀረበለት። ካሚል ለማሰቢያ ጊዜ ሳያጠፋና ምንም ሳያመነታ "በሰነዱ ላይ የሰፈረው ትክክል ነው ብላችሁ ታምናላችሁ?...አስቲ ሐይለማሪያም! ልጠይቅህ የኢህአዴግ ኩባንያዎች በግልፅነት መርህ የሚመሩ ናቸው? እውነት ከመንግስት ያገኙት ወይም የወሰዱት ቅንጣት ሳንቲም የለም? ኩባንያዎቹ የተቋቋሙበት ተልዕኮ በመንግስትም ሆነ በባለሀብቶች ሊሸፈን የማይችል ቀዳዳ ለመድፈን ነው? እውነቱን ለምን አትናገርም?" በማለት ጠየቀ።

በድጋሚ ምላሽ ሳይጠብቅ "አስቲ ሬድዋን ልጠይቅህና መልስልኝ። እውነት የኢህአዴግ ኩባንያዎች በከልሎች መካከል የተመጣጠነ እድገት መኖር አለበት የተባለውን መርህ አይፃረሩም? በመርካቶና ሌሎች ቦታዎች ያሉ ነጋዴ ዘመዶችህ ዘወትር ስለ ኩባንያዎቹ ምንድነው የሚሉህ? ንግዱንና ኢኮኖሚውን ተቆጣጠሩት፣ መፈናፈኛ አሳጡን፣ የቻይና ጫማና ማጭድ ሳይቀር ተቆጣጥረውታል አላሉህም?...ታዲያ ይሄን ለምን አትናገርም? እውነቱን አያወቅን ዝም ማለት ለማንም አይበጅም! ድርጅቱንም ይዞት ይጠፋል እንጂ አይጠቅመውም" በማለት ጠየቀ።

አሁንም ካሚል አህመድ ማቆም አልፈለገም። ወደ ሀገሩ ልጅ ሰለሞን ተሰፋዬ ዞሮ "ጓድ ሌቲቪ! የኢህአዴግ አህት ድርጅቶች ኩባንያ የሚባለውን ታምንበታለህ? እስቲ የአህያዉ ዲንሾ፣ የአንና የአንተ ወንዶ የሰሩት አንዲት ፋብሪካ ካለ በኢቲቪ አሳየን!...ዲንሾና ወንዶ ለህዝቡ የሰሩት አንዲት ጥርጊያ መንገድ ወይም ወፍጮ ቤት ካለ ንገረን!...ተናገር እንጂ "በኤፈርት፣ በጥረት፣ በዲንሾና ወንዶ መካከል ያለው ልዩነት ነባራዊ እንጂ በአድልዎ የተፈጠረ አይደለም አያለ ጓድ! መለስ ሲናገር አልዘገነንህም?... ኧረ ለመሆኑ ዲንሾና ወንዶ በህይወት አሉ?" በማለት ጠየቁ። በመፅዱ ላይ የተሰበሰብነው ካድሬዎች በሙሉ ስቃኝ ከአኔ በስተቀር ደኢህዴንች ናቸው። ሁሉም የካሚል ግርፎች ናቸው። በደጉ ዘመን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሰነዶች ኢንዶክትሬት አድርጎ ወደ ፓርቲው የመለመላቸው እሱ ነው። ዛሬም በትላንት አይኑ ስለሚመለከታቸው በእነሱ ላይ ያሳደረው ንቀት ከፍተኛ ነው። እነሱም ቢሆን በጣም ይፈሩታል። በተለይ ሐይለማሪያምና ሬድዋን ፍራቻቸው ከሩቅ ይታያል። እሱም ቢሆን ሥሥ ብልታቸውን ስለሚያውቅ በፍራቻ ላይ ፍራቻ ይጨምርባቸዋል።

2

ካሚል ወደ ፀጋዬ ሐይለማሪያም ሴባ ጣቱን እየጠቆመ "ጓድ ፀጋዬ! ለስሙ ህግ ተምሬያለሁ ብለህ በሚረባው በማይረባው እንቀጽ እየጠቀስክ ቀኑን ሙሉ ታደነቁረናለህ። ዛሬ ምነው አንደበትህ ተዘጋ?... በየቡድኑ ያሉ ካድሬዎች "በፍትሃብሔር ህጉ መሰረት ግብረ-ሰናይ ድርጅት ማለት ምን ማለት ነው? የኢህአዴግ ኩባንያዎች በጎ አድራጎት (ኢንዶውመንት) የሚባለውን መስፈርት ያሟላሉ ወይ" ብለው ሲጠይቁ ምነው እፍህ በሙጫ ተጣበቀ?_ግብረ-ሰናይ ድርጅት በንግድና ሌሎች ለትርፍ የተዘጋጁ ኢንቨስትመንቶች ላይ መሳተፍ ይችላሉ ወይ ተብሎ ሲጠየቅ ጅሮህን የዝሆን አደረከው?" በማለት አፈጠጠበት።

ለካሚል የቀረሁት እኔ ነበርኩ። አልቀረልኝም። በቦንብ ፍንጣሪ የተሰነቀ የፊቱን ጠባሳ እየነካካ "አንተስ ብትሆን ወትሮ ቆፍረህ የምታመጣው መረጃ ኤፈርት ጋር ሲደርስ ምነው ተደፈነ? ጓድ መለስ! "እነዚህ ኩባንያዎች እንደማንኛውም ባለሀብት በህግ ተመዝግበው በህግ የሚሰሩ ናቸው" ብሎ ሲናገር አፍህ ተዘጋ?... ኩባንያዎቹ ከማንም በላይ ህግና መመሪያ አክብረው የሚንቀሳቀሱ ናቸው በማለት በድፍረት ሲናገር ከማንም ቀድማ የምትቀሰረው ጣትህ ዛሬ የት ገባች?...አካውንቲንግ ተምሬያለሁ ስትል አልነበር! ለመሆኑ ኩባንያዎቹ አዲት ይደረጋሉ? የአዲት ውጤቱ ለፍትህ ሚኒስቴርና ለድርጅቶቹ አባላት ይፋ ሲሆን ተመልክትሃል?" በማለት በቡድን ውይይት ወቅት ካድሬዎች ያነሱትን ጥያቄ የራሱ አስመስሎ ጠየቀኝ። ጥያቄው ከየትም ይምጣ ትክክለኛ ስለሆነ በውስጤ "ሂሴን" ዋጥኩ።

ለደቂቃዎች ዝምታ ሰፈነ።
ሁሉም እቀርቅሮ መብላት ጀመረ።

በዝምታው መሀል ካሚልን ለጨንቀሬ ተመለከትኩት። ሰለእሱም ማሰብ ጀመርኩ። ለእገላሲጤ ይቅርታ ይደረግልኝና ካሚል ፍልጥ መሀይም ነው። "ጨዋነቱ" የፈጠረበትን የበታችነት ስሜት ለመደበቅ የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። ሰእንድ በኩል የተማሩ ግን ደግሞ የድል አጥቢያ ባለስልጣናትን ሲያገኝ የሰርአቱ ባለቤት መሆኑን ማሳየት አንዱ አላማው ነው። የማይተካና እጅግ የሚፈለግ ሰው መሆኑ ያመላክታል። ባገኘው አጋጣሚ ወይ ድርጅቱን በሰላ ሁኔታ ይተቻል። አሊያም በተበራራ ሁኔታ የለብዮታዊ ዴሞክራሲ መርሆዎች በመስበክ የሕሊና እርካታ ያገኛል። በሌላ በኩል በመካከለኛ ደረጃ (ዞንና ወረዳ) የተመደቡ ካድሬዎችን ሲሰበስብ ደግሞ ጠረጴዛ መደብደብና እንደ አውራ ዶሮ መንጎማለል ልዩ ባህሪው ይሆናል።

3

ከካሚል ልባዊ ንግግርና አርምሞ በኋላ በግራ ጎኔ የተቀመጠውን ሐይለማሪያም ተመለከትኩት። እየበላ ጫን ጫን ይተነፍሳል። ከሳንባው የሚወጣው አየር የተኛ ፀጉር ያስነሳል። በእንዳች ምትሃታዊ ኃይል ከአጠገባችን በሮ የሸማኔ ጉድጓድ ውስጥ ቢደበቅ የመረጠ ይመስላል። ሐይለማሪያምን ጠጋ ብዬ እንዳየሁት ከሆነ እንደዚህ ያለ መረር ያለና ህሊናን የሚፈትን ጥያቄ ሲቀርብለት በሚያስታውቅ ሁኔታ ያምቧትራል። ለምላሹ ማጠፊያ ሲያጥረው ያፋ ማሰሪያ ተፈቶ እንደተዘቀዘቀ ቀልቀሎ ይዘረገፋል። በፖለቲካው ዘርፍ ሳይሞቅ ይፈላል።

ታዲያ የሐይለማሪያምን እንደዚህ መሆን ሳስብ በሊደርሽፕ ትምህርት ላይ "አምባገነን መሪዎች ምን አይነት ተከታዮችን ማፍራትና ወደ አመራርነት ማምጣት ይፈልጋሉ?" ለሚለው ጥያቄ የተከራከርነው እና የሰራነው ወረቀት (Term paper) ትዝ ይለኛል። ለምን እንደሆነ በማውቀው ምክንያት አቶ መለስ እና ሐይለማሪያም ፊቴ ድቅን ይላሉ። ሳኪን አድጋር የሚባል የሊደርሺፕ ፀሀፊ "አምባገነን መሪዎች ለሃላፊነት የሚመርጡት ተከታይ የአለት ጥቅማቸውንና ፍላጎታቸውን ካገኙ የህዙብ ችግር የማይገባቸው፤ የአምባገነን መሪውን ትእዛዝ ያለማቅማማት የሚቀበሉና እንደወረደ የሚያስተጋቡ፤ በህዝቡ ዘንድ የተናቁና ጅላጅል ቢጤዎች ናቸው" በማለት ይገልጣል።

(የአቶ መለስ ግብአተ መሬት የተፈፀመ ሰሞን አንዳርጋቸው ጽጌ ከኢሳት ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና ጋር ቆይታ አድርጎ ነበር። ጋዜጠኛ ሲሳይ አንዳርጋቸውን "በአቶ መለስ ምትክ ጠቅላይ

ሚኒስትር የተደረጉትን አቶ ሐይለማሪያም ደሳለኝ ያውቋቸዋል ወይ?" በማለት ጠይቆ ነበር። ለንባርጋቸው ምላሽ ሲሰጥ በአርግጠኝነት ውስጥ ሆኖ "ሐይለማሪያምን አላውቀውም። ነገር ግን መለስ ለጠነቡ ሊያስጠጋቸው የሚችለው ማንን ነው ብዬ ሳስብ እጅግ በጣም ደካሞችን መሆኑን አውቃለሁ" በማለት ምላሽ ሠጥቷል።)

ያም ሆነ ይህ ታጋይ ካሚል አህመድ በኢህአዴግ የኢኮኖሚ ድርጅቶች ("ኢንዶውመንት") ላይ ግዙፍ ጥያቄዎችን አንስቷል። ነባራዊው እውነት አግጦ እየወጣ ስለሆነ መወሻሸቱ ይቅር እያለን ነው። በተለይ የህወሓት ንብረት የሆነው ኤፈርት ጉዳይ በአጭር ጊዜ እልባት ካላገኘ በየቀኑ እየተወሳሰበ ምንአልባትም በትግራይና በሌሎች ወጣቶች መካከል የተቀባረ ፈንጂ እየሆነ እንደሚሄድ መገመት አያስቸግርም። አቶ መለስም ሆነ ህወሓት ለትግራይ ወጣቶች እንደ ገፀ-በረከት ይዘውላቸው የመጡት "ኤፈርት፣ ትልማና ረሰት" የሚባሉ ኩባንያዎችና ማህበራት ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ጋር በአዲስ ግምብ አጥር እየለዩአቸው ሔደዋል።

4

ተወደደም ተጠላም ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው ትልቁ ጥያቄ ብሔራዊ አኩልነት እና የጋራ ተጠቃሚነት ሆኗል። ይህንን ጠንቅቆ አለማወቅ ተጨባጩንና ትከከለኛውን ሁኔታ አለመረዳት ያስከትላል። ያየነው እና እያየነው ያለነው ነባራዊ ሐቅ ፀረ- አኩልነት እና አትብታቸው ከተቀበረበት ከልል ውጭ እርቀው ማየት የተሳናቸው ወጣቶች እየተበራከቱ መሔድ ነው። በዚህ መልኩ ከቀጠለ ነገ የሚፈጠረው ነገር የህሊና ፀፀት መፍጠሩ የማይቀር ይሆናል። አንደ ሀገር መቀጠል የማያስችልበት ሁኔታ ይፈጠራል። በአንድ በኩል ከአፍትሐዊ እንቅስቃሴው ተጠቃሚ የሆኑ ልምቡጦች እየተፈጠሩ ነው። እያገኙት ያለው ጥቅም ልበ-ድፍን አድርጎአቸዋል። በሌላ በኩል ከበደሉ ብዛት አንጀቱ የነፈረና ሌሎች አማራጮች የሚያማትር እየተፈጠረ ነው።

ከምንግዜውም በላይ አሁን ያለንበት ሁኔታ የትግራይ ወጣቶች ቆም ብለው የሚያስቡበት ወቅት መድረሱን ያመላክታል። ህወሓት እነሱን እንደ መተማመኛ ቀብድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ህወሓቶች በመንግስት ካዝና ላይ ባላቸው ባለቤትነት የተነሳ የትግራይ ወጣቶችን በልዩ ሁኔታ እየጠቀሙ እንደሆነ እያመላከቱ ነው። በዚህ ምክንያት የኦሮሞ፣ አማራ፣ ጉራጌ፣ ወላይታ ወዘተ ወጣቶች ጥያቄ ማንሳት ጀምረዋል። "ወርቁ፣ ቡናው፣ ከብቱ፣ እፈሩ፣ ማዕድኑ፣ እህሉ በየአይነቱ የሚበቅልባቸውና የሚገኝባቸው ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ፣ አቆር-ከልሎች ያሳዩት ለውጥ ከትግራይ ጋር እንዴት ይወዳደራል?" በማለት እየጠየቁ ነው። የትግራይ "ምርጥ ልጆች" በአዳሪ ትምህርት ቤት ("ቃላሚኖ") እየተማሩ ለምን እኛ ማለት ጀምረዋል።

"ቃላሚኖ ለምን ኦሮሚያ ላይ የለም? ቃላሚኖ ለምን አማራ ክልል የለም? ቃላሚኖ ለምን መላይታ ላይ የለም?" ማለት ጀምረዋል..."ባለፉት ሁለት አሰርተ አመታት አልመዳ ጨርቃጨርቅን፣ አዲግራት መድሐኒት ፋብሪካን፣ መስፍን ኢንዱስትሪያልን፣ መሰቦ ሲምንቶን፣ ብሩክ ኬሚካልን፣ ሊዘና ማዕድንን፣ ህይወት ሚካናይዜሽንን፣ ሼባ የቆዳ ማምረቻን የመሳሰሉ ዘመናዊ ፋብሪካዎች የትኛው ክልል አገኘ?" በማለት መጠየቅ ጀምረዋል።

5

በመሆኑም የትግራይ ወጣቶች ኦሰሜት ከመነዳት፣ መጠን ካለፈ ኢ-ፍትሐዊ የተጠቃሚነት ፍላጎት፣ ሌላውን በጥርጣሬ ፣ ግዮት ተቆጥበው ቆም ብለው የሚያሰቡበት ወቅት ላይ ደርሰናል። በአጭሩ ከትግራይ ወጣቶች በላይ የሚፈለግ ሚና አግጦ እየመጣ ነው። የኢትዮጵያን ሁኔታ ቤተሰባቸውንና ራሳቸውን እንዲሁም ህወሓትን ያለምንም ይሉኝታ መመርመር ይኖርባቸዋል። ከእነሱ በላቀ ሁኔታ ሌሎች የኢትዮጵያ ወጣቶች ዘንድ የለውጥ ፍላጎት በተግባር እየታየ ያለው በምን ምክንያት እንደሆነ መፈተሽ ያስፈልጋል። ባሳለፍኩት ቀኪድሬነት ዘመኔ አንድ የታዘብኩት ነገር ቢኖር በኢህአዴግ ውስጥ ያሉ "የወጣት ሊጎች" እንኳን የትግራይ ወጣቶች አብረዋቸው ሲኖሩና ላይኖሩ የሚናገሩት ፊጽሞ የተለየ ነው። በተናጠልም ሆነ በቡድን ከርከር ተጀምሮ በአጋጣሚ የትግራይ ተወላጅ ከመጣ የውይይቱ ድባብና ቃና ይቀየራል። በማህበረሰቡ ደረጃም (የትግራይ ተወላጅ ሆኖ የህወሓት ተቃዋሚን ጨምሮ) ሁኔታዎች እየተቃየሩ ነው። ህብረተሰቡ ወላጆቻቸው ባሰፈኑት ኢ-ፍትሐዊ ስርአት ምክንያት የትግራይ ወጣቶችን የማግለል ሁኔታ በሰፈው ይስተዋላል። የተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ "እከሌ እየመጣ ስለሆነ አጅንዳ አንቀይር!" የሚባልበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። አደገኛው ነገር "እከሌ" የሚባለው ሰው የትግራይ ተወላጅ መሆኑ ነው።

እናም! በትግራይ ወጣቶች ዘንድ እንደ ሀገር (እንደ ኢትዮጵያ) የመቀጠል ፍላጎት ካለ (እንዳለ አምነት አለኝ) በሰከነ መንፈስ ማሰብ የሚገባበት ጊዜ ቢኖር አሁን ነው። በትከከለኛው መረጃና ማስረጃ ላይ ተደግፎ ለለውጥ ራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። የጋራ ተስፋና ራዕይ ሊኖረን ይገባል። ከቁያችንና ከመንደራችን ተሻግረን ከአድማስ ባሻገር መመልከት ያስፈልጋል።

9

ክፍል 1

የኤፌሪት ታሪካዊ መነሻ

7

8

ምዕራፍ 1

"ውቅያኖስን በጭልፋ"

ሉፎይታ፦ "እንዳንድ ወገኖቻ ሌሎች ከልሎች መዳህ አንኳን ለቅታቸው ትግራይ ግን በማንባታው መስክ ከፍተኛ ሩጫ ላይ ናት የሚል ከስ ያሰማሉ። የአርሶም አስተያየት እንዴት ነው?"

ሰብሀት ነጋ፦ "ይህን የሚያነሳ ካለ መሀይም ነው"።

(ሉፎይታ መጽሔት ግንቦት/1990)

9

የአዲስ አበባ ባለስልጣናት እና ካድሬዎች ለማደሪያ የተሰጠን አዳራሽ በጦፈ ክርክር ተቃጥሷል። ልዩ ትኩረት የተሰጠው ደግሞ የኤፈርት ጉዳይ ሆኗል። አቶ መለስ በተበሳጨ አንደበት ሆኖ "ጊዜያችሁን እየሞተ ያለው ኤፈርት ላይ በመነጋገር አታጥፉ" ማለቱ አልተዋጠልንም። ወይዘሮ አዜብም ባለቢቷን ተከትላ " ትዕምት አፈር ልሶ አየተነሳ ነው" ማለቷ ሁኔታውን የበለጠ አከራካሪ አድርጎታል። በተለይም ሚንስትር ግርማ ብሩ "ኤፈርት ሞኖፖሊን ሊፈጥር የሚችልበት አድል የለም!" በማለት በልበ-ሙሉነት መናገሩ ምን ያህል አድርባይነት እንደተጠናወተው አመላካች መሆኑ የሚገልጽ ሆነ። ለሚንስትር ግርማ አቶ መለስ "ምንጣፍ ጎታች" የሚል ስያሜ መስጠቱ ተገቢ መሆኑን መተማመን ተደረሰ። የኢህአዴግ ጎበልስ አቶ ግርማን "ሞላጫ ሳመሩና!" ይለዋል። ድርጅቱ ደግሞ "የሸዋ ፊውዳል፣ ምንጣፍ ጎታች!" በማለት ከጅርባ ያላግጥቢታል። እነዚህ ሁሉ የአቶ ግርማ ብሩ የእንጀራ ስሞች ናቸው። ምን አልባት ጊዜው ሲደርስ ለመታሰቢያ እንዲሆን አንዲት ሠርጥ መንገድ ስያሜ ይሠጥበት ይሆናል። አሊያም እንደ ውሻ የታሠረበት ሠንሠለት ሲበጣጠስ በሙርኮው የተያዘው ሀሊናው እንደ ሳማ ይለበልበዋል...ለአፍቅሮ ነዋይ የተገዛው አንደበቱ እውነቱን ተናግሮ በመሸበት ያድራል።

ከርከሩ በተሟሟቀ ሰአት የአደራሹ በር ብርግድ ብሎ ተከፈተ። የኤፈርት ማርኬቲንግ ዋና ዴሬክተር የሆነው ታጋይ አተይ ታደለ ነበር። ታጋዩ ወደ ውስጥ ሲገባ በአንድ ጊዜ ዝምታ ሠፈነ። አንዳንዶቹ የተናገሩትን ያወቀባቸው በሚመስል መልኩ ተደናገጡ። ሁሉም ፊታቸውን ወደእኔ አዞሩ። ጓደኝነቱ የእኔ ስለሆነ እኒን ፈልጎ መምጣቱ ለሁሉም ተገልጦላቸዋል። ከዚህም በመነሳት ቶሎ ይገርው እንድወጣ መፈለጋቸው ገባኝ። በተለይም ጠርናፊያችን ካሚል አህመድ እንጉቱን በማዞርና ጭንቅላቱን በመነቅነቅ "ይዘኸው ውጣ" የሚል ምልክት አሳየኝ። ተጎኮለኛው ፀጋዬ ሐ/ማርያም ወደ ጆሮዬ ተጠግቶ "ሜኒያኩ መጣልህ!" አለኝ። ፀጋዬ የህወሓት ታጋይ ባለስልጣናትን "ሜኒያኪ" በሚል የጥቅል ስም ይጠራቸዋል። ለግብራቸው የሠጠው ቅጽል ስም ነው።

ይገርው ወጣሁ።

***

10

በአጋጣሚ አንድ ነገር ትውስ ብሎኝ፣

"አተይ! ኤፈርት (ትዕምት) ምን ማለት እንደሆነ ብዙ ካድሬዎቻችን ግራ ይገባቸዋል?"በማለት ጠየኩት።

"ትካል ዕግሪ ምትካል ትግራይ " ማለት ነው። መልሱም " የትግራይ መልሶ ማቋቋም ድርጅት ነው" አለኝ።

"የንብረቱ ምንጭ ምንድነው?...ኢህአዴግ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር ህወሓት የነበረው የፉይናንስ አቅምና ድርጅቶች ምን ያህል ነው?"

ትከ ብሎ እየተመለከተኝ፣

"አንተም እንደሌላው ያንን የትግራይ ህዝብ ጠላት የሆነው ንብረመድህን እርእያ ንግግር ሰለባ ሆንክ እንዴ?... ሰውየው በሄደበት ሁሉ የህወሓት ንብረት የተገኘው በዝርፊያ ነው እያለ እንደ አህያ ያናቱል" አለኝ።

"ታዲያ ኤፈርት የማነው?" በማለት ጠየኩት።

"አንተ የማነው ትላለህ?" እየሳቀ ጠየቀኝ።

"የትግራይ ህዝብ ነው አንዳልል ንብረትነቱን እያስተዳደረው ያለው ከህዝብ የተውጣጣ ኮሚቴ አይደለም። ወይም የከልሉ መንግስት የሚመራው አይደለም። በጐ አድራጐት ድርጅት አንዳልለው የኤጅንሲው ሰራ አስኪያጅ አሊ ሲራጅ ለአንድም ቀን ኤፈርት አፈጻጸሙን ሪፓርት አንዳላደረገ ሲያነሳ ሰምቸዋለሁ"

ሽጉብ እየተመለከተኝ:

"ስብሀትና አዜብ መስፍን አህዴዱ አሊ ሲራጅ ጋር እንዲሄዱ ትጠብቅ ነበር?_ቆይ ቆይ! ቅድም አሊ ሲራጅን ለረጅም ሰአት ስታወራው ነበር። ምንድነው የምታወሩት?"አለኝ።

"ዳታ እንዲሰጠኝ ፈልጌ ነበር። የበጐ አድራጐትና ማህበራት ኤጀንሲ ዳሬክተር እንደመሆኑ መጠን በተቋማቱ ዙሪያ ያለውን ሁኔታ ለጥናታዊ ጽሁፉ ፈልጌ ነበር"

"እና ምን ነገረህ?"በማለት ጠየቀኝ።

11

"ብዙም አልረዳኝም።"

አጨንቁሮ እየተመለከተኝ፣

"እናንተ የአዲስ አበባ ልጆች አኮ ልባችሁ አይገኝም። ከሁሉም ጋር ተመሳስላችሁ መኖር ስለምትፈልጉ ታመቻምቻላችሁ" አለኝ።

"ምን ነካህ አተይ! የቦሌን ለባሌ ሰጠሽው እኮ?"

"እንዴት?"

"ልቡ የማይገኘው ማን ሆነና?... እንደሰማሁት ኤርትራ ውስጥ አጅግ በጣም ጠመዝማዛና አስቸጋሪ የሆነ መንገድ አለ። ኤርትራውያን 'ልቡ-ትግራይ' ይሉታል። እስከ አሁንም በዚህ ስሙ የሚጠራ መንገድ እንደሆነ ሰምቻለሁ። መቼም ሳታውቀው አትቀርም" አልኩት።

"የሲ.ማሊ.ሞን መንገድ ስላላዩት ነው?..እንደውም አንድ ነገር አስታወስከኝ። በትግራይ አባቶች ዘንድ በዚህ ዙሪያ የሚባል ነገር አለ። ቅድም ባልከው ጠመዝማዛ መንገድ ላይ የዘመዱ ንጉስ ሀይለስላሴ፣ የኤርትራው አገር ጥሎና የትግራዩ አገር ጥሎ እየሄዱ ነበር። እናም የኤርትራው ጥሎ ወደ ንጉሱ ጠጋ ይሉና 'ጃንሆይ ይህ መንገድ ልበ -ትግራይ እንደሚባል የውቃሉ?' ብለው ይጠይቋቸዋል። ንጉሱም ኪት ብለው ይሉቱና ወደ ትግራዩ ጥሎ ዞረው "ይሄን መንገድ _' የትግራዩ ጥሎ ምን ብሎ እንደመለሰ ታውቃለህ?"

"አላውቅም።"

12

"ጃንሆይ ኤርትራውያን እናንተን ሳያገኙ በፊት የሰጡን ሰያሜ ነው በማለት እዞረው ነገሯቸው" በማለት በኩራት ነገረኝ።

"እሱን ተወውና ዛሬ በየቡድኑ ተነሰቶ ወደነበረው ኢፈርት አጀንዳ እንመለስ። በእነዚህ ተቋማት ዙሪያ አንዱ የተነሳው የፓርቲ ንብረት አይደሉም ወይ ነው? _የፓለቲካ ፓርቲዎች አዋጅ አይፈቅድም። በአዋጁ አንቀጽ ... መሰረት ፓርቲዎች በንግድ ስራ መሰማራት እንደማይችሉ ይጠቅሳል።"

"የትግራይ ህዝብ ነው ካልከኝ እሰቲ ለህዝቡ ማህበራዊ ልማት የዋለውን በፐርሰንት ንገረኝ?... ስንት ትምህርት ቤት፣ ስንት ጤና ኬላ፣ ሆስፒታል ለህዝቡ እንደገነባችሁ ንገረኝ?"

አተይ እንዲህ በማለት ተናገረ፣

"እንደዚህ አይነት ልማቶች በትግራይ ልማት ማህበር፣ በከልሉ መንግስትና በፌደራል መንግስት ድጋፍ የሚሰራ እንደሆኑ አቅጣጫ ተቀምጧል። ኤፈርት በትላልቅ ግራንድ ፐሮጀክቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል።"

"እንተ ደግሞ!... የትግራይ ህዝብ አንጡራ ሀብት ነው!!" ብሎ በግራ አይኑ ጠቀሰኝ።

እኔም በቀኝ እይኔ ጠቀሰኩት። የሀገሪቱ አዋጅ ለእንዱ በጥቅሻ ሰሊላው በትከሻ የሚሸከሙት ሆኗል።

"ነገ ቢሊዩን ብር የማይሰበሰብ አካውንት እንዲገባ ተደርጓል እንዴ?"

"ከእርባ አመት በኋላ አብዬታዊ ዴሞክራሲ ሙሉ ለሙሉ በትግራይ ከስሞ የሊብራል አሰተሳሰብ ይተካል።"

"እንዴ! ዛሬ አዶ መለስ ያስተማረንን ገደል አስገባኸው"

አሁንም ጠቀሰኝ።

እኔም ጠቀስኩት።

***

13

ማደሪያችን በፌደራል ፖሊስ እና ልዩ ሀይል የተወረጠ በመሆኑ ከፍተኛ ጭንቀት ይፈጥራል። በየአሰር እርምጃ ፖሊሶቹ በተጠንቀቅ ቆመዋል። የማይታለፍ አጣዳፊ ምክንያት ከሌለ በሰተቀር እንደ ጅበራ የተገተሩትን ፖሊሶች ቀርቦ ማናገር እንደማይቻል ጥብቅ መመሪያ ተላልፏል። እነሱም ሳይነገራቸው አልቀረም ገና ሰንቀርባቸው ፊታቸውን ይከሰክሳሉ። በፈረጠመ ሰውነታቸው ላይ ያነገቱቱን ጠብመንጃ መነካካት ይጀምራሉ። የተደፈነ ልባቸውን ለማሳየት ይሞክራሉ። አልፎ አልፎ ደጋን አማራቸውን እየንተቱ ይንጎማለላሉ። ብዙዎቹ ፅልምያኮስ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም ሠልጣኝ ባላሰልጣናት እንድ ጊዜ ወደ ማደሪያ ግቢያችን ከገባን በኋላ መውጣት አንችልም። ፀሀይ ከጠለቀች በኋላ በከተማዋ የተገኘ ባላሰልጣን በፖሊስ ታድኖ ይያዛል። ለሚፈፀመው መመሪያ መጣስ የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ እንዲፈርም ይደረጋል። ለመጣበት የብሔር ድርጅት እና ለስልጠናው ቡድን መሪ ሪፖርት ይደረጋል። ጠዋት የቡድን ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት ከተማ የተገኘው ካድሬ ሂስ ያወርዳል። ግለ ሂስ ይሰጠዋል። ሁለተኛ እንደማይደግም ቃል አስሮ ወደ ስልጠናው ይመለሳል።

ከዚህ በተለየ ለተወሰኑ ቁልፍ ባለስልጣናት እንደፈለጉ እንዲዘዋወሩ የይለፍ ካርድ ተሰጥቷቸዋል። ራሳቸውን የሚጠብቁበት መሳሪያ እንዲይዙ ተፈቅዷል። ከግቢው ሲወጡ እና ሲገቡ አይፈተሹም። የይለፍ ቢጫ ካርድ የመስጠት ስልጣን የህወሓት ፕሮፖጋንዳ ሀላፊው

ቱድሮስ ሀጎስ በመሆኑ ምክንያት አብዛኞቹ የትግራይ ልጆች እንደፈለጉ መውጣትና መግባት እንዲችሉ ሆነዋል። ከዚህም አልፈው በመሄድ ሹፈሮቻቸውን በመሀል ከተማ አልጋ እንዲይዙ አድርገዋል። በግል መኪና እንደልባቸው መንቀሳቀስ ችለዋል። በተቃራኒው ሚኒስትሮቹን ጨምሮ የሌሎች ክልል ባለስልጣናት ሹፌራቸውን ከነመኪና ሸኝተዋል። ራሳቸው እያሽከረከሩ የመጡትም የማለፊያ ካርድ ስለሌላቸው ማንቀሳቀስ አይችሉም።

14

እንደዚህ አይነት የቢጫ ካርድ እና የግል መኪና ከተፈቀደላቸው ታጋይ ባላስልጣናት መካከል አተይ ታደለ አንዱ ነው። በፈለገው ሰአት ውጥቶ የመግባት ልዩ መብት ተሰጥቶታል። የግል ሹፌሩ አዳማን ሳይለቅ አልቤርጎ ለወራት እንዲይዝ አድርጓል። ከህወሓት ውጪ ሌላ ጌታ የሌለው ታጋይ አተይ ሲወጣ እና ሲገባ ሌሎቻችንን ወደ ታች የሚመለከተው በያዛት ካርድ በመመካት ነው። ከሌላ ብሔረሰብ የመጡ ባለስልጣናት ሲያናግር እንኳ ካርዱን እንደ መኪና ቁልፍ ያሽከረክራል። እንደ አውራ ዶሮ ይንቀባረራል። በሙሉ አይኑ ለማየት አስከመጠየፍ ድረስ አንድ አይኑን ዘግቶ ይመለከታል።

ከአተይ ጋር ወደ ውጪው በር ስንሄድ ከኪሱ ውስጥ አውጥቶ ቢጫውን ካርድ ሰጠኝ። ለሶስት ቀናት ብቻ የሆስፒታል ጉብኝት እንዳለኝ ተደርጎ የተሰራ የይለፍ ወረቀት ነበር። በር ላይ ያሉት ዋርድያዎች ጥያቄ ካቀረቡልኝ ወደ ሆስፒታል እየሄድኩ እንደሆነ እንድነግራቸው አስጠነቀቀኝ። በተሳሳተ እና ዙሪያ ጥምጥም በሆነ መንገድ ወደ ውጭ መውጣቴ እልተመቸኝም። ቢሆንም ግን ተመሳሳይ መልክ ማየቱ ሰልችቶኛል። ወጣ ብሎ አየር መውሰዱ ከእስር ቤት የመለቀቅ ያህል ተሰምቶኛል።

የመውጫ በር ላይ ስንደርስ ብዙ ባለስልጣናት እትወጡም በመባላቸው ተሰፋ ቆርጠው ሲመለሱ አገኘናቸው። የደቡብ ክልል ፕሬዝዳንቱ ሽፈራው ሽጉጤ፣ እሱን የተካው ፕሬዝዳንት ደሱ፣ የፌደሬሽን አፈጉባኤ ደግፌ ቡላ ከእነ ባለቤቱ ም/ሚኒስትር ስመኝ ውቤ እንዲሁም ሚንስትር አለማየሁ ተገኑ በቅርበት የተመለከትኳቸው ነበሩ። ሚኒስትር አለማየሁ ከርቀት ሲመለከተኝ አንገቱን እየነቀነቀ "ያላዝናል" የሚል ምልክት አሳየኝ። እነዚህ ቱባ ባለስልጣናት መንቀሳቀስ ተከልክለዋል። በተቃራኒው እንደ አተይ ያሉ ማንም የማያውቃቸው ካድሬዎች ወታደራዊ ሰላምታ እየተሰጣቸው ሲወጡና ሲገቡ ለተመለከተ በጣም ያበሳጫል። ህሊና ያደማል። እኔም ከአግር ጥፍሬ እስከ ራስ ጠጉሬ ሊደቂቃዎች ነዝሮኝ ነበር። ለምን እንደሆነ እንጃ መውጣት

የተከሰከሱትን ሚኒሰትሮች ሰመለከት ከወትሮው የተለየ ንዴት ተሰምቶኝ ነበር። ርግጥ የሚባለውን ላዳመጠና ላስተዋለ ሁሉ የሚያናድድ ነው። ችግሩ ብዙዎቻችን ሰማየት አንጂ ለማስተዋል፤ ለመስማት እንጂ ለማዳመጥ ፍላጎትና ወኔው የለንም። ለመኖር ስንል እንዋሻለን። ብዙውን ጊዜ ብዕርና ወረቀታችን ከውስጣችን ጋር የተከራከረውን እና የተሚገተውን በተቃራኒ ያሠፍራል። እውነትን መጻፍ፣ ሐቅን ማስተላለፍ ሰለምንፈራ ብዕራችን ከጅምሩ ይሠበራል። የምንናገረው እና የምንፅፈው የእነ በረከት ሰምአንን መልክ እና ገፅታ መለዋወጥ እያየን ነው። አድርባዮች በመሆናችን እኛ ጋር እውነት እንደ ነውር ይቆጠራል። የወስላታነት መስቀያ ጥቁር እንጨት ውጠን እንኖራለን።

15

የማደሪያችንን የውጭ በር አልፈን እንደወጣን የአተይ መኪና ፊት ለፊታችን መጥቶ ቆመ። በፍጥነት ተያይዘን ወደ መሀል ከተማ አመራን። የአዳማ ከተማ ጭር ብላለች። ባልተለመደ ሁኔታ ነዋሪው በጊዜ ወደ ቤቱ ገብቷል። መንገዱ ሁሉ ሰፍር ቁጥር በሌላቸው የፌደራል ፖሊስ አባላት ተወሯል። የከተማው ዋና መንገድ በከፍተኛ ፍጥነት በሚመላለሱ የፖሊስ መኪኖች ተወጥሯል። በእውራ መንገዶች ጎን በየሀምሳ ሜትሩ ሁለት ሁለት አጋዚዎች አፈሙዛቸውን ወድረው ይታያሉ። መታጠፊያና ኩርባ መንገዶች በሠራዊቱ የፈጥኝ ተይዟል። በአጠገባቸው የሚያልፈውን መንገደኛ ከራሰ ፀጉር እሰከ እግር ጥፍሩ በመገለመጥ ይመለከታሉ። አልፎ አልፎ ያየናቸው መንገደኞች ባለቀያይ ኮፍዮቹን ሠረቅ አድርገው በማየት በፍጥነት ይራመዳሉ። አላሰችል ሲላቸው ወደኋላ ገልመጥ ገልመጥ በማለት ፍጥነታቸውን ይጨምራሉ።

ወደ መሀል ከተማ ሰንደርስ የቡና ቤት መብራቶች ደምቀው በርተዋል። የከፈቱት ሙዚቃም ከሩቅ ይጣራል። ሆኖም ግን ከተማዋን ፍርሃት ስለዋጣት ገብቶ የሚዝናና የለም። በየቡናቤቱ ጥግ የተወሸቁት ልዩ ኮማንዶዎች ከተማዋ ባድማ እንድትመስል አድርገዋታል። በርካታ ሱቆች በጊዜ ተዘግተዋል። አልፎ አልፎ ውር ውር የሚሉ ጋሪ እና ባጃጆች ይታያሉ። በህዝቡ መራወጥ የተሸፈነው የከተማዋ ቆሸማዳነት በግላጭ ይታያል።

አዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያለው የውጭ ድርጅት በፐሮጀክት ማናጀርነት የሚሰራ ጓደኛ ስላለኝ ቢያንስ በሁለት ወር አንዴ አሉዳለሁ። ከምንም በላይ የመንገዱ መበላሸት እና አለመኖር በጣም ያስገርመኛል። ዋና የተባለው መንገድ ራሱ ቀጭን፣ ደረጃውን ያልጠበቀ በዛ ላይ በየቦታው የተቦረቦረ በመሆኑ የመኪና ጠር ነው። በዚህ ምክንያት የሚደርሰው የመኪና አደጋ ከፍተኛ ነው።

ቡተለይም ከተማዋን ለቆ ለመውጣት እና ከአዲስ አበባ ቡተታራኒ ወደ ከተማዋ ለመግባት መንገድ የሚያሳየው ፍጻ የሚረሳ አይደለም።

የአጋጣሚ ነገር ሆኖ በከተማዋ የሚገናውን አንድ ለአናቱ የሆነ የመንግስት ሆስፒታል በተደጋጋሚ የመሔድ አድል አጋጥሞኝ ነበር። በጦሩ ነበራ "ሐይለማሪያም ማሞ ስም የተሰየመው ሪፈራል ሆስፒታል እጅግ በጣም ያረጀ፣ ሰረጅም ጊዜያት እድሳት የማይደረግለትና የተረሳ ነው። ለሶስት ያህል ጊዜያቶች ወደ ሆስፒታሉ ሠው ለመጠየቅ ሔጀ በቁሻሻ እና መጥፎ ሽታ ምክንያት ህመም ተሸክሜ ተመልሻለሁ። ከሁሉም የሚገርመኝ ሆስፒታሉን ሊጎበኝ አሊያም ሠው ሊጠይቅ ሔዶ "ሰልታመመ መጣሁ!" ብሎ የተናገረ ሠው አጋጥሞኝ አያውቅም። በመጨረሻው የሆስፒታሉ ጉዞዬ የሔድኩት ከአዲስ አበባ ተዘዋውሮ የአዳማ ምክትል ከንቲባ ሆኖ ከተመደበ በቀለ ከሚባል "የታሰተር ባደግ ትቤት" ጓደኛዬ ጋር ነበር።

16

ለበቀለ ስለ ሆስፒታሉ እርጅና እና መቆሸሽ አንሰቱ ስጠይቀው የውሻ ምላሱን እያሳየኝ፣

"ሐይለማሪያም ማሞ ወደ ምድር ተመልሶ ቢመጣ ስቅስቅ ብሎ እያለቀሰ ለምን ይሔ ሆስፒታል በእኔ ስም እንዲጠራ አደረጋችሁ? ብሎ ይለናል" በማለት ነገረኝ። አስከትሎም "ለአህዴድ ሠማዕታት ሐውልት ማስገንቢያ 20 ሚሊዮን ብር የለገሠው ሼህ አላሙዲን ድርጅት ለሆስፒታሉ መጠገኛ አንድ ሚሊዮን ብር ጠይቀናቸው ዛሬ ነገ እያሉ ያመላልሱናል" በማለት በንዴት ተናገረ። የከለሉ መንግስትም ቢሆን ከፈደራል መንግስት አሳብ መውጣት እንደማይቻል:

"በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የጤና ፖሊሲ መሰረት ትኩረት የምንሠጠው ለጤና ጣቢያ እንጂ ለሆስፒታል አይደለም በማለት በጀት ከለከለን" ሲል አጫወተኝ።

ርግጥም አቶ መለስ የጻፈው "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የጤና ፖሊሲ" በመከላከል ላይ የሚያተኩር ስለተባለ ሆስፒታል እና ከፍተኛ የጤና ሙያተኞችን መፍጠርን እንደማያበረታታ ስለማውቅ የምክትል ከንቲባው አባባል አዲስ አልሆነብኝም። ባይሆን ጭምቱ በቁ እንጉቱን እየነቀነቀ "በትግራይ ዋና ከተማ የተሰራው የመቀሌ ሆስፒታል በኢትዮጵያ የሬሳ ምርመራ ከሚካሄድባቸው ሁለት ሆስፒታሎች አንዱ ሆኖ ሲገነባ፣ የጨፈው መቀመጫ ያለውን ቀለም ለመቀባት ትኩረት አይደለም ሲባል በአንድ ሀገር ሁለት ፖሊሲ አለወይ?" በማለት ለጠየቀኝ በቂ ምላሽ መስጠት አልቻልኩም። በመልሴም እሱ የማያውቀው፣ እኔ የማውቀው የተለየ ነገር

የለኝም። መጀመሪያ በአዳማ ዙሪያ ከአርሲ አዋርጠው የመጡ በሸተኞች አልጋ አጥተው አግዳሚ ወንበር ላይ ተረፍርፈው ህይወታቸው ሲያልፍ እየተመለከትኩ "የመከላከል... የማከም...ፖሊሲ" አያልኩ ልደበኩር አልችልም። ...ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰጤና ጥበቃ ሚኒስትሯ፣... ከጤና ጥበቃ ሚኒስትሯ ለአዲስ አበባ ጤና ቢሮ በተጻፈ ደብዳቤ ከአዲስ አበባ ህዝብ ላይ ተቀንሶ 17 ሚሊዮን ብር ለትዕምት (አዲግራት መድሐኒት ፋብሪካ) የተሰጠበትን እያየሁ "አብየ ታዊ ዴሞክራሲ አንድ አይነት ፖሊሲ ይከተላል" ልለው አልችልም። ሽምጥጥ አድርጌ የምክድበት አንዳችም ምክንያት የለኝም። በዝምታኝነት የማወቀው በቀለ ቁጣው ፣ንፍሎ ትግራይ ተጠቅማ እያየሁ ላሰዝበው አልፈለኩም።

ርግጥ ከአዲስ አበባ ህዝብ የጤና ሰራ ከተመደበው የአንድ አመት አጠቃላይ ባጀት ከሆነው 6 ሚሊዮን ብር ውስጥ አራት ሚሊዮኑን (67%) ተነጥቆ ለትዕምት የተሰጠበት ሠነድ በእይኔ በብረቱ አይቼ እንዴት ልዋሸው እችላለሁ?... እትብቴን የተሸከመችው "አዱነኔ" ምን ትለኛለች?

***

17

ሹፌሩ ደመቅ ያለ የምሽት ከበብ ጋር ሲደርስ መኪናውን አቆመ። ቀለጠፍ ቀለጠፍ ብለን ከመኪና ወረድን። አተይ በመስኮት ብኩል ለብቻው ሹፌሩን ማውራት ጀመረ። ፈንጠር ብዬ የዳንስ ቤቱ በር ላይ ቆምኩ። ከመፅቅበት ከጀርባዬ "ጋሼ! አንድ ብር አበድረኝ!" የሚል ድምጽ ተሰማኝ። ዞር ብዬ ስመለከተው ቡትቶ የለበሰ ያበደ ሰው ነው። ሰውየው በቂጡ መሬት ላይ ተቀምጧል። የሚቅመውን ጫት መሬት ላይ ዘርግቷል። በጉንጮቹ የጠቀጠቀው ጫት ሁለት ኳስ አክሏል። አንደገመድ የተጠቀለለው ፀጉር ወርዶ መሬት ደርሷል። የቦብ ማርሌን ዘመዶች አስመስሎታል። አንገቱን በመቅላቱ ፊቱን ማየት ባልችልም የሚያጨሳት ሲጋራ የምትፈነረው ብርሃን የደለዘ መልኩን ለስኮንዶች ታሳያለች። የቀይ ጥቁር እንደሆነ ያስታውቃል።

"ጋሼ! አንድ ብር አበድረኝ!" የሚለውን የልመና ዘዴ ስለማረከኝ እጄን ወደ ኪሴ ሠደድኩ። በአጋጣሚ የነበረኝ ድፍን አምስ ብር ነበር። እንዲዘረዝርና የጠየቀኝ እንዲወሰድ ነገርኩት። ሠውየው ቀና ሲል አይን ለአይን ተጋጠምን። እጢዬ ዱብ አለ። በፍጹም ያልጠበኩት ነበር። ሰውየው እንዳወኩት ሲያውቅ ከመሬት ላይ ተነሳ። ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎና ሠውነቱን እየፎከተ ከኪሱ ዝርዝር ብሮች አውጥቶ መቁጠር ጀመረ። ሲጠጋኝ የለበሰው ቡትቶ ልብስ

ቀረንጠሎ በጣም ይሸታል። አይነ ምድሩን በራሱ ላይ የተጸዳዳ ያህል ውርናቱ አያስቀምጥም። ለጥቂት ሠኮንዶች ከአመሥመቀ በኋላ እጆቼን አገላብጦ የሚሰም አስመስሎ በብጣሽ ወረቀት ላይ የሞባይልህን ባትሪ ንቀል አለኝ። ባትሪ እስከመነቀል የሚደርስ ኮር ምን እንዳመጣው ግራ ገባኝ።

18

አስከትሎም ስሜን እየጠራ፦

"ከሁለት ሰዓት በኋላ በጀርባ በኩል ባለው አልቤርን ናኒ...የመኝታ ቁጥሩ ሠባት ነው። እደራህን እንዳወከኝ ለማንም እንዳትናገር። መስማማትህን በአይንህ ብቻ ምልክት አሳየኝ" በማለት ታናገረ። መስማማቴን በቅንድቤ ብቻ አሳየሁት። "መኝታ ቁጥር ሰባት" አለኝ በድጋሚ። እንደ አብድ እየተቅበዘበዘ ሁለት እጀን አገላብጦ ከሳመኝ በኋላ መሬት ላይ ተመልሶ ተቀመጠ።

የሆዴን በሆዴ ይዤ ወደ ጭፈራ ቤቱ ከአተይ ጋር ተያይዘን ገባን። ከውጪው ሙቀት በላይ የምሽት ቤቱ እንደ ወላፈን ይለበልባል። ይህም ሆኖ ቤቱ እስከ አፍንጫው ተጠቅጥቋል። የጆሮ ታምቡር በሚቀድ ድምጽ የሚዘፍነውን ዘፋኝ ከበው የሚጨፍሩት ሠዎች አብረውት ይዘፍናሉ። ወደ መድረኩ ስመለከት የዘፋኙ ግንባር እና ደረት በቀያይ ብሮች እስኪሸፈን ድረስ በመሸቀዳደም ይሸልሙታል። አሱም ያለ ማቋረጥ "እምበር ተጋዳላይ" የሚለውን የህወሓት የበረሃ ዘፈን ያንቆረቁራል። የእንጉርጉሮው መድመቅና የደናሾች ቁመና ስመለከት የሞቅታ ድባቡ በጭፈራ ቤቱ መንገሱን ይናገራል። አልኮል ያጋለው ጨዋታ ከከበሮው ድለቃ ጋር ተደባልቆ ቆሌ ይገፋል። የሚያፈዝና የሚያደነግዝ አዚም ይፈጥራል። በየቦታው የሚንቦለቦለው የሲጋራ ጭስ ቤቱን ከማፈኑም በላይ መጥፎ ሽታ ፈጥሯል።

18

ፍርሃትና ጭንቀቱ ባይለቀኝም እንደምንም ራሴን አረጋግቼ አከባቢውን ቃኘሁ። ዳንስ ቤቱን በሙሉ ያጥለቀለቁት የህወሓት ካድሬዎች ናቸው። የህወሓት ፖለቲካና ድርጅት ሀላፊ ከሆኑት ቴድሮስ ሀጎስ እና ጎበዛይ ጀምሮ እንድም የህወሓት ሰው የቀረ አይመስልም። የፓርቲው የተሐድሶ ፕሮግራም ይመስላል። አብዛኛዎቹን አውቃቸዋለሁ። አልፎ አልፎ አይናቸውን በማቁለጭለጭ ረፍት የነሱ ፀጉረ ልውጦች በመሀላቸው ይገኛሉ። የአይናቸው መቅበዝበዝ እና ፋታ ማጣት ምንአልባት የደህንነት ስራ የሚሰሩ እንደሆነ ገምቻለሁ። በህሓት ውስጥ ሠላይ እና ተሠላይ በቅጡ አይታወቅም። ዛሬ ሠላይ የሆነው ነገ ተገልብጦ ተሠላይ ይሆናል። በጋራ ጠላት ከመጠባበቅ ባልተናነሠ እርስ በራስ በአይነ ቁራኛ ይጠባበቃሉ።

ከሁሉም ቀጠሮዎች በምሽት ቤቱ የሚገኙት የህወሓት ካድሬዎች እስከ ዞን አመራር የደረሰችን ጨምሮ ነው። በሌላ አነጋገር ሁሉም የቢሮ ካርድ ባለቤቶች ከላይ እስከ ታች አንሱ ናቸው። የህዴድ እና ደኢህዴግ ሚኒስትሮች ከጣቢ አንዳይወጡ ማስፈራሪያ እየተሰጣቸው የህወሓት የዞን ታጋይ ባለስልጣናት ሉዳማን በ"እንበር ተጋዳላይ" ሲጨፍሩ ማየት ከመገረምም ያስገነዝባል። ሴላው የገረመኝ ሁሉም የሚጠጡት የመጠጥ አይነት ተመሳሳይ ነው። ከማን አንሺ በሚመስል መልኩ በየጠረጴዛው ላይ የውስኪ ጠርሙስ ተቀምጧል። ይሔ የተለመደ ባህሪያቸው ቢሆንም ቢጋራ በሚገኙ ሠላት ያደርጉታል ብዬ አልጠበኩም። ለካስ የሶዶምና የገሞራ ሠዎች ከድሮ ህጋቸው ብዙም አልተላቀቁም። አንዳንድ ቦታ አኩል ናቸው።

አርግጥም፣ የጋራ አሸናፊዎች ናቸው። በታሪክ አጋጣሚ የዛሬ ድል አድራጊዎች ሆነዋል። ግዜን ተቆጣጥረዋልና ሌሎች የተነፈጋቸውን ከብርና ውዳሴ ቢሹ የሚበዛባቸው አይደለም። የተንናጸፉትን እከሊል በውስኪ ተሐድሶ ቢያከብሩ ለምን ይገርመናል?... የትላንትናን ችግር፣ ስቃይ፣ ረሀብ እና ድንቁርናቸውን ማካካስ ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱ እንደዚህ አይነት አስረሽምቺው ነው። አይናቸውን በጨው የታጠቡ ደፋሮች የሆኑት ካለማወቅ ሊላቀቁ ባለማቻላቸው ነው። ርግጥ ባህሪያዊ የሆነባቸው የበታችነት ስሜት ያቆቅ ህይወት እንዲመሩ አድርጎአቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ የተጠናወታቸው የበታችነት ስሜት የደነደን ትከሻ እንዲሸከሙ አድል ፈጥሮላቸዋል። ለአይን ሳይሞሉ፣ አይን ተጥሎባቸዋል። አመጣጣቸው ከገበሎ ወገን ቢሆንም አንደ አንበሳ ተቆጥረዋል።

19

በነገራችን ላይ አብዛኛው የከተማ ካድሬዎች ልብ ለልብ ስንነጋገር በአንድ ነገር እንስማማለን። ይሽውም ከአቶ መለስ ጀምሮ ያሉትን የህወሓት ባለስልጣናት ቀርበን ስናውቃቸው የሚሰማን ስሜት ነው። ከርቀት ግዙፍ የሚመስሉን ሠዎች በቅርበት ስናያቸው እያነሱብን ድንክዬ ይሆናሉ። የጭንቅላት ባዶነታቸውን እንዳብሳለን። አለበለዚያም የበታችነት ስሜታቸው የሚፈጥርባቸውን ቅናት እናየዋለን። ከፊታችን ተቀምጠው እንደ በረዶ ከምር ሲሟሙና ሲቀልጡ እንመለከታለን። የተለበጠበት ኖራ አጠገባችን ሲረግፍ እናያለን። በኖራ የተቀባው መቃበሪያቸው ሲከፈት "እፉ- ዘርጣ" መሆናቸውን እንመለከታለን።

እንደ እኔ የቅርብ ጓደኛ አድርጎአቸው ሲኖር ደግሞ ብዙ ነገር ይታዘባል። በተለይም እንደዘሬው አዘውትሮ የምሽት ከበብ ከእነሱ ጋር የሚወጣ ሰው ሰነ- ስርአት አልባነታቸውን በቀላሉ ማየት ይችላል። እንደ ተቀለበ ኮርማ የፍትወት ፍላጎታቸው ቀሚስ ባዩ ቁጥር ሲንበለበል ይመለከታል። በአጠገባቸው ያለፈች የቡና ቤት ሴት ጨብጠው ወሲባዊ ትንኮሳ ካላደረጉ የተገናኙ አይመስላቸውም። ያቺንም ይቺንም በነገር እየነነተሉ መዳራት ይወዳሉ። ሴቶችን አክብሮ በትህትና ማናገር ውርደት ይመስላቸዋል። የቡና ቤት ሴቶች ትንሽ ኮስተር ካሉባቸው ደግሞ ከህወሓት ታጋዮች አንደበት የሚወጣው ፀያፍ ቃላት ለጆሮ ይዘገንናል። በእደባባይ ሰመናገር ይከብዳል። "ለምን ትሰድበኛለህ" ብላ ከጠየቀች የአፀፋ ምላሻቸው በጥፊ መመታት ነው። በትንሽ ቃል ፊልቶ የሚገነፍለው "ውንቅላታቸው ለሁሉም ነገር ምላሹ የፈረጠመ ጡንቻ ማሳየት ነው። የሚያሳዝነው ሴተኛ አዳሪዎች እኛንም በእነሱ አይን ስለሚመለከቱን ይንቁናል። ከነሱ ሰዎች ጋር ውሰን እኛም አናንሳለን። ለነገሩ አባባሉስ ቢሆን "ከማን ጋር እንደምትውል ንገረኝ እና ማንነትህን እነግርሀለሁ" አይደል የሚለው!... ከአፈ ፀያፎች ጋር ውለን እኛስ ምን ልንሆን እንችላለን?...

20

እንደእውነቱ ከሆነ ከኑግ የተገኘ ሠሊጥ በመሆናችን የውርደቱን ዳፋ መውሰድ ያለብን ራሳችን ነን። ራሳችንን ለጊዜያዊ ጥቅም አሳልፈን የሠጠን በመሆኑ ይገባናል። ሀብረተሰቡ በንቀት እና በጥርጣሬ አይን ቢያየን የሚያንሰን አይደለም። የሚያሳዝነው የእንዳንዶቻችን የታማኝነታችን ምንጩ ለአርቴፊሻል ስልጣን እና ብርጭቆ ውስኪ ፍላጎት ማርኪያ ያልዘለለ መሆኑ ነው። መንታ ምላስ ተሸክመን የምንዞረው ማንነታችን አሳልፈን ስለሰጠን ነው። ሰዎች በንቀት የሚመለከቱን ከአለት ተአለት ግብራችን ተነስተው ነው። በህብረተሰቡ ዘንድ መሳቂያ እና መሳለቂያ የሆነው በራሳችን ምክንያት ነው። በህቅ እንነጋገር ከተባለ አፍና ልባችን ለየቅል በመሆኑ ምክንያት ህዝቡ ጠልቶናል እስከ መቼ ራሳችንን እያታለልን እንኖራለን?... አሁን አሁንማ ራሳችንን ማታለል ባህሪያዊ እየሆነብን እማዚአብሔርን ሳይቀር ለማታለል እንፈልጋለን።

"ምን እያሰብክ ነው?" የሚለው የአተይ ጥያቄ ከሐዲኩበት ረዥም ሀሳብ መለሰኝ። የማስበውን ያወቀ ስለመሰለኝ ደነገጥኩ። ካወኩት ቀን ጀምሮ እንደ ሴት የሠው ምስል አይቶ ስሜት የማንበብ ችሎታ እንዳለው ተገንዝቢያለው። አንዳንድ ጊዜ ኮከብ ቆጣሪ ይመስለኛል። ሳላስበው በውስጤ ያለውን እየተናገረ ቆሌዬን ይገፋል።

ሰማራ መጋቡት ውስጥ ሆኜ፣
ዋሙሪቃው ጩኸት ረበሸኝ። አንተን አልረበሸህምና" በማለት መልሺ ጠየኩት። ደማቅነት
የሌለው ደብዘዝ ብርሃን ሙሉ ገፅታውን ሲያሳየኝ አልቻለም።

አስተናጋጁን ለመጥራት እያጨበጨበና ትናጋው አስኪጥል እየጮኸ፣

"መጠጣት ስላልጀመርክ ነው። ደግመገም ስታደርገው እንደ መአሲ የሰው ሚስት ታማግጣለህ" በማለት ተናገረ። አስከትሎም እጅቹን በጥሞ በኩል ወደ ሚደንሱት ሠዎች አመላከተኝ። ጓደኛዬ ፍሰሀ መአሲ እና ሞንጆሪኖ ነበሩ።የፊረሰው የካሳንችሱ መንግስት ባለቢቶች። በጣም ገረመኝ። ዛሬም አልተለያዩም። እፍ ለአፍ ገጥመው ይደንሳሉ። "ሞንጆሪኖ" የፈትለወርቅ ገ/እግዚአብሔር የፊረስ ስሟ ነው። "መአሲ" ደግሞ የፍሰሀ ዘሪሁን!... እውነትም እንደ ድሮው አንድ አካል፣ አንድ አምሳል ሆነው ሲያወሩ ስመለከት በጣም ደነቀኝ። በትዝታም ወደኋላ ወሰደኝ። ቀና ብዬ ተመለከትኳቸው የመአሲ ቅንዝርኝነት ቆዳው ተሸብሽቦ አልበረደም። የጫን ገረዱ ሞንጆሪኖም እንደ ማስትሽ ተጣብቃበታለች።

ሁለቱ የካዘንችሰ ዘውዶች!
የህወሓት ጥሩቱር እንቁዎች!

21

አተይ ሳቁን ማቆም አልቻለም... የማአሲንና ሞንጆሪኖን ትዕይንት እየተመለከተ ሆዱን እያንቀጠቀጠ ይስቃል። ደጋግሞ እየጠቀሰኝ ይሳቃል። አተኩሬ ሳየው ጤነኛ አልመስለኝ አለ። "ቀበሮ ዘሎ አልሆንለት ሲለውና ተስፋ ሲቆርጥ "የወይኑ ፍሬ መራራ ነው" በማለት ጥሎ ይሔዳል" የሚለው አባባል ሳስበው በጭንቅላቴ መጣ። ቀረብ ብዬ እንዳየሁት በአተይ እና መአሲ መካከል ጥላቻና መናናቅ አለ። አተይ ይጠላዋል። መአሲ ይንቀዋል። በተለይ የመአሲ ንቀት ወሰን የለውም። የትየለሌ ነው። እሱን ከአተይ ጋር ካገኘኝ "ከዚህ የተንኮል ድርና ማግ ጠርናፊ ጋር ምን ትሰራለህ?" በማለት ይቆጣኛል። በተቻለ መጠን እንድሸሸው ይመክረኛል። እኔም "ፊሽ አያሳስብህ አተይን አይኑንም ጥርሱንም ቀንዱንም እውቀዋለሁ" አለዋለሁ። በርግጥም ይህን ውሸልሸል፣ ውሻ በጨው የማይቀመሰው ፍጡር ባለውቀው ይገርመኝ ነበር። በየቀኑ የጭቃ አሾህን ሲወረውር እያየሁት ባልጠነቀቅ ከእሱ በምን አለያለሁ?...

ለነገሩ አተይም ቢሆን ለመአሲ የሚተማ ሠው አይደለም። የሽላይነቱን ለማሳየት የማይቆፍርለት ጉድጓድ የለም። በረቱ አያሞነሰው ከጀርባው በአስራ አንድ ቁጥር ሚስማር ያስቀጠቅጠዋል። ሰምሳሌ የድሬዳዋ ከንቲባ እንዲሆን ከጀርባ ግራት አድርጓል። እንዲቀየር ያደረገው በአዲስ አበባ ከቆየ ያሳጣኛል በሚል ቅናት ተነሳስቶ ነበር። እንደጠበቀው ሳይሆን መአሲ የድሬዳዋ ከንቲባ ሲሆን ሰሙ እንደ ዝሆን ገዘፈ። የኢኮሞሚ አቅሙ እየደለበ ሔደ። ይህን በማየቁ ሌላ ሴራ ጎነጎነበት። ገንዘብ በአካፋ ከሚዛቅበት ድሬዳዋ ተነስቶ የሰባራ ሳንቲም ጉድለት የምታባርረው መቀሌ በከንቲባነት እንዲመደብ አደረገ። አስተሳሰቡ ገና ኮሜዲ አልወጣም ተብሎ ከሚነገርለት የትግራይ ፕሬዝዳንት አለቃ ፀጋዬ ጋር አጣመደው። በብዙ የነወሐት ታጋይ ባለስልጣናት እንደተገለጠው ከአለቃ ፀጋዬ ጋር መስራት ማለት አስር አመት ከአለም አንቅስቃሴ ወደ ኋላ መጎተት ነው። ርግጥም መአሲ እያየሁት ወደ ኋላ መውደቅ ጀመረ። እሱም እንዳንዴ ሲበሳጭ እየደወለልኝ "ከእንሽርት ጋር ውዬ እንሽርት ሆንኩኝ" ይለኛል። እኔም ላጽናናው ስፈልግ "ፊሽ አንተ የሸንት ውሀ ከሆንክ አማ አለቃ ፀጋዬ ምን ሲሆን ነውና... በማለት እናገረዋለው።

22

ለነገሩ በሁለቱ የነወሐት ጓዶች መካከል ያለውን መገታተር ማወቄ ሳይጠቅመኝ አልቀረም። ያኛው የነገረኝን መረጃ ለዚህኛው ከነገርኩት፣ ይሔኛው የበለጠ አስፋፍቶ ይነግረኛል። በተለይ አተይን "ፍስሀ መአሲ ኤፈርትን በተመለከተ እንደዚህ ብሎ አሜውተኝ" ካልኩት በመቀደሙ በጣም ይናደዳል። ከምፈልገው በላይ የኤፈርትን ሚስጥር እየዘከዘከ ያወጋኛል። "እሱ ምን ያውቅና?፣ ...ይሄ ውሳኔ ሲወሰን መቼ ነበር?፣ ...ማን ሊነግረው ይችላል?" የሚሉ ንግግሮችን እንደመንደርደሪያ ይጠቀማል። ከፓርቲው መዋቅር በላይ የዘር ሀረጉን ይመዛል። የአጥንቱን ጥራት እየቆጠረ መመካቱን ያሳያል። እንዳየሁት ከሆነ በነወሐት አይን የአተይ አጥንት ከመአሲ ይወፍራል ...አድዋ እና አክሱም ተዳቅለውቢታል። የእኛ ዘመን የእውነተኛ ስልጣን መወጣጫ መሪ ቃል ደግሞ "የትም እደግ አድዋ (አክሱም) ተወለድ" ሆኗል።

ለትንሽ ደቂቃ ስቆዝም ከቆየሁ በኋላ፣

"በዛሬው ስልጠና መለስ ኤፈርት በከፍተኛ ኪሳራ ውስጥ መሆኑን በዝርዝር ማቅረቡ የተሻለ ግልጽነት እንዲፈጠር አድርጓል። አንዳንዶቻችን ድርጅቱ ያለበትን ደረጃ መረጃ ቢኖረንም ብዙሀኑ ካድሬ እስከዛሬዋ ቀን ድረስ ብሸቦታዎች ነበሩት"። ጓድ መለስ እውነትን ለመግለጥ የሚያደርገው ጥረት ያስደሰተኛል። ባለስልጣናት ጉዳዩን ከተባራሪ ወሬ ወጥተው በእስተውሎት እንደሚመለከቱት ይረዳል" በማለት ዋሸኩት። ርግጥም በውስጤ አቶ መለስ "ኤፈርት እየሞተ

ነው" ብሎ መዋሸቱ አበሳጭቶኛል። የሚስትር ግርማ ብሩ "ኤፈርት ኢኮኖሚውን እይቆጣጠርም። የግል ባለሀብቶችን ይደግፋል" ማለት የበለጠ አታጥሶኛል።

ከፊት የነበረውን ውስኪ በአንድ ትንፋሽ እየጨለጠ፤ አጠያየቁ ስላቅ የተሞላበት መሆኑ ገብቶኛል። አልቻለበትም አንጂ አንዳንድ ጊዜ እንደ ጮሌ መታየት ይፈልጋል።

"አንተ እንዴት ልታውቅ ቻልክ? ...አውነት ይመስልሀል? ...የአዲስ አበባን ህዝብ ካድሬ ማመን ቀብሮ ነው" በማለት ጠየቀኝ።

"እንግዲያውስ አዲስ አበቤዎች ህወሓት ሆነናል በለኝ!" በማለት ምላሽ ሠጠሁት።

ከመቅጽበት ፊቱ ሲለዋወጥ ቀለል አድርጌ፤

"የምሰራው እኮ ለህዝብ መረጃ ቅርብ የሆነው ኢህአዴግ ቢሮ ነው!... በዛ ላይ የእይይ ትግራይ እምብርት የሆነችው መቀሌ ከንቲባ የልብ ጓደኛዬ መሆኑን የዘነጋኸው መሠለኝ" አልኩት። ምላሹ ምን እንደሚሆን ስለማውቅ ነበር የፍሰሀ መአሲን ስም ያነሳሁበት። እሳተ አፍ እንደበቱ ወዲያው እንደሚከፈት አልተጠራጠርኩም። ራሴን በአተይና መአሲ መካከል ባለው ግንኙነት ሳስበው የእብድ ገላጋይ የሆንኩ አድርጌ አቆጥረዋለሁ።

አንዳሰብኩት ከአፌ ተቀብሎና ወደ መአሲ እየተመለከተ፤

"እሱ ስለ ትዕምት ምን የሚያውቀው ነገር አለ? ...ለምን የሌለበትን አንደ ነበረ አድርጎ ይዘለብዳል?" አለኝ። ትክ ብዬ ተመለከትኩት።የቀይ ዳማ ፊቱ ልውጥውጥ አለ። በሰጠሁት ምላሽ ቆሽቱው ብዙ ሀሞት ሲረጭ ታወቀኝ። የህወሓት ታጋዮችን ማበሳጨት የውስጣቸውን እንዲናገሩ አድል ይሰጣል።

"ተው እንጂ አተይ! እንዴት አያውቅም ትላለህ? ለምን የለበትም ትላለህ?... ቢያንስ የኤፈርት ጉዳይ በጉባኤና ማዕከላዊ ኮሚቴ ተነስቶ ውይይት ሲደረግበት ይመለከታል። ኤፈርት በመቀሌ ውስጥ ሊሰራባቸው የሚፈልገው የልማት ስራዎች የመአሲን ይሁንታ ሳያገኝ ሊፈፅም አይችልም" በማለት ምላሽ ሠጠሁት። ርግጥም ኤፈርትን በተመለከተ ከመአሲ ጋር ለበዙ ጊዜ እንስተን ተወያይተናል። ኤፈርት በሀገሪቱ የሚካሄዱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን እንደ ጆፌ አሞራ

ለመሰብሰብ የሚደረገው እንቅስቃሴ ለመእሲ ምቾት አይሰጠውም ነበር። ታጋይ እያለ ህወሓት ወደ አዲስ አበባ ሲገሰግስ በገባበት ከተማ ሁሉ የህዝቡን ንብረት እየኮረሰ ወደ ትግራይ ሲወስድና ህወሓት ሲወርስ ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆኑ በሶማም ይፀፅተዋል። ቡተሊይም ህወሓት የጎሻም አከባቢን ሲቆጣጠር የጣና በለስ ንብረት የሆኑትን የግብርና ማሽነሪዎች፣ ትራክተሮች፣ የጭነት መኪኖችና የሆስፒታል ቁሳቁሶች ጠራርጎ የህወሓት ንብረት ሲያደርጋቸው ቀጥተኛ ተሳታፊ መሆኑን ሲያስብ አንደ አበቬጋሬ ሀሊናውን ይኮሰኩሰዋል። መእሲ እንዳሚወተኝ ከሆነ ህወሓት ከጣና በለስ ፕሮጀክት በወቅቱ የወረሰው ንብረት ከ50 ሚሊዮን ብር በላይ ነው። ይሁን እንጂ በወቅቱ የጣና በለስ የወረዳ 2 የኢህአዴግ ካድሬ የነበረ ግለሰብ እንደገለጠው ህወሓት የወረሙው ንብረት መእሲ ከጠቀሙው እጥፍ በላይ ነው። የኤፈርት የግብርና መሳሪያዎች ከፊሎቹ ከጣና ፕሮጀክት የተመረሱ ናቸው።

24

አተይ ሽቅብ እየተመለከተኝና እያምቢተረ፣

"ከእኔ ይልቅ ለአሱ እንደምታደላ እውቃለሁ። ብዙ ጊዜ ቂጥ ለቂጥ ገጥማችሁ ሲታሴሩ አይቻለሁ።... ለጠየከኝ ጥያቄ ግን የትዕምትን እቅድ እና አፈጻፀም በጉባኤ እና የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ መገምገም ከቀረ ሠባት አመት አለፈው። እንጂዎቹ ከተባረሩ በኋላ የትዕምት የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ከትትል የሚደረገው በመለስ ብቻ ነው። መለስ በትዕምት የስራ እንቅስቃሴ ላይ የሚያጠፋው ሠአት በመንግስት ሀላፊነቱ ከሚያጠፋው ጋር እኩሌታ ነው። በዚህ አመት ብቻ ለተከታታይ ሁለት ሳምንታት ከትዕምት ስራ አስፈጻሚዎች እና ዴፊከተሮች ጋር የአምስት አመቱን አፈጻጸም ሲገመግም ነበር። የቀጣይ አምስት አመት ስትራቴጂክ እቅድ ሲያብራራ ነበር። መእሲ ስለዚህ ምን የሚያውቀው ነገር አለ?...ግምገማው ላይ መቼ ነበረ?...ማንስ ሊኮገረው ይችላል?..የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ለጦር መሳሪያ መግዣ መንግስት ሶስት ቢሊዮን ብር ከህወሓት (ኤፈርት) መበደሩን ዛሬ በግርማ ብሩ ከመነገሩ በፊት ያውቅ ነበር?...እስቲ በል ንገረኝ?" በማለት በጥያቄ አጣደፈኝ።

በአተይ ሀሳብ መስማማቴን እንዲያውቅ አንገቴን ከላይ ወደ ታች በመነቅነቅ አሳየሁት። ከመገረም ግን መውጣት አልቻሉም። ቀን ከነበረን የአቶ መለስ ማብራሪያ ተነስቼ በርካታ የህሊና ጥያቄዎች ከበቡኝ። ሠውየው ቀላል የማይባል ሠአቱን የሚያጠፋው ይህን የኢንዱስትሪና አገልግሎት ኢምፓየር በተጠናከረ መንገድ ለማስቀጠል የሚያስችለውን ስትራቴጂና ስልት ሲነድፍ ይከርማል። በተቃራኒው የሌላ ክልል ባለስልጣናት በኤፈርት ላይ ጥያቄ እንዳያነሱ "ንቃችሁ

ተዉት" በማለት ያጣጥላል። ርግጥ እቶ መለስ የኤፈርት የበላይ ጠባቂ በመሆኑ ሳድርጅቱ ትነሣ አንድሚሰጥ ምሚይዛድ ሀቅ ነው። ይህም በመሆኑ ከብንያው የሚያድግበትን ሁኔታ ቢከተ ምሚሸም ለይደለም። ከቶቱ ከለንደቡቱ የወጡት ቃላቶች በከሸት የተሞሉ መሆናቸው ላይ ከ ለኛም ለዛኝ ቅቤ ለንጓች አንድንሆንለት መፈለጉ ነው።

ይህም ተብሎ በየማደሪያው ባለሰልጣናት የሚያደርጉትን ከርከር በጥሞና ሉተከታ ሠው ድርጅቱ ስለ ኤፈርት ያስተላለፈው መልዕከት የተተረጎመው በተቃራኒው ነው። በአዳራሽ ውይይት በፍርሃት የተገዛው ሠው ቢጤውን በማደሪያ ሲያገኝ የልቡን ይተነፍሳል። አልፎ አልፎ በቡድን ውይይት ወቅት ፍርሀት በሠፈነበት ድባብ ውስጥ እየተሸማቀቀ ይናገራል። ሰር እየበደ ያለውን እድሎአዊነት እና የልማት ስርጭት መጪው ትውልድ ላይ የሚያሳርፈውን አደ ይገልጣል።

በነገራችን ላይ ባለስልጣናት እና ካድሬዎች ስንጨዋወት መናገር እና መጠየቅ ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት ዘዴ አላቸው። "ጥገኛው ሃይል እንዲህ እያሉ ያነሳሉ"..."ትምክህተኛ እና ጠባብ ቡድን እንዲህ እያለ ያወናብዳል"... "ኪራይ ሠብሳቢው የቀረችው መንጠልጠያ ያቺ ናት.." በማለት የራሳቸውን ስሜት ይተነፍሳሉ። ታዲያ አንዳንድ ከተማ ቀመስ ካድሬዎች ለብቻችን ስንጫወት "ጥገኛ ፣ ኪራይ ሠብሳቢ የሚሉት አብዮታዊ ቃላት ባይኖሩ ኖሮ ምን ይውጠን ነበር?" በማለት እንኑታገራለን። የቃላቶቹን ፈጣሪዎች አናወድሳለን። ምስጋና፣ ጥገኛ ኪራይ ሰብሳቢ፣ ጠባብ እና ትምክህት የሚሉትን አብዮታዊ ቃላት ለፈጠሩ!! ነብሳቸውን በአጸደ አብዮት ያውልልን።

እርግጥም የጥቅም ተገዢነት የበላይነት በያዘበት ሁኔታ ፍርሀት ቢኖር የሚያስገርም አይደለም። በላዩ ላይ ኢትዮጵያዊ ይሉኝታ ሲጨመርበት ደግሞ ፍርሀቱ እንዲፋፋ አድርጎታል። በዛ ላይ በፓርቲው ማዕከላዊ አሠራር መሠረት "ሠውየው!" እንደ አማልክት እና ጣኦት እንዲታይ መደረጉ የተለየ ሀሣብ እንዲራመድ አድል አይሠጥም። በዚህም ምክንያት በስርአት ውስጥ ኖረው እድጉን የሚብከነከኑ ሠዎች የቁጭት መልእክታቸውን የሚያስተላልፉት በዝምታ ነው። በተለይ ከህወሓት አባላት ውጭ ላሉ ካድሬዎች ዝምታ ወርቅ ነው። ከመናገር ደጅ አዝማችነት የሚቀረው ለህወሓት ባለስልጣናት ብቻ ነው። እነሱ የሚናገሩት አንዱ ብስል ሌላው ጥሬ መሆኑ እየታወቀ ጮክ ብሎ የመናገር ያልተገደበ መብት አላቸው። ሌሎቻችን ደግሞ "ጥገኛው...ትምክህተኛው...ኪራይ ሰብሳቢው" በሚላቸው ቀያይ ሴጣኖች እያሳበብን የልባችንን

እንተነፍሰለን። ነፍሳችንን ለማዳን እንዋኛለን። በርሜሉ መቀደዱን እያየን ውሃ ለመሙላት እንታተራለን።

26

ለምሳሌ በዛሬው ሰብሰባ ሚኒስትር ግርማ ብሩ ማብራሪያ ሲሰጡ፡ "ኤፈርት በመኖሩ ምክንያት ኢትዮጵያ በኢትዮ- ኤርትራ ጦርነት አሸናፊ ሆና እንድትወጣ ሆኗል። ኒዮሊብራሎች ብድር ለመስጠት ፍቃደኛ ባልሆኑበት እና ማዕቀብ ሊጥሉ ባሠፈሠጉበት ጊዜ ሶስት ቢሊዮን ብር ለኢትዮጵያ መንግስት ኤፈርት በማበደር ደማቅ ታሪክ ጽፏል" በማለት ሲናገር ነበር። ኤፈርት ያህል ፖንዘብ እንዳበደረ የኢደባባይ ሚስጥር ቢሆንም ኦፈጸጸሙ እንዴት ነበረ የሚለው ለባለሰልጣናቱ እንቆቅልሽ ነበር። ጦርነቱን የመሳሪያ ግዢውንና ኤፈርትን የሚመራው ህወሓት በሆነበት ሁኔታ "ህወሓት ለህወሓት" ያበደረው ብድር እንዴት ይታመናል?_ በኢትዮጵያ በኩል በተበዳሪነት ከተፈራረሙት ውስጥ ከትግራይ ተወላጆች ውጪ ሴላ በሌለበት እንዴት የኢትዮጵያ እዳ ይሆናል?...በምን ያህል ወለድ፣ በምን ያህል አመት ከፍያ ብድሩ ተፈጸመ_ የሚሉት ጥያቄዎች ምላሽ ባላገኙበት ጥያቄውን "የኪራይ ሰብሳቢዎች" አጅንዳ እድርጎ ማቅረቡ በራሱ አስገራሚ ነበር። እነሱ ለኢትዮጵያ አበዳሪ ሆነው መቅረባቸውም ብዙ ሰው አናዶታል። አቶ ስብሀት ነጋ መልሶ መላልሶ "መሶቦ በትግራይ ቢገነባም የኢትዮጵያ ሀብት ነው፣ አልመዳ የሚያመርተው ጨርቃጨርቅ የሀገር ምርት ነው" እያለ መናገሩ ካድሬው ለምን እንደሆነ ተረድቶታል። ኤፈርት ለኢትዮጵያ ህዝብ ሊደብቀው የማይችል አድገት ላይ በመሆኑ መካዱ አያዋጣም።

26

በምሽት ከበቡ ያለው ዳንስና ጭፈራ፣ መጠጡና ሁካታው እንደቀጠለ ነው። ከአተይ ታደለ ጋር የጀመርነው ኤፈርትን የተመለከተ ጨዋታ ቀጥሏል። የመአሲ ስም ባነሳሁለት ቁጥር እየተበሳጨ የሚጨልጠው አልኮል ወደ ሞቅታ ወስዶታል። የብሽቀት ሳቁም አላባራም። የፍትወት ፍላጎቱም እየጨመረ ሔዷል። የቡና ቤት ሴቶችን እጅ ከመያዝ መቀመጫቸውን መምታት ጀምሯል። ቅንዝር ባህሪው አገርሽቶበታል። ስርያ እንደፈለገ ጠቦት ፍየል የሴቶችን ዳሌ በእጁ ኪሎ እየመዘነ ያምቧቧል። ይባስ ብሎ ጡታቸውን ሳያስቡት ወደ መጨበጥ ተሸጋግሯል። እንደገመትኩት ሴቶች እኔንም ደርበው ከእግር እስከ ራስ ፀጉራችን በንቀት አይን ቁልቁል ይመለከቱናል። በጣም ሲያበዛው አደብ እንዲገዛ ደጋግሜ መከርኩት ሴሰኝነቱ እና መንቻካ ባህሪው በማሸነፉ ከድርጊቱ ሊቆጠብ አልቻለም። በተፈጥሮ ባለጌ የሆነን ሠው ከመምከር ቁንጫ መርገጥ ይቀላል።

የአተይን ነውረኛ ድርጊት በአይነ-ሀሊናዬ አየታዘብኩ ሁለት ሠአት ሆነ። ድሮ የማውቀው እና አብድ መስሎ ምሽት ከበቡ ጋር ተቀምጦ የነበረው ሠው ቀጠሮ የሠጠኝ ሰአት ደረሠ። ጊዜ ሳላጠፋ አተይ ወጣ ብዬ ከባለቤቴ ጋር ስልክ ላወራት እንደምፈልግ ነገኩት። ስልክ ላይ ብቆይበት እንኳን ሀሳብ እንዳይገባው ጨምሬ ገለፅኩለት። ወደ መጸዳጃ ቤት የምሔድ አስመስዬ ወደ ውጭ ወጣሁ። ዙሪያ ቅኝት አደደረኩ በጀርባ በኩል ወደሚገኘው መኝታ ቤት በፈጣን እርምጃ አመራሁ። አልቤርጎ ቁጥር ሰባት አጠገብ ስደርስ በሩን በቀስታ እንኳኳሁ።

መምጣቴን ሲጠባበቅ የነበረው ሰው ከመቅፅበት በሩን ከፈተ። ወደ ውስጥ እንድገባ ጋበዘኝ። እንጉቱን ብቻ ወደውጭ አውጥቶ አካባቢውን ተመለከተ። ተከትሎኝ የመጣ ሰው መኖርና አለመኖሩን ለማረጋገጥ እንዳደረገው ገመትኩ። ቀጠል አድርጎም የስልኩን ባትሪ አሳየኝ። እንተም ባትሪህን አውጣ ማለቱ ስለገባኝ በፊት ለፊት አውጥቼ አሳየሁት።

በሩን ከዘጋ በኋላ እየሳቀ፣

"በል ጓድ እንተዋወቅ። የዚህ ሁለት ወር ስሜ ሚደቅሳ ጫላ ይባላል። ከምስራቅ ሐረርጌ የመጣሁ አውቆ አበድ ነኝ!" አለና እጁን ዘረጋልኝ። ትከሻ ለትከሻ በመመታታት ሠላምታ ተለዋወጥን። ቅድም ካየሁት ተገላቢጦሽ ሆኗል። አፈር የመሰለ ፊቱ ተቀይሯል። ያማረበት ልጅ እግር ኮበሌ መስሏል። የሰውነቱ ወዝ የሚንጠባጠብ ይመስላል። የለበሰው የለሊት ልብስ ውበት በውድ ዋጋ የተገዛ መሆኑን ያሳብቃል። በአልቤርጎው የተጨሰው ከርቤ ቤቱን በጥሩ ማዕዛ አውዶታል። በድሬዳዋ እና ሀረ መኖሩ ተፅእኖ ሳያሳድርበት አልቀረም።

የመኝታ ቤቱን ዙሪያ እየተመለከትኩ፣

"መቼም ይሔ 665ኛው ሰምህ ሳይሆን አይቀርም! በዚህ መልኩ ከቀጠልክ ኢትዮጵያዊ ሰም አልቆ በቁጥር መጠራት ላይ ሳትደርስ አትቀርም" አልኩት። በደህንነት "ድርጅታዊ አሠራር" መሰረት አንድ የደህንነት አባል ቢያንስ በየስድስት ወሩ ስሙን መቀየር ይኖርበታል። በዚህም ምክንያት አብዛኛዎቹ የደህንነት አባላት "የመንደር ጎረምሶች" አይነት ባህሪ አላቸው። የሰብአዊ መብትን ማፈንና መርገጥ ዋነና ስራቸው እንደሆነ አድርገው ይወስዳሉ። ቅኝታቸውም እንደዛው ነው።

በድጋሚ እየሳቀ፣

"ምች ይቀራል ብለህ ነው? ዘመኑ ስምንተኛው ሺህ መሆኑን ዘነጋኸው መሠለኝ! ...እናንተ የኢህአዴግ ባለስልጣናት እንደልባችሁ ተኝታችሁ ማደር የቻላችሁት የእኛ እንደ ስፔስ 99 ማያ መቀያየር ስለቻልን ነው"በማለት ተናገረ።

28

አልጋው ጠርዝ ላይ እየተቀመጥኩ፣

"መቼም፣ ከዘመኑ ጋር እያያዝክ የምትናገረው መሬት ጠብ አይልም።... ለማንኛውም እውቆ አበድ የሚሆንበትን ልብስ የት እደረከው? ያደፈና ቀረንገሱ ልብስ ሲያምር ያየሁት በእንተ ላይ ብቻ ነው። በተለይ የራስታ ፀጉሩ አምሮብህ ነበር" አልኩት። በእጅቼ ሻንጣውን እያሳየኝ፣

"እናንተ ከመምጣታችሁ ሁለት ወር በፊት የቀን ቀን ልብሴ ሆኗል። አስቀድሜ የመጣሁት ህዝቡ እንዲለምደኝ ታስቦ ነው። አሁን ከሞላ ጎደል ለእዳማ ህዝብ ፀጉረ ልውጥ አይደለሁም። አንድ ሁለት ጊዜ በፖሊስ ከፍት መኪና የፈጥኝ አስረው ወደ እስር ቤት ሲወስዱኝ ህዝብ ተመልከቷል። ህዝቡ "ይሔን እብድ ምን አድርግ ነው የሚሉት?" እያሉ ሲናገሩ በጆሮዩ ሠምቻለው። የሚገርምህ በፖሊስ ጣቢያው አስርቤት ለተከታታይ ቀናት ታስሬ እንኳን ፖሊሶቹ እያውቁኝም ብሎ ሻንጣውን ከፍቶ እያሳየኝ፣ "ከወንጀል መከላከል ሀላፊው ውጪ የሚያውቀኝ ሠው የለም። የከተማው ፖሊስ አዛዥ እንኳን እንዲያውቀኝ አልተደረገም ..."

ከማለቱ አቋርጬው፣

"ወንጀል መከላከሉ እንዲያውቅህ ለምን ተፈለገ?" አልኩት። ከጠየኩት በኋላ መጠየቅ እንደሌለብኝ አስቤያለሁ። ግን ደግሞ ያልተመለሱልኝ በርካታ ጥያቄዎች አሉኝ። መጀመሪያ የተመለከተኝ ጊዜ እና አሁን ሲያወራኝ ስልኬን እንዳጠፋ፣ ባትሪውን ከስልኩ እንድለይ ማድረጉም ከመጠርጠር ውጪ ትክክለኛ እውነት አልገባኝም።

ትከ ብሎ እየተመለከተኝ፣

"ሁሉንም ሚስጥር ማወቅ አይጠበቅብህም። አንደሱ ከሆነማ እኛ ምን ስርተን እንበላ?... ለማንኛውም የአህዴድ ካባ የለበሰና አሮምኛ አቀላጥፎ የሚናገር የህወሓት ጓድ ነው። ከዚህ በፊት የመከላከያ መኮንን ነው። የመከላከያ የጦር መኮንኖች፣ የፖሊስ አዛዥ እንዲሆኑ በተወሰነው መሠረት የመጣ ነው" አለኝ። ውሳኔው ትዝ ብሎኝ አንገቴን በመነቅነቅ መስማማቴን አሳየሁት። ከምርጫ 97 በኋላ ከአቶ መለስ ውሳኔዎች አንዱ የህወሓት ታጋይ ከነበሩ የመከላከያ ሠራዊት

ውስጥ ተመርጦ ስልጠና በመስጠት የፖሊስ አዛውቾ አንዲሆኑ ነበር። አዲስ አበባን በመሰሉ ከተሞችና ከ/ከተሞች ሀላፊ አንዲሆኑ የታሰበ ነበር።

አስከትሎም፣

"ይልቁንስ በኦሮሚያ ክልል ተዟዙሬ አየሰራሁ የታዘብኩትን ልንገርህ። ህዝብ ከኢህአዴግ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኗል። አየሰራችሁት ያለው የፖለቲካ ስራ ለውጥ አላመጣም። እያደር ጥሬ ሆኗል። የፊጥኝ አያሰሩ ወደ አስርቤት ከሚወስዱኝ ፖሊሶች ጀምሮ ምሬትና የስርአት ለውጥ የሚፈልጉ ናቸው። እኔን እንደ አብድ ስለቆጠሩኝ የሚናገሩትን የምሰማ አይመስላቸውም። በተለይም በወረዳ እና ቀበሌ ካድሬ ሆነው የተመደቡት ከአህዴድ ላይ ፊታቸውን ካዞሩ ቆይተዋል። ህወሓት የኦሮሞን ንብረት እየዘረፈ ትግራይ ላይ ኢንንዱስትሪ፣ ፋብሪካ፣ ዩኒቨርሲቲ፣ ሆስፒታል እየገነባ ነው የሚል ቅሬታ አላቸው። የሚገርምህ ሆሮጉድሩ የሚገኝ የቀበሌ ካድሬ ጣቶቹን እየቆጠረ መሰባ፣ አልመጻ፣ መስፍን ኢንዱስትሪያል፣ ኢዛና፣ አዲስ መድሐኒት ፋብሪካ ይልህል...። ምስራቅ ሐረርጌ አወዳይ ከተማ ያለ ገበሬ ጉና፣ ትራንስ፣ ደሳለኝ እያለ ሲናገር ትሰማዋለህ። እዚህ አፍንጫችን ላይ ወለንጪቲ የሚገኝ የአንደኛ ደረጃ ር/መምህር ሜጋኔት፣ ዋልታ፣ ኤምአይቲ ፣ ቃላሚና የሚባሉ ተቋማትን እየጠራ ሲከራከር ታደምጣለህ" አለኝ ።

አፈን ከፍቼ አዳምጠው ጀመር። ሚደቅሳ ማቆም አልፈለገም።

አንዲህ በማለት ንግግሩን ቀጠለ፣

"በተለይ በኤፈርት ቁጥጥር ስር ያሉ ኢንዱስትሪዎች፣ ፋብሪካዎች፣ ሚካናይዝድ እርሻዎች፣ የማዕድን ቁፋሮዎች፣ የትራንስፖርት አገልግሎቶች፣ የፋይናንስ ተቋማት...ወዘተ ህዝቡ በቁጥር አያነሳ ጠይቆናል። ከትናንሽ እስከ ሜጋ የመሠረተ ልማትና ፕሮጀክቶችን የፋቀራመተው ኤፈርት አንደሆነ በመረጃ ተደግፎ ሞግቶናል። ይህ ኢ-ፍትሐዊ የሆነ ለውጥ የህዝቡ ተቃውሞ እና ምሬት በከፍተኛ ሁኔታ አንዲጨምር አድርጓል። ከኢትዮጵያ ህዝብ ከተቀማ ገንዘብና ንብረት የተቋቋሙት እነዚህ ኩባንያዎች በቅርብ ጊዜ የጥቃት ኢላማ መሆናቸው አይቀርም። ይህ ሊመጣ እንደሚችል ለእለቆቻችን ነግረናቸዋል...። ብዙ ኢትዮጵያዊያን በትግራይ የብቻ ጉዞ ላይ ደስተኛ አይደሉም። ይሔ ደግሞ በመረጃ እና ማስረጃ ላይ የተደገፈ ነው።... በኢትዮጵያ ትልቁ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣ በኢትዮጵያ ትልቁ የሲምንቶ ፋብሪካ፣ በኢትዮጵያ የትምህርት እንቅስቃሴና ማዕከል፣ በኢትዮጵያ የእስከሬን ምርመራ በዘመናዊ ቴክኖሊጂ የሚያደርግ ብቸኛ

ሆሰፒታል በትግራይ ተቋቁሚል።... አርግጠኛ ነኝ አሜሪካን ሀገር ከሚገኘው ማሳቹሴቴስ ኢንቲቲዩት አፍ ቴክኖሎጂ ልምድ በመውሰድ የተቋቋመውን የመቀሌ ኢንስቲትዩት አፍ ቴክኖሊጂ (MIT) መቀሌ የሐይቲክ ጊዜ ጎብኝተሽዋል። በኢትዮጵያ ምድር እንደዛ አይነት ዩኒቨርሲቲ በጣሸ ክፍለዘመን የሚታሠብ አይደለም።...ከዘመናዊነት የተነሳ ወጪው ከፍተኛ በመሆኑ ምክንያት ማሰተዳደሩ ከኤፈርትና ትልማ ተነስቶ ለትምህርት ሚኒስቴር እንዲሠጥ የውሳኔ ሀሣብ ቀርቧል። ...እንግዲህ ይታይህ በጀት የሚመድበው ትምህርት ሚኒስቴር፣ የሚማሩት ግን የትግራይ ወጣቶች! ...ምን ማለት ነው?"

ሚደቅሳ በጥሞና እያዳማጥኩት መሆኑን ሲገነዘብ በውስጡ የቋጠረውን ቅሬታ መዘርገፉን ቀጠለ፦

"የትግራይ ህዝብ የኢትዮጵያ ህዝብ እንደመሆኑ መጠን ቢለማ የሚጠላ የለም። ሌላው ህዝብ የሚያነሳውም ሆነ በጋዜጣና በመጽሔቶች የሚቀርቡ መጣጥፎች በትግራይ ይህን ያህል ፕሮጀክቶች በመከፈታቸውና በመቶሺዎች ቋሚ የስራ እድል በመፈጠሩ ምክንያት የመጣ ቅሬታ አይደለም። ህዝቡም ሆነ መጣጥፎቹ እየገለጡ ያሉት አኩል እንደግ፣ ፍትሐዊ ልማት ይምጣ፣ በክልሎች መካከል የተመጣጠነ እደገት ይኖራል ብላችሁ የለፈለፋችሁትን በተግባር ላይ አውሉ የሚል ነው። ህዝቡን 'ኤፈርት በጎ አድራጎት ድርጅት ነው፣ የህወሐት ቢዝነስ ኢምፓየር አይደለም ብለህ የምትሸወድበት ዘመን አልፏል። የኤፈርትን ኩባንያዎች፣ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ካፒታሎች፣ በመላው ሀገሪቱ እና በውጭ ሀገር ያሉትን ኢንቨስትመንቶች እና ቢሮዎች በማየት ብቻ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በቁጥር አንድ የተቆታጠረ መሆኑን ትመለከታለህ።...እንደው ግን የኢትዮጵያን ህዝብ በመድረክ አግኝቷችሁ ይህንን ጥያቄ ቢጠይቅ ምላሻችሁ ምንድነው?" በማለት ከባድ ጥያቄ ጠየቀኝ።

ለሚደቅሳ ድጋፍ ለመስጠት ብዬ፣

"ማይክ! ...የኤፈርት ጉዞ በጣም አስደንጋጭ ሆኗል። ህወሓት የፖለቲካ የበላይነትን ለማምጣት የኢኮኖሚ የበላይነት መረጋገጥ ይኖርብርታል ብሎ የቀየሰውን ስትራቴጂ እያሰፈጸመ ያለው በኤፈርት አማካኝነት ነው።...ከሁለት ወር በፊት የትዕምት ማርኬቲንግ ሀላፊው የእመት አቅድ ሲሠራ እንዳግዘው ስለጠየቀኝ ቢሮው እመላለስ ነበር። የትዕምትን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት፣ ካፒታሉን፣ የገባበት የኢኮኖሚ ዘርፍ ስመለከት በጣም ደነገጥኩኝ። በሌላ በኩል ተናደድኩኝ። ብአዴን፣ አህዴድ እና ደኢህዴን ምን እየሰሩ እንደሆነ ግራ ገባኝ" አልኩት።

አስከትዬም በእጇ ያለውን መረጃ አካፈልኩት።

አተይ የጉና ማርኬቲንግ ዲፓርትመንት አመታዊ አቅድ አውጥቶ አቶ መለሰ ጋር ከመላኩ በፊት እንዳግዘው ይጠይቀኝ ነበር። ቢያጋስ መሠረታዊ የአቅድ አሠራርን (አላማ፣ ግብ፣ የሽያጭ መጠን ትንቢያ፣ ስምሪት፣ ሊደጋገሙ የሚችሉ ችግሮች.. ወዘተ) መሞላታቸውን አረጋግጥለታለሁ። በዚህ ኢንባሚ ለአቅዱ መነሻ እንዲሆን አፈርት ባለታላይ እና ጉና በተናጥል ያሰየውን አመታዊ አድገት በዝርዝር እንመለከታለን። እንዳንድ ጊዜ አተይን መርዳት አስኪያቅተኝ ድረስ እናደዳለሁ። በሴላ በኩል ልቀባጨረው የማልችለው ቁሞት ያድርብኛል።

በትግራይ ክልል የሚንቀሳቀሱት አፈርትና በስሩ ያሉት ኩባንያዎች በሊንዴስትሪ፣ በማዕድን፣ በእንልግሎት፣ በአርሻ ሚከናይዜሽን፣ በትራንስፖርትና ኮሚኒኬሽን፣ ባንክና ኢንሹራንስ፣ ኮንስትራክሽን... ወዘተ የሊንቨስትመንት ካፒታላቸው ተደምሮ ሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች ተብለው የተደራጁት በጋራ ሆነው ቢደሙ መሳ ለመሳ ይሆናሉ። ከትግራይ ሊንቨስትመንት የአንድ ሠው የንብስ ወከፍ ድርሻ አዲስ አበባን ሳይጨምር የሁሉም ቢደመር ሁለት እጥፍ ይሆናል።

(ወደ ኋላ ሔዶ ዝርዝር ጉናት መስራት የፈለን መንግስታዊ ጋዜጣ የሆነውና በፐሬስ ድርጅት የሚታተመውን የአንግሊዘኛ ጀሬዲድ ጋዜጣ ናስምባር 28/96 የወጣውን መመልከት ይቻላል። ጀሬዲድ ጋዜጣ ያቀረበው የኢትዮጵያ የሊንቨስትመንት ባለስልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ ሊፓርላማ ያቀረቡትን ሪፖርት ቃል በቃል ለስተምጣቷል። በሊንቨስትመንት ባለስልጣኑ እንደተገለጠው የትግራይ ሊንቨስትመንት የእንድ ሠው የንፍስ ወከፍ ድርሻ ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ነፍስ ወከፍ ድርሻ ሲሠላ 60% ይሆናል። የአርሚያ ክልል የንፍስ ወከፍ ድርሻ ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሊንቨስትመንት ነፍስ ወከፍ ድርሻ ሲሠላ 5% (አምስት ፐርሰንት)፣ የአማራ ክልል 1% (አንድ ፐርሰንት)፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች 2% (ሁለት ፐርሰንት) ያህል ነው። ከፍተኛ የህዝብ ከምችትና የተረባሮ ሀብት ያለው የደቡብ ኢትዮጵያ የታየው የሊንቨስትመንት መጠን መቅኒ እና አሮቃ ላይ የተተከሉት መሳብ ሲሚንቶ፣ ለልማዳ ጨርቃጨርቅና መነፍን ሊንቨነሪንግ ላይ የተደረገው ሊንቨስትመንት ብቻ ተደምሮ የደቡብን ይበልጣል።)

ከአተይ ጋር የአፈርትን አድገት ወደኃላ ሔደን ስንመረምር ያሳቱት ከብርቦን የፈጠነ አድገርት በአለም ደረጃ የማሬያ ድርጅት ካልሆነ በስተቀር ሊታሰብ የሚችል አይደለም። በተለይ አልመዳ ጨርቃጨርቅ፣ መሶቦ ሲሚንቶ ፋብሪካ፣ መኪናን ሊገጅነሪንግ፣ አሥና ወርቅ ማዕድንና አምበረድ፣ ሰር ኮንስትራክሽን፣ ጉና ኮርፖሬሽንና ሂደምት አርሻ ሚካናይዜሽን ያሳቱት የካፒታል አድገት ትዕምት ምን ያህል የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሀብቶች እንደተቆጣጠረ የሚያመላክት ነው።

ጉና ኮርፖሬሽን የህወሓት ታጋዮች በሆኑት ማርግይ ንመድህን፣ ግደይ ንመድህን፣ ህፍር ገ/ኪዳን፣ ሠሳሞን ገህደውት፣ ሙሉ ሀንስና ፀጋዜ ጣዕም ያለው የተቋቋመ ነው። እያንዳንዳቸው ዋሬ ፕንዙብ 500ሺህ ብር እና በቁሳቁስ ብ ሚሊዮን ብር (በድምሩ ፴ ሚሊዮን ብር) የተቋቋመው ጉና በ600 እተኖ አድጓል። በመላ ሀገሪቱ አዲስ አበባ እና ከጋኃ በላይ ቅርንጫፍ ጽቢቶች ከናቷል። ከ፴ሺህ የማያንሱ የቸርቻር ሱቆች ከናቷል።

ሌላም የሚገርም ነገር አለ።

በአስራ ሠባት ቁምጣ አዲስ አበባ የረገጡት ታጋዮች ጉና ትሬዲንግን ለማቋቋም በቁሳቁስ ያሰያዙት ወደ ፭ሚሊዮን ብር አካባቢ ነው። እያንዳንዳቸው በአማካይ አንድ ሚሊዮን ብር የሚጠጋ ቁሳቁስ (In kind) አሰይዘዋል። የብር ቁሰም አይቶ ያማያውት አንኳን ቢሆን አንድ ብር ይሁን አስር፣ ...አስር ይሁን ሀምሳ፣ ...ሀምሳ ይሁን ሙቶ፣ መለየት የማይችል የሜክ ሠራዊት በተሬ ንገዘብ 3 ሚሊዮን፣ በቁሳቁስ 8 ሚሊዮን ብር አዋጥቶ ጉና ትሬዲንግ መሠረተ ማስት በራሱ አስቂኝ ነው። ህሊና ላለው ሠው ያናድዳል። እየሠሙ እና እየተመለከቱ ከመናደድ አለማውቅን የመሠስ ነገር የለም።

በተመሳሳይ መልኩ ሚጋ ኮርፖሬሽን የህወሓት የበረሃ ታጋዮች የሆኑት ብርሃኔ ገ/ጻዲቅ፣ ብርሃኔ ረዳ፣ ኪሮስ ምሩጽ፣ ሀይለ ገ/ሚካኤል እና መብርሐቱ ከበደ የተቋቋመ ነው። እነዚህ ታጋዮች በተሬ ንንዘብ እያንዳንዳቸው 200ሺህ ብር እና በቁሳቁስ (In kind) 600ሺህ ብር (በድምሩ 4ሚሊዮን ብር) የተመሰረተ ሲሆን በሁለት አስርተ አመታት እንቅስቃሴው በ500 እተኖ (2በሊዮን ብር) አድገት አሳይቷል። እንደ ጉና ሁሉ የሚጋ ባለቤት የተመዘገበሳቸው ሀብት ከበረሃ ተሸከመው የመጡት አይደለም። የመንግስት ንብረት የሆኑትን እንደ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት በሞተ ዋጋ በመግዛትና ሠራተኞችን አባረው የህወሓት አባላትን በመተካት የተፈፀመ ነው። ታጋሮ በተሠጣ ሙታንታ የምትቀናው የአቶ መለስ ባለቤት (በሚጋ ፈረስ ስሚ "ያምለም መስፍን")

ይሆንን ድርጅት ቀድሞ ከነበረበት በሦስት ሙዶ አጥፍ ማሳደግ መቻሏ የከርሰሓታዊ አመራር ችሎታዋን የሚያመላክት ነው።

የጦና ኮርፖሬሽን የነበያ አቅድ ከአተያ ጋር ለመሰራት በተንቀሳቀስኩኝ ወቅት የነበሙዎቹን ዩትዕምት ኩባንያዎች ለጀማመር እና እድገት ለማየት ችያለሁ። ከእነዚህ ውስጥ በሦስተኛ ደረጃ ትኩረቴን የሰበው በአርከበ አቁባይ የሚመራው መስፍን ኢንዱስትሪያል ኢንጂነሪንግ ያሳየው እድገት ነው። በትዕምት፣ ሀይወት ግብርና ሜካናይዜሽን፣ በሱር ኮንስትራክሽን፣ ትራንስ ኢትዮጵያ እና አርከበ አቁባይ የአክሰዮን ባለቢትነት የተጀጀመው መስፍን ኢንዱስትሪያል መነሻ ካፒታሉ ነዐሚሊዮን ብር ብቻ ነበር። በቡምስላጉ አርከበ አቁባይ አብዮታዊ አመራር ወደፊት የተሰፈነጠረው መስፍን ኢንጅነሪንግ የካፒታል መጠኑን በ500 እጥፍ አሳድጎ 6ቢሊዮን ብር አድርሶታል። ይሔ ማለት በሌላ አኳኋር መስፍን ኢንጂነሪንግ በአመት በአማካይ 300 ሚሊዮን ብር አዲስ ካፒታል ይጨምራል። ርግጥም ፋብሪካው እና የሽያጭ ቢታው በመቀሌ እና ታሲቲ አንዲሁም ዱከም ያደረገው መስፍን ኢንዱስትሪያል ወዲ አቁባይ እየተመራ እንደ አቦሸማኔ ባይሮጥ አጠያያቂ ይሆን ነበር። አርከበ አንድ ሠሞን ታሲቲና ዱከም መመላለስ ሲያበዛ ከአልጋ መውደቅ ባሻገር ሌላ ተልዕኮ እንደነበረው እምነት ነበረን። ነብሱን ይማረውና የዱከም ከንቲባ የነበረው ሚደቅሳ በምግብ ተመርዞ የሞተ ሰሞን ከአርከበ ጋር በየካ እና ዱከም መሬት ጭቅጭቅ ገጥሞ ስለነበር እምነታችንን ያጠናከርልናል። አርከበ በማስተር ፕላኑና የኢንዱስትሪ ዞን ስም በአዲስ አበባ ዙሪያ ያሉ የኦሮሚያ ከተሞችን ለመቆጣጠር ጥረት ከማድረጉ በፊት በተበጣጠሙ መንገድ ለሀሙሉት ብሎም ለትዕምት ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ መሬት "በመንግስታዊ ወረራ" መልኩ ይቀማ ነበር።

ለማንኛውም ለንፅፅር እንዲመች የተወሰኑት የኤፈርት ኩባንያዎች በሁሉት አስርተ አመታት ያሳዩትን መመንጠቅ በኩባንያ ሰም፣ በመነሻ ካፒታል፣ አሁን በደረሠበት ካፒታልና በሰንት እጥፍ እንዳደገ በሠንጠረዥ ወደ መመልከት እንሸጋገር። ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ትዕምት ካሉት ከ90 በላይ ፋብሪካዎች፣ ድርጅቶች፣ የንግድ ተቋማት፣ የፋይናንስና ኢንቨራንስ ውስጥ አሰራ ሁለት ብቻ ለናሙና ቀርበዋል።

ትዕምት ካሉት ከ90 በላይ ፋብሪካዎች፣ ድርጅቶች፣
የንግድ ተቋማት፣ የፋይናንስና ኢንቨራንስ ውስጥ አሰራ ሁለቱ

ተ.ቁ	የኩባንያው ስም	መነሻ ካፒታል (ብር)	የተደረሰበት ካፒታል (ብር)	በሰንት እጥፍ አደገ	ምርመራ
1	አልማላ ጨርቃጨርቅ	180 ሚሊዮን	8 ቢሊዮን	44 እጥፍ	3 ቅብረከ
2	መስፍን ኢንጂነሪንግ	10 ሚሊዮን	6 ቢሊዮን	500 እጥፍ	3 ቅብረከ
3	መሰቦ ሲሚንቶ	340 ሚሊዮን	8 ቢሊዮን	23 እጥፍ	2 ቅብረከ
4	ጦና ኮርፖሬት	10 ሚሊዮን	6 ቢሊዮን	600 እጥፍ	25ቅርንጫፍ ጽቢት፣ ወጪህ ችርቻሮ ሱቅ
5	ሚጋ ንቭ ኮርፖሬት	4 ሚሊዮን	2 ቢሊዮን	500 እጥፍ	4 ኢንቨርተሬ ደንብ እና ኢጀንሲ
6	ሱር ኮንስትራክሽን	100 ሚሊዮን	5 ቢሊዮን	50 እጥፍ	
7	ትራንስ ኢትዮጵያ	100 ሚሊዮን	3 ቢሊዮን	30 እጥፍ	
8	ሀይወት ግብናደልሽን	25 ሚሊዮን	1 ቢሊዮን	40 እጥፍ	
9	ኢዛና፣ መደባይ-ታዮር ወርቅ ማዕድን፣ ፀንበላ መይዲ ወርቅ ማዕድን፣ ሳቡ እምነበረድ	89 ሚሊዮን	4 ቢሊዮን	45 እጥፍ	4 ቅብረከ
10	ብሩክ ኬሚካል	20 ሚሊዮን	6 ቢሊዮን	300 እጥፍ	
11	ደደቢት ባንክ	20 ሚሊዮን	8 ቢሊዮን	400 እጥፍ	
12	ድምር	798 ሚሊዮን	57 ቢሊዮን	72 እጥፍ	

ሰንጠረዥ ቁጥር ፤ ለናሙና የቀረቡ የትዕምት ኩባንያዎች እና አድጎታቸው

በሥንጠረዥ ቁጥር ፣ እንደሚታየው ትዕምት ካሉት አሏላፍ የኢንዱስትሪ፣ ማዕድንና ኮን
ኮንስትራክሽን፣ ትራንስፖርት፣ ባንክና ፋይናንስ፣ ኢንሹራንስና አገልግሎት ዘርፉ ውስ
አንፀባራቂነን ብቻ መዝን ብንመለከት መነሻ ካፒታላቸው 798 ሚሊዮን አካባቢ ነ
ከተመሠረቱ ሁለት አስርተ አመታት በኋላ ካፒታላቸው በ72 ያህል እጥፍ በማደግ ወደ ገ
ቢሊዮን ብር እንዲጠጋደግ አድርጎዋል። ይሔ ማለት በሌላ አነጋገር እነዚህ 12 ኪባንያዎች ገ
በአመት በአማካይ ካፒታላቸው ከመነሻው ጋር ሲነፃፀር በ3 ቢሊዮን ብር አያደገ ይሔዳሉ
በተለይም እንደ ንና እና ሚጋኔት ኮርፖሬት አይነት በንግድና አገልግሎት ዘርፍ የተሰማ
ድርጅቶች ያሳዩት እድገት በ600 እና 500 እጥፍ ያህል ነው። ለሁሉም ግልፅ ሆኖ እንደሚታ
ንና መንግስታዊ የንበረውን የአገር ውስጥ ሸቀጦች ማከፋፈያ ድርጅት (ኢ.ፋ.ዲ.ሲ) ሙሉ በሙ
እንዲተካ በመደረጉ በመላው ኢትዮጵያ በቀላሉ መዋቅሩን በመዘርጋት ከ100ሺህ በላይ የቸርቻ
ሰቆቸን እንዲመሠርት አድርጓል።

እንግዲህ የህወሓት ኩባንያዎች በተለይም ትዕምት ውስጥ ያሉ ኮርፖሬት ድርጅቶ
ሲመሠረቱ የነበረቸው እና አሁን ያደረሱበት ካፒታል ቢነፃፀር ምን አይነት አስደንጋጭ (አስገራ
ውጤት እንደሚገኝ መገመት ይቻላል። ከላይ በሰንጠረዡ ያልተካተቱት አብዛኛው እንዳንተ
ፋይናንስና ባንክ ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው የሚኖራቸው እድገት በሠንጠረዡ ላይ ከተካተ
ያናልበትም እጥፍ ይሆናል። ከኢንዱስትሪ በተቃራኒ አገልግሎት ሠጪ ኩባንያዎች ቋሚ
ወጪያቸው (Fixed cost) እጅግ በጣም አነስተኛ እንደሆነ ይታወቃል። ባንክና ኢሸራን
አስመጪና ላኪ፣ አስጥቦ ትራንዚት አገልግሎት፣ የኮንሰሊታንሲ አገልግሎት፣ የሚዲያ
ኢንፎርሜሽን ሠርቪስ፣ የትራንስፖርትና አስጎብኚ ድርጅት ያላቸው ወጪ ከኢንዱስትሪ አና
ፋብሪካ ያነሰ ነው።

ትዕምትን ከማቋቋሪያ አንባር አቶ መለስ ባለቤቱን የድርጅቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ ካደረገ በኋ
የወሰደው እርምጃ ሌላኛውን የእድገት ምዕራፍ የሚረዝንት ነው። ይህ እጣፋፊ እርምጃ
የተወሰደው በመጋቢት 2001 ዓ.ም. ሲሆን እስከ 50 ቢሊዮን ብር ቋሚና ተንቀሳቃሽ ካፒታ
አንዳለው የተገለጠውን ኮርፖሬት (ደጀና ኢንዶውመንት) ከኤፈርት ጋር ማቀራረ ነበር።
ከኤፈርት ጋር የተቀላቀለው ደጀና ኢንዶውመንት ስድስት ትላልቅ ኩባንያዎችን የሚያንቀሳቅ
ነበር። እነዚህም ብሩህ ተስፋ ፕላስቲክ ፋብሪካ፣ ማይጨው ፓርቲክልስ ቦርድ፣ ናሽናል ጀ

ቴክስታይል ፋብሪካ፣ አበርገል የእንጥት ማደለቢያና ኤክስፖርት፣ አላጌ የደን ልማት፣ ሲሚ የማርና ውጤቶች ፋብሪካ ናቸው።

እንግዲህ ትዕምት እና የትግራይ ልማት ማህበር (ማህበረ ረድኤት ትግራይ) ንብረት የሆነው ደጀና ኢንዶውመንት ሲቶሳቀሱ የሚደጥሩት ሲነርጂ ሀወሓት የተሰሙውን ግብ በፍጥነት ለማሳካት ያስቸለዋል። ትዕምትም ሆነ ትልማ የጋራ አላማና ግባቸው የኢኮኖሚ የበላይነትን በማምጣት የፖለቲካ የበላይነትን መረጋገጥ በመሆኑ መዋህዳቸው የተቅም ግጭት የሚያመጣ አይደለም። ትዕምትም ሆነ ደጀና ኢንዶውመንት ለአንድ አላማ መነሳት የተቋቋሙ እንደመሆናቸው መጠን በተናጠል እደረሽጀትና አመራር መመራታቸው ትርፉ ብክነት መሆኑ አይቀርም። በየግላቸው ከሚያመጡት ኢኮኖሚ ትልቅ ከመሆኑ ባልተናነሰ ጠንካራ ድርጅት ለመፍጠር ያስችላቸዋል።

•••

በአልቢርነ ቁጥር ሰባት ውስጥ ከሚደቅሳ ጋር የምንጫወተው አለለቀም። ሚደቅሳ ስለ አፈርት ሲያወራ ስልጠና ውስጥ ያለ ይመስል ንበር። ወጋቸንን ለማስቀጠል ፈልጌ፡

"ይገርምህል! የዛሬ የመሰስ ገለጻ ያተኮረው አሁን እጉቱ በጠየኸኝ ኢንዶውመንቶች ላይ ነው። እንደ መለስ እምነት ከሆነ ከላይ የጠቀስከቸው ድርጅቶች በከፍተኛ ኪሳራ ላይ ሰሚገኙ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተፈጥሮአዊ ሞታቸውን ይሞታሉ' አልከት። እንድ የማለውቀው ሀይል እንዳምነው አድርነኛል። ደግሞም እየነገርከት ያለሁት በእደባባይ ተነግሯል። በቪዲዮ የቀረጸ ነው።

በድጋሚ አጨንቁር እየተመለከተኝ፡

"የስብሰባው አዳራሽ ውስጥ ነበርኩ። ሠውየው ገለጻ ሲሠጥ በማማሽ ልብ ተከታትየዋለሁ። አቦይ ስብሀት "በትግራይ ያለው ልማት በሙሉ የኢትዮጵያ ልማት ነው' አያለ ሲናገር እደምሚለሁ። እጠንቢ የነበረው አባዳለ እንተን በአምነታ ይነቀንቅ ነበር። ሌላኛው ልቢ እንድ በአነግ የሚጠረጠር የነግ አስተዳዳሪ ቢኪታተል ነበር። እስከአሁን እነማነቱ ላይ ምንም ሳንኝበት አልቻልኩም። ለማንኛውም ግን መሬት ላይ የሚንቀሳቀሰውን እውነታ ማዳምጥ የሚያስፈልግ ይመስለኛል። በኦሮሚያ ውስጥ በትንሽ ሰው የምትሰኮስ አሳት መብረጃ አይኖራትም። በወረዳ እና

ተበሌ የሚገኙት በመቶ ሺህ የሚጠጉት ካድሬዎች አውፍሰፈው እየጠበቁ ያሉት የለውጥ ከብሪት የሚለኩሰላቸውን ሠው ነው" ለለኝ ፊቱን እጪግደ።

"ሚደቅሳ፣ አናንተን የመሰለ ቸን ከሴት ደህንነታችንን የሚጠብት ታታሪ አያለ ምን እንሆናለን፣ ፀረ አብዮቱን እየመነጠራችሁ፣ ..እያባረራችሁ፣ ..እያሠራችሁ ..ምን ከፉ ነገር ይመጣብናል? ..የህዝብ ኑር እየበተናችሁ፣ ጎጅ እያፈረሳችሁ ቢቱን "ውሪድ በሌ" አድርጋችሁት የለ?" በማለት ጠየኩት። ፊቱን ሳያዞረታ እንዲህ መለሰ፣

"እይምስልህ! በደል የተጫነበት እና የተቆጣን ህዝብ አደብ ማስገዛት በጣም ከባድ ነው። በደህንነት፣ በስለላ፣ በሰራዊትና እጋዚ ልዩ ኮንዶ ተማምነህ የህዝብን ጉልበት መናቅን የመሰለ ስህተት የለም። የህዝብ ፍርሃት እንድ ጊዜ ከተሰበረ መመለሻ የለውም። በሽብርም ቢሆን መብቱን ለማስከበር ወደኋላ አይልም። ህዝቡ ቁፍድዶ ከያዘው የፍራቻ ቆፈን እየወጣ መሆኑን የሚያሳዩ ግልፅ ምልክቶች አሉ። በዛ ላይ በመረሸ እየተደገፈ ሔዷል። ወንድሜ፣ ዛሬ ትሳንት አይደለም... ህዝቡ እየተማረ ነው... በዛ ላይ በደህንነት መዋቅሩና ሠራዊቱ ውስጥ ያለው የአርስ በራስ መናናቅና የጥላቻ ህመም የሚድን እንዳይመስልህ። እንዳች መንሸራተት ቢመጣ ለእልቂት እና ዘረፋ ቅድሚያ የሚሰጠፈው እሱ ነው" በማለት ተናገረ።

እስከትሰማ፣

ማስተወሻ ደብተር ከደረቱ ውስጥ አወጥቶ "ከፈረሱ አፍ" የሚል ቃል ከተባ። እንግሊዘኛውን እንድፅፍለት ትንሿን ማሰታወሻ አቀበለኝ። "From the Horse Mouth" በማለት አስከ አትተርጉሙ ደፍኩለት። በደስታ ብዛት ብርሞቶዩን በደረቅ ውስኪ ሞላው። ጨዋታችንም በዛው ልክ ሞቅ አለ።

አተይ ማሰታወሻ ደብተሩን ትኩር ብሎ ከተመለከተ በኋላ፣

"እንደውም አንድ ነገር ኢጠይቅህለው ብዬ አሁን ትዝ አለኝ። በቡድን ውይይት ሠኔት ያ፣ ጀትዮቱ የአዲስ አበባ ካድሬ መስፍን መንግስቱ የሆነ በእንግሊዘኛ የተጻፈ መፅሀፍ እያነባበጠ "የእንዳራዊነት ቲዎሪ" አያለ የሚናገረው ምንድነው?... አልበርት ምናምን ያለው የቲዎሪው ደራሲ ከማርክስና ሌኒን ጋር ሊመጻደር ይችላል?... መቼም አልበርት አብዮታዊ ዲሞክራት መሆን አለበት_ መሰፍኔ ደግሞ ደጋግሞ ዴሞክራሲ በአንጻራዊ ቲዎሪ መታየት አለበት ያለው የአልበርትን አብዮታዊ ዲሞክራትነት አረጋግጦ መሆን አለበት። አንተም በአሱ ላይ ተጨማሪ ያደረከው ተንጣራችሁ ድርጅታዊ አጻም ውስጣችሁ መሆን አለበት" በማለት ጠየቀኝ።

ገልጦ የሚያሳየኝን የደረት ኪስ ማስታወሻ እየተመለከትኩ፣ "ወዲ ታደለ፣ _ሠውየው በአለም ከሚታወቁ ሳይንቲስቶች በቁጥር አንድ የሚጠቀስ ነው። አልበርት አንስታይን ይባላል። በተለይም በአንጻራዊነት ሐልዩት_ (ሪላቲቪቲ ቲዎሪ) _ለአለም ያካበተው የምርምር ውጤት ገና ተጠንቶ አላለቀም። _"ከግለቱ አጽርጠኝ፣

"ፈጠንከብኝ። ሠውየውን መጀመሪያ ልጻፈው። _ሐልበርት አንስታይን፣ _አሁን አንጻራዊነት (ሪሊርቲቪቲ) የሚባለውን ትርጉም ንገረኝ" በማለት ጠየቀኝ። በመቀስ የተከረከሙ የሚመስሉ ጻፊጻም እጅች ለመጻፍ የጽመጡ መሠሉ።

እንዴት ብቡ በሚገባው መንገድ እንደማስረዳው ግራ ገባኝ የአንጻራዊነት ታዎሪ ማብራትና የለተይ ሞንቅላቶን ሮሚያዋድድ ምሳሌ ማምጣት አቅተኝ። ከውልደቱና እስተዳደጉ ጋር ሚመሣን ማብራሪያ ማሠላሠል ጀመርኩ። የህወሓት ባለስላጣን ታጋሮች የሚበልጣቸውን ማህበረሰብ በከፍተኛ ደረጃ የመለቱል ስሜት አለቸው። ሀሊናቸው በሚረብሽ የተቢቱይነት ስሜት የተሞላ ነው። በዚህ ምክንያት ሥዎች እርስ በራስ እንዲጋጩ በማድረግ ፍላጎታቸውን ለማሞላ ተረት ያደርጋሉ። ህወሓት ሲታገድጋቸው በቁናተኝነት፣ በምቀኝነት እና ሥሥት ሰለሆነ የሚሽኪሹሩት በጥላቻ ቀለበት ውስጥ ነው። የጨዋታችን ማዕከል "እርሶም ይሞክሩት" የሚል ሰምሜ የተሰጣት ባለስልጣን፣ አምባሳደር ብርሃን ገ/ክርስቶስ፣ የቀድሞ ባለቤቱ እና ኢፈርት ሆኑ።

ወደ ኋላ መለስ በለን የባለስልጣኗን ግለ-ገድል አያነሳን ጣልን። በፈጸመው በትዳር ላይ የማንታ እርምጃ ከስሬው እንዲባረር ተወስኖበት ስለነበረው "ከቡር አምባሳደር" ተነጋገርን። የስነ ምግባር ጉድለቶቹንም በዝርዝር አያነሳን የእልኮል ማወራረጃ አደረግነው። አምባሳደሩ ለወረት ያሳለፈው የመከራ ለሊት እንዴት እንደነጋ ተሚወትን። በሌላ በኩል ከቡር አምባሳደሩና የዲቪ ጨልሴዋ ንግስት ላለፉት ወርታማ ጊዜ የራኒከስና ሜከሲኮ ሆቴሎች እንዴት ማህሌት ቆመው እንደሚያድሩ በእይን ልቦናችን ተመለከትን።

ከአተይ ጋር የነበረን ጨዋታ በኢህአዴግ ባለስልጣናት ዘንድ ቤሔሜት እና ቅሬታ የሚኑትን ጉዳዮች እውነታነት ያረጋገጠ ነበር። በተለይም የኤፈርት ገንዘብ እንዴት፣ በማን እና መቼ በውጭ ሀገር ባንኩች እንደሚቀመጥ የሚንረው ከሀት ያልራቀ መሆኑን የሚያመላክት ሆነ። ከዚህም በተጨማሪ የነበረን ቆይታ "ኢትዮጵያን ወክሎ" ተብለው የሚመደቡ አምባሳደሮች እና ዲፕሎማቶች የት ሀገር በምን መመዘኛ እንደሚመረጡ ህወሓት የቀረፀው የውስጥ መመሪያ መኖሩን ማወቅ የሚያስችል ነበር።

ርግጥ በውጭ ጉዳይ መስሪያቤት ያለው ሠራተኛና የዲፕሎማቲክ ሠዎች ምደባ በአድሎ የሚፈጸም እንደሆነ በተጨባጭ መረጃዎች እናውቃለን። ድሮም ቢሆን ከህወሓት ውጪ ያሉት የቤሔር ድርጅቶች ለብቻቸው በተሰበሰቡ ቁጥር ከለደራሹ በማይመጣ መልኩ በተደጋጋሚ ቅሬታ የሚያቀርቡበት ሆኗል። በተለይ ህወሓት ለሁለት የተሰነጠቀ ሠሞን ፓርቲው ተጻኪሟል በሚል ከሚቀርቡት ግልፅ ትችቶች ዋነኛው ይሔ ሆኖ ነበር። በአካል በተገኘሁበት የካርታ ስራ

ድርጅት አዳራሽ የአህዴድ ባለስልጣናት ስብሰባ፣ ለቶ መለስ ሰጥያቁው ምላሽ አተቶ ሲገደፉደፍ ተመልክቻለው። ያሰግንባራዝር የተፈጠረውን በዘር ላይ የተመረኮዘ አድሎ እውነት እንደሆነ እምኖ ሊቀበል አይቻለሁ። ቢሆንም ግን ኢ-ፍትሐዊ አሠራሩ የተፈጠረው የአንጀምቤ ሚትግራይ የበላይነት" ሮሚያሰፍን ምኞት የወለደው እንደሆነ አሰረግጠ ተናግሯል። አንጀምቹ እነ ተወልደና ሰየ ሚትግራይ የበላይነት" ለማምጣት ሲሰሩ እንደኸረሙ እጋልዉል። አጋሻምቹ ሆነ ብለው በፈጠሩት አድሎአዊነት የወንጀለኛ ሰሜት እንደሚሰማው ተናግሯል።

እንደ እውነቱ ከሆነ ለቶ መለስ በወቅቱ የክረውን ፈታኝ ሠአት በዚህ መልኩ ካለፈው በኋላ የዲፕሎማቲክ ሠዎች ምደባ መመሪያ እና አሠራሩን ይቀይረዋል የሚል ተስፋ ነበር። ሆኖም እንዳንድ ሲታይታ የሚሆኑ ጥናዊ ለውጦች ከሚድገርግ ውጪ የተሰየ ነገር አልተፈጠረም። ይልቁንስ የህወሓት የውስጥ መመሪያ እና ደንብ በማውጣት የድርወን "የትግራይ የበላይነት" አመለካከት እንዲጠናከር አደረገ። መዳቢና አባፊሪዎቹ ራሳቸው ህወሓቶች ሆኑ። ዳግም ህወሓቶች እኛ አህዴዶችን፣ ብአዴኖቻችንና ዲኢህዴንቻን አታለሉን። አሞኙን። ሙንቅላት ወፍራምና እንተተ ደንዳናንታቸውን በእደባይ አሳዩን።

በሁሉም የኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣናት እንደሚታወቀው "ኢትዮጵያን ወክሎ" የሚባሉ አምባሳደሮች እና ዲፕሎማቶች የሚመደቡት በሶስት ቁልፍ የህወሓት ባለስልጣናት ውሳኔ ነው። ኦህኩን ይማረውና ጠቅላይ ሚንስትሩ መለስ፣ የውጭ ጉዳይ ሚንስትሩ በዩም መስፍንና ፀጥታው ሀላፊ ጌታቸው አሠፋ ናቸው እነዚህ ባለስልጣናት ሲላውን ያገለለ ስውር መመሪያ ደንብና አሠራር ቀርፀዋል። ቅሬታ የሚያሰማውን የሚያስፈራሩበት ብሎም የሚሠየቱበት ሠይፍ አዘጋጅተዋል።

ይህ "በሥንገስት ውስጥ ያለ ስውር መንግስት" የዲፕሎማቶች ምደባ ሲያደርግ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ነገር አለ። ይኸውም ተመዳቢዎች ለኤፈርት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ላይ በመመርኮዝ ይሆናል። ከአምባሳደር ጀምሮ እስከ የኤምባሲው ሹፈር የሚመደቡት ሠዎች ለኤፈርት ገበያ የማፈላለግ፣ በርካሽ ዋጋ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቧቸውን ማሽናችና ምርቶች የማጓጋጀት ስራ የሚሰሩ መሆን ይገባቸዋል። ሹመታቸው እምባሳደርም ሀገም ሲላ፣ ኤምባሲውን በውስጥ የሚመሩት እነዚህ የህወሓት ወኪሎች ናቸው። የተመዳቢዎቹ ሞንኳሬ እና ደክመት የሚመነው ለህወሓት እና ለኤፈርት ኩባንያዎች ከሚፈጥሩት እድል በመነሳት ነው። ከዚህ በተጨማሪም ህወሓት እና ኤፈርት ከኢትዮጵያ የሚያሸሹትን ገንዘብ እየተቀበሉ የሚያስቀምጡት

እነዚህ ሰሞር ተልዕኮ ያላቸው ዲፕሎማቶች ናቸው። የህዝቡን ከዝና የተቀማጠረው ኤፈርት ሀብትን በቡድን እና ግለሰብ ስም በማስቀመጥ የሚሸሸገው እንደዚህ ዓይነት የውስጥ አሠራር ስለ ቀረበ ነው።

(ሰናይ ትሬዲንግ ስራ አስኪያጅ ታጋይ አቶ ታደለ ጋር በነበረኝ ቆይታ የሚመራውን ተቋም ... የገንዘብ እና የሰነዶች (ላፕቶፕ ...) በሆቴል መሰከ እንደተወሰደ ... ማቀፍ አለፈልግም። እንዳንድ ጊዜ በሆቴሉ እንጂ ... ከኢ ውስጥ የሚወሰደው ገንዘብ ወደን መሆ ኢህአዴግ ቢሮ ሠራቶች ከሚገኘው በኢትዮ ... ይሰጣል። ከዚህ በተጨማሪም አርከበ እቁባይ፣ የደህንነት ቢሮው የበላይ ሃላፊዎችና የህወሓት ... ቢሰራን ላይ ያላቸው አመለካከት የወዳጅነት እንዲሆን ያደረገው ግርት ታጋይ ... በስራ የተደሞ ጓደኞቹንም ሆነ ባለስልጣናት ... የሚረዳው አይደለም። ከዚህ በተረፈ የቀድሞ ጓደኞቹንም ሆነ ባለስልጣናት ... ቀጥር ጊዜ ለሆቴሉ ስብሰባ እና መሰል ዜናዊ ነገሬ ሚኒስትር ዴኤታ ባደረሱት ለምን ... ሚስጥሩን ያውቃል፣ የምታገኙት ከሆነ ንገሩልኝ በማለት የሚናገረው ከሌውንት የረቀ ነው።

ከኢህአዴግ ቢሮ ተዘዋውሬ ኮመዩኒኬሽን ጽቤት እንድመደብ ያደረገው በረከት ስምኦን ነው። ህወሓቶች በዚህ ቁልፍ ቦታ መመደብ ያስቡት የእኛ ሰው ነው በማለት ይፋዊ ቅሬታ ሲኣቀ ማሰ እንዳቀረቡ አውቃለሁ... ቢሆኑ የሠራሁትን ሚስጥር ለምን ያውጣል የሚለው ቅሬታ ተገቢ ... አይመስለኝም። ጉዳዩ ከግለሰብ ሚስጥር በላይ የሀገር ሀብትና የመንግስት ሆኗል። ወዳጄ አቶ ... በዚህ ማስታወሻ መግቢያ ላይ ለሰጀኝህ ያቀረብኩትን ምክር ላንተም ይሁንልኝ። በመቅድሙ ... እንደተጠቀሰው፤

ግትግራይ ወጣቶች ይህን ማስታወሻ ሲያነቡት በንዴት ለእምር እንዳበሉት። የሌና ... ለመጠበቅ በማሰብ፤ ማመለከርና ማስተዋል ኢሲኦት። መሬት የተነጠቀውን እውነት ... ለመረዳትና ለመከራከር ህወሓት በትግራይ አያደረገ ያለውን ከሌሎች የብሔረሰብ ድርጅትና ከሌሎች ጋር በማወዳደር ተመልከቱት... የወዲ አፎም ወጣት ተከስተ ስብሀት ነጋ ይህን ማስታወሻ ሲያነብ ራሰህን የሰመስለ ወጣት ደሲታው መሀመድ ሚሚ ውስጥ ከተትኩ... ኣፎም ... መሰሉ ሲታነበ የመለከት ዶር ለስና ... ቀሚስ ውስጥ ግቢ... ያላበስኩሉ አለላ ሠላምን ይህንን ማስታወሻ ሲታነብ እንደ ቀደመው ማስታወሻ "አውቀዋለሁ ... አዘዙ አሠራልዋለሁ" እያለክ በሸገር ቤቱ ከመቀ ይልቅ አሽቱ አማ ኬና ሚሚ ውስጥ ንበተህ

እንዳበውሎ... ። አቶ ዘይ ይሆን ማድረግ ከቻለ ድርጊቱ እብሮ የፈፀሙትን ሚስጥር የሚያውቅት ሊሆን የተጣሰመዉን የማትናት እንደሆነ ተደርጋለሁ።

ሀገራችን ላይ አሉላ ሠላምን ወደ ሀገሬ በመሰስ በራ ዲሞክራሲውና ሠው በሰው ህወሓት ይዘዋቸው በማለት የሥራቂ ተታችን ጠይቆ የሚኖር የህወሓት ሰላይ ነው።]

ወደ ቀደመው ጉዳያችን ስንመለስ ከነና ስራ አስኪያጁ አቶ ታደለ ጋር የትዕምትን እቅድና አፈፃፀም ለንመለከት የምናገኘው "ሰናይ ትሬዲንግ" ነው። የትዕምት ንብረት የሆነው ሰናይ ትሬዲንግ በእንግሊዝ የንግድ ኩባንያዎች ምዝገባ ውስጥ "The trustees of EFFORT" በሚል ተመዝግቧል። ድርጅቱ የተመሠረተበት የስራ መስክ በአስመጪ እና ላኪነት ነው። ይሔ ህወሓት አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ ሁለት አመት በኋላ የተመሰረተ ኩባንያ ህወሓት በመላው አውሮፓ የሚያደርገውን ኢምፖርትና ኤክስፖርት በበላይነት የሚመራ ነው። ከእንግሊዝ ህግ መሠረት ተመዝግቦ የሚንቀሳቀሰው ሰናይ ትሬዲንግ በሼር ባለቤትነት የተመዘገቡት በእንግሊዝ ኢትዮጵያ ኤምባሲ በወታደራዊ እና ኢኮኖሚ አታሼ ሆነው የተመደቡ የህወሓት አባላቶች ናቸው። እነዚህ በኤንባሲው እንዲሠሩ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰዩም መስፍን የተሾሙ ዲፕሎማቶች በኤንባሲው ያላቸው ስልጣን ከአምባሳደሩ በላይ ነው።

ሰናይ አስመጪና ላኪ ትሬዲንግ ህወሓት መልሶ ሲደራጅ አገልግሎቱ እንዲሠፋና ከሌሎች የአውሮፓ ኩባንያዎች ጋር በሰብ ኮንትራት እንዲሠራ በማሰብ "ታወር ትሬዲንግ ካምፓኒ" በማለት እንዲደራጅ ተደርጓል። የኢትዮጵያ ህዝብ በዲፕሎማትነታቸው ደሞዝ እየከፈላቸው ህወሓት ደግሞ የታወር ትሬዲንግ አላማ ለማሳካት ይመድባቸዋል። የሶን ከሌት ስራቸው ለትዕምት ኩባንያ ለሆኑት አልመዳ ጨርቃጨርቅ፣ መስፍን እንዱስትሪያል፣ ብሩክ ኬሚካል፣ ህይወት ሜካናይዜሽን... ወዘተ ማሽኖችን ማፈላለግ፣... የአውሮፓ ታዋቂ ኩባንያዎችን በሰብ ኮንትራት እንዲሠሩ ማግባባት፣... ትዕምት ለሚያመርታቸው ምርቶች ገበያ ማፈላለግ ዋነኛ ተልዕኮአቸው ይሆናል። በአውሮፓ የሚገኙ ግዙፍ ኩባንያዎች ከታወር ትሬዲንግ ጋር የፈጠሩት ግንኙነት ፍሬው በግልፅ እየታየ ነው። ህወሓትም ለቁልፍ ስራ ቁልፍ ሠው መመደብ በሚለው መርሁ መሠረት ከመቀሌ ከንቲባነት አንስቶ ጓደኛዬ ፍስሀ ዘሩሁን (መአሲ) በእንግሊዝ ኢምባሲ ዲፕሎማት አድርጎ መድቧል። የታጋይ ፍስሀ መአሲ ትልቁ ስራ ለትዕምት ኩባንያዎች ገበያ ማፈላለግ ሆኗል።... ትልቁ ስራ ትዕምት ያለ ቀረጥ የሚያስገባቸውን ምርቶችና ማሽኖች እያፈላለ

በመግዛት መሳተ ሆኗል።_ ትልቁ ስራ ከባድ መኪና፣ ትራክተር፣ አውቶሞቢል የሚያ_ የአውሮፓ ድርጅቶችን በማፈላለግ ትዕምት ኢትዮጵያ ገበሞ እንዲሸጣቸው መደራር ሆኗል።_ ትልቁ ስራ ትዕምት ከኢትዮጵያ የሚያስወጣውን ዶላርና ታውንድ በውሎ የሚገኙ የህወሓት አባላት አማከኝነት ኢንቨስት ማድረግ አሊያም ባንክ ማስቀመጥ ሆኗል።

በነገራችን ላይ ቢቻይናም ተመሳሳይ ነው። በታሪክ አጋጣሚ በቻይና ንዋንዙ የሚባል ግዙት ሰንበኛ ካድሬዎችም በጣም ተገርመው በተሸናገን ቁጥር የምንጫወተው ነበር።

ከግምታችን ውጪ የነበረው አጋጣሚ በአጭሩ እንዲህ ነበር፦

በዋንዙ ፕሮቪንስ ለንብኝት የሔደን ነ ካድሬዎች በሳምንት አንድንበኝ የተመረጠው በቻይና የሚገኘውን ትልቁ አውቶሞቢል የሚሠራ ኩባንያ ነበር። በተቀመጠልን የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ወደ ኩባንያው ሔድን። ከጠበቅነው በላይ ከፍተኛ አቀባበል ተደረገልን። አቀባበሉ የደመቀው ይዞን የሔደው የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ የወጣቶች ሊግ ፕሬዝዳንት በመሆኑ በኋል ላይ ተነሳሐልን። ቻይናዊያን ቢፓርቲ መዋቅር ተመድበ የሚሠራ ባለስልጣን እንደ ፈጣሪ አንደሚፈሩ የተገነዘብነው በዛ ንብኝታችን ወቅት ነበር።

አናም የመኪና ማምረቻ ኩባንያው ስራ አስኪያጅ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ለማድረግ ወደ መድረክ ወጣ። ለካስ ለስራ አስኪያጁ የተነገረው አንግዶች ከአፍሪካ አሸር ሀገሮች የተወከልን የውጭ አመራሮች እንጂ የትኛውን ሀገር እንደወከልን አልነበርንም። ስራ አስኪያጁ የካምፓኒውን ስራ ከማስተዋወቁ በፊት ልኡካን ቡድኑን ከየት ሀገር እንደመጣን ለማወቅ የቡድን መሪዎችን በተናጠል መጠየቅ ጀመረ። ከሳውዝ አፍሪካና ግብፅ ቀጥሎ የእኛ ቡድን መሪ "ኢትዮጵያ" ብሎ አስተዋወቀ። ወጣቱ ስራአስኪያጅ ግራ ገባው። ግራ መጋባቱን የተመለከተው የቡድን መሪያችን "ኢትዮጵያ"...ምስራቅ አፍሪካ!...የ3 ወረ የፀሀይ ፀጋ!... የሠው ሏጅ መገኛ! ...ቅኝ ግዛ ያልተያዘች ብቸኛ አፍሪካዊት ሀገር!" እያለ ደረደረ። ወጣቱ ስራ አስኪያጅ "ምንድነው የምትቀበታተረው?" በሚመስል መልኩ አተኩሮ ተመለከተው። አጠገቡ የተቀመጠውና ሁኔታው የተገለጠለት የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ የወጣቶች ሊግ ፕሬዝዳንት ወደ ጆሮው ጠጋ ብሎ በቻይኒኛ ነገረው።

ስራ አስኪያጁ በሚያስገርግር መልኩ ራቱን ፀሐይ አስመስሎ፣

"እነ ኤፈርት፣ ...ትግራይ ኤፈርት። ...ባለፈው ባምንት ከአምባሳደራችሁ አዲስአለም ባሌማ ጋር እራት በልተናል። አዘሀ የምታቱትን አውቶሞቢል ትግራይ ለመገጣጠም ፍላጎት አንዳላት ነግሮናል። ከሦስት ወር በኋላ ትግራይን ለመጎብኘት አመጣለሁ። ተግራይ በብዛም ቆንጆ ሀገር እንደሆንች ነግሮናል።" በማለት ተናገረ።

ከስራ አስኪያጁ ንግግር በኋላ ሁላችንም ተያየን። ሠውየው ኢትዮጵያን በስም እንኳን እያውቃትም። ይልቁንስ ኤፈርት እና ትግራይን በተመለከተ ዝርዝር ማብራሪያ ባለተሰጠው ኢትዮጵያ የምትባለው ፍጡር ትግራይ የሚባል ሀገር ውስጥ እንዳለች ተነገረዉ። ...ትግራይ ሀገር፣ ኢትዮጵያ ከፍለሀገር፣ ...ትግራይ ቻይና፣ ኢትዮጵያ፣ ንዋንዙ፣ ...ያሳዘናል።

በዚህ ቢያቆም ምናለበት?

ከአስሩ የአፍሪካ ሀገር ልውካን ቡድኖች ተደብቀ በሚስጥር ለእኛ ብቻ ልዩ የአራት ማዕዘን መዚጋጅቱን ተነገረን። በአራቱ ላይ በሚኒስትር ማዕረግ ያለ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ መሪ፣ የፓርቲው ወጣቶች ሊግ ፕሬዝዳንት እና ማብሃለውን የጠራው የአውቶሞቢል ፋብሪካ ስራ አስኪያጅ እንደሚገኙ ተነገረን። የአፍሪካ ወገኖሞቻችንን አምባሲያችን ሊያናግሪን እንደሚፈልግ በመናገር ዋሸናቸው። ብዙም ሳይቆይ ሽንጠ ረጃጅም ተቋቁር ማርሲዲሶች ሆቴላችን በመምጣት ወደ ማብሃለው ወሰዱን። የሚገርም ድግስ ነበር!!

ብቻ እንደ ባትሪ የተሞላውን የሚተረተረው የፋብሪካው ስራ አስኪያጅ እየመላለሙ "እናት ሀገር ትግራይ" እያለ ሙቀራት አልተመቸኝም። ከዚህ በኋላ አስተካክሎ እንዲናገር ሰለፈለኩ የእኔ መናገር ተራ ሲደርስ ሀገራችን ኢትዮጵያ መሆኗን፣ ትግራይ ደግሞ የኢትዮጵያ አካል እንደሆነች ተናገርኩኝ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ወደ 90 ሚሊዮን እንደሚጠጋ፣ ከዚህ ውስጥ ከ5 ሚሊዮን የማይበልጠው ብቻ ትግራይ በምትባለው ከፍለ-ሀገር እንደሚኖር ረዘም አድርጌ አስረዳሁ። ሠውየው በመሳሳት ይቅርታ ጠይቆን ከዚህ በኋላ "ኢትዮጵያ" እያለ እንደሚጠራ ቃል ገባ።

ከእኔ ቀጥሎ የተናገረው የትግራይ ውጣቶች ማህበርና ሲግ ፕሬዝዳንት አብርሃ ገቦህድ ነበር። አብርሃ በተቆጣ ስሜት ውስጥ ሆኖ "Tigray is equal to Ethiopia... Ethiopia is equal to Tigray" በማለት ለማስረዳት ሞክረ። የአዲስ አበባ ውጣቶች ፕሬዝዳንት ታጠቅን ጨምሮ የሁሉም ከልል ተወካዮች አብርሃን ተቋቋመው ተናገሩ። አብርሃ ተናግሪዎችን እያጽረጠ

እንዲያስተካክሉ ሲያከር ተናድጀ "አብርሃ! አዚህ ውስጥ ካለንው 12 ኢትዮጵያውያን ዘ ያህሉ ትግሬይ አይደለንም ቡማስት አቅጨን ነክርኩት። አስቲ ይፈንዳ ይሆን እየቸሰሁ!... ደግሞም እውነት ነው፣ አብርሃ ባሠባበት መንደር እንደድ ከተባለ "አናት ሀገር ኦሮሚያ!_" አናት ሀገር አማራ!_"አናት ሀገር ደቡብ" እያልን ልንተዋል ነው። _እንዴት ይተፋል! _እንዴት ይከብዳል!!

ከዛች ሰዓት በኋላ "ወዲ ገሞህድ" ለንቦጩን ጣለ። መቼም የህወሓት ታጋዮችም ሆነ ከትኩቱው ያሳደጓቸው ተተኪዎች በትንሹ ማኩረፍ ይወዳሉ። ከሁሉም የብሔረሰብ ድርጅቶች የራሳቸውን አከልና እምሰል መፍጠር የቻሉት ህወሓቶች ብቻ ናቸው። _እናም ተተኪው የትግራይ ፕሬዝዳንት እኮረፈን። ቁልቁል ሳየው ተመልከተ ፊቱን ከፊቴ ላይ እንሳ። እያሠላሠለ ያለውን ነገር ከእንደበቱ ሳይወጣ በእይኑ ውስጥ አነበብኩት። እቆን ለጉሞ የቀረበለትን በአሳ ነባሪ ሲጋ የተዘጋጀ መረቅ ይጋትው ጀመር። ጋባናቸን ያመጡትን ታዋቂና ውድ ባህላዊ መጠጥ ሎንግ ሁ ዶ (Long Hu Dou) መለኪያ እያጋጨን እንደንጨልጥ ሲጠይቀን ከቻይናምቹ ጋር ብቻ በመገጫጨት መጨለጥ ቀበለን። የአብርሃ ገሞህድ ኩርፊያ ሁለት መለኪያ ሎንግ ሁ ዶ እና ባይጃ (Bai Jiu) ጠጥቶ እስኩከር ነበር። ለነገሩ ሁላችንም በቀረበልን አልኮል በእጭር ጊዜ ጥጋቢራችን ዞሮ ሰለንበር ከቻይና ወንድምና እህቶቻችን ጋር የነበረን ወሬና ሞራራ አብዮታዊ መስመሩን ዘሉ ነበር።

(ለንደ እውነቱ ከሆነ ቻይና ዝሮሚ ሀገር ናት። የሦስት ሳምንት ቆይታችን የሦስት ለመቃ ያህል ቆይታ ለንዲደረን ሠው ቻይናን ለንድናውቃት እድርንናል። ፕሀፍ ጂጅ በቲይንሜና "ታላቁን ግንብ" ያተበኩሙቸው ቢንጂንግን ጨምር ሲድስት ያህል ግዛቶችን ለመጎብኘት ችለናል። ከአንደኛው ግዛት (ፕሮቪንስ) ለላኛው ግዛት ለመሔድ በአማካይ የሦስት ሠአት የለውርፕላን ጉዞ ይጠይቃል። ቻይና ሔደው የሚያልቋባት ሀገር አይደለችም... የሀገሯንም ኦሮ ከፕሮቪንስ ፕሮቪንስ በባህረው የተለየ ነው። ሀገሯ ለመጋገኑም በዛው ልክ ይለያያል። ከምብ ጋር በተያያዘ ንዋንዘምቾ ታዋቂ ለባህል ለለቸው። "በአየር ላይ ከሚሔድ ለውርፕላን፣ በመሬት ላይ ከሚሄድ መኪና፣ በውሃ ላይ ከሚሄድ መርከብ በለተቀር ሁለንም ለንበላለን" ይላሉ። ለኛም ብንሆን በአብዮታዊ ግዴታ ተጠርንረን ለነ ባይጂ (Bai Jiu) ሹንጂ (Huang Jin) እና ሎንግ ሁ ዶ (Long HU Dou) ለንበላ እና ለንጠጣ ነበር። ...ቢቻይኒኛ Long ለባብ ሲሆን Hu ደግሞ ደመት ነው።_ለባብ እና ደመት !! ...ለዝርዝር ማለታወሻው የክርሞ ሰው ይበለን)

ታዲያ ይሔ በግለሰብ ስም ገንዘብ ማሸሽና ማለፋሙ መሰናክል የሚያጋጥመው ጊዜ አለ። አንዳንድ የህወሓት ባለስልጣናት በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ይዘው ይጠፋሉ። የቀድሞው ገቢዎች ሚኒስትርና በጓላም ላይ የኤፈርት ምክትል ሀላፊ የነበረው ጌታቸው በላይ ይህንን አድርጓል። ደሞ ሌላ ጊዜ ባለስልጣኖቹ የስነ-ምግባር ንቅዘት ምክንያት ተመሳሳይ ገንዘብ የሚበከንበት ጊዜ አለ። ለዚህ አባባል ምስክር የሚሆነው ደግሞ በአንድ ወቅት በአሜሪካን የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆኖ የተመደበው ብርሃነ ገ/ክርስቶስ የፈፀመው ቅሌት ነው። ይህ የአምባሳደር ብርሃኔ በነ- ምግባር ጉድለት በህወሓት ካድሬዎቻ ዘንድ እንደ አግር አሳት በውትር የሚነሳ አጀንዳ ሆኗል። በየጊዜው በህወሓት ውስጥ በሚካሄደው ግምገማ የሠወናው ሀጢያት • እየተወሳ የትግራይ ህዝብና እናት ድርጅቱን ይቅርታ እንዲጠይቅ ሁሳብ ይረመጻል።

እነሆ ዛሬም ታጋይ አተይ የቀረበለትን ደረቅ ውስኪ ሽየተጋተና ባንኩኒ እየደበደበ የሚያወጋኝ ይሆንን ታሪክ ሆኗል። ጨዋታውን ከስር መሰረቱ ጀምር እንዲያጫውተኝ ፈልጌያለሁ። በመሆኑም እንዲህ በማለት አስተያየቴን ጀመርኩ፤

"አተይ፣ አንተ እኮ በኤፈርት ማርኬቲንግ ዴፈከተርነት መወሰን አልነበረብህም። አዚህ መሰፍንን ተክተህ የትዕምት ሰራ አስፈጻሚ መሆን ይገባህ ነበር። ትምህርት ዝግጅትህ ዶክትሬት ሊደርስ አንድ ድግሪ ብቻ ነው የቀረህ። በዚህ ደረጃ ያሉት ጥቂት የኢህአዴግ ባለስልጣናት ብቻ ናቸው። እንዳየሁት ከሆነ ነገሮችን ከስር መሰረቱ በጥንቃቄ ከሚያዩ ጥቂት የህወሓት ባለስልጣናት እንዱ አንተ ነህ። በተለይም የማስታወስ ችሎታህ ሳስበው በጣም ይገርመኛል። አንተን የፈጠረች ትግራይ ሞንጀራዋ እና መአሲን መፍጠሯ በጣም ያሳዝነኛል። አሁንም ቢሆን የትዕምት አልጋ ወራሽነት ከአንተ ውጪ ማሠብ አይቻልም አልኩት።

ፊቱ እንደ ቱትር ፀሐይ አብረቅረቀ። ባቀረብኩለት መግሳ እንደ መኩራራት ቢለው ታወቀኝ። በደስታ ስሜት ፈነደቀ። በዚህ ስሜት ውስጥ እንዳለ በአተይ ውስጥ የህወሓት ባለስልጣናትን ተመለከትኩ። ሁሉም በዚህ ባህሪ ተመሳሳይ ናቸው። ምናልባትም ለምን ተመሳሳይ እንደሆኑ ለማወቅ ዝርዝር ጥናት ሳያስፈልገው አይቀርም። ከሞተ ሠው የተሻለ ስብዕና የሌለውን "እንተ እኮ የሀገር ብርሃን ነህ" ተብሎ ሲሞነስ በቁሙ ይሠከራል። በጠራራ ፀሀይ የሚታሸና አልሚ የሆነውን ታጋይ ባለስልጣን "እንተ እኮ የጀግንነት እና ታላቅነት ተምሳሌት ነህ" ተብሎ እንዲነገረው ይፈጋል። "የህወሓት መሪ" ከተባለማ ሽላሚውን የአህዴድ፣ አሊያም የብአዴን ወይም

የደኢህዴን መሪ እንደሚያደርገው ቃል ይገባልና መጀመሪ የበታችነት ስሜት መጥፎ ነው። ራስን እንዳያውቅ ያደርጋል።

"አተይ፣ "አርሰም ይሞክራቶ" ስለተሳሳቷቸው ባለሰልጣን እንዲት ልታውቅ ቻልከ!" በማለት ጠየኩት።

በነገራችን ላይ ባለሰልጣኗ በትምህርት ሙያዊ ችሎታ በብዙ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ትታወቃለች። በተለይም በአንድ ወቅት በዐባይ ሀላፊነት የተመደቡበትን ተጃም ባልተጠበቀ ሁኔታ ግልብጥብጡን በማውጣቷ ከፍተኛ አድናቆትን ተቸራ ነበር። በወቅቱ በነበሩት የግል ሚዲያዎች ሳይቀር "ተቋሙ በአከሊት ጊዜ ቀረ" እስኪመስል ተደርሶ ነበር። በኢትዮ. ኤርትራ ጦርነትም የነበራት ሚና ቀላል አልነበረም። ያ ሁሉ የፈሠሠ ደም፣ የወደቀ ነፍስና የባከነ ንብረት ለአለም ፊፓርት ሲደረግ የነበረው በእሷ እንደበት ነበር። ርግጥ የህወሓት ባላጉጣ በመሆን እሚረኩ መሸን የነበረ የቃድሞ የሚን ወዳጂ (ሠወቶው "my cohabit lady" ይሊታል) የህዝብ ግንኙነቱን ስራ እማዚታል። በተፈጠረው አጋጣሚ በአጋባሲሩ ተቀምቶ የነበረ ወዳጁን መልሶ በመገጠቅ ፍቅራቸውን ማደስ ችለዋል።

አተይ በረጅሙ ተንፍሶ፣

"የሚገርምህ የትግራይ ህዝብ ገንዘብ ከተበላ በኋላ የሲትየሞን ማንነት ለማጥናት ተሞክሮ ነበር" በማለት ንግግሩን ጀመረ። አስከትሎም፣ "ሲትየሞ ተወልዳ ያደገችው በአዲስ አበባ ነው። አስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን የተከታተለችው በአዲስ አበባ ሲቶች ብቻ የሚማሩበት ትምህርት ቤት ነው።

"ሲትየሞ ትምህርቷን የተከታተለችው የቀድሞ ኮምዩኒስት ሀገር የሆነችው ሶህብረት ነው። በርግጥ በኋላ ላይ ህወሓት ባደረጉት ምህራዊ ጥናት ሶህብረት ኮሚኒስት አንዳልነበረች ተደርሶቢታል። አሜሪካን የህዝባችን ስትራቴጂያዊ ጠላት እንደሆነችው ሁሉ ሶህብረትም ተመሳሳይ ነበረች። ምንም እንኳን ሁለቱም ኢምፔሪያሊዝም ቢሆኑም፣ ሶህብረት ሶሻል ኢምፔሪያሊስት ነበረች_" ከማለቱ እቋርጬው፣

"አተይ አሰጉ ከህወሓት የነበ ዓመት ጉዞ ማምጣጣ መልሰና ላይ እንብቢ ተረድቼዋለሁ፣ አሁን ያልገባኝ ስለ ሲትየሞ ብቻቸው ወደ ኋላ ሌላ ተንታኔ መፍደህ ነው" አልኩት።

አተይ ደረቅ ፈገግታ እያሳየኝ፣

"ጉዳዩን ከስር መሰረቱ ላማውትህ ብዬ ነው። ነገሮችን መጀመሪያ ፓለቲካሊ ማየት መልመድ መቻል አለብህ። ከጅምሩ ፖለቲካሊ ማየት፣ ካልቻልክ በኋላ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ላይን ማየት ይቸግርሀል። በአብዮታዊ ኑርህ የአብዮታዊ ዲሚሀራሲ አሰተሳሰብ የበላይነት ማረጋገጥ ያቅትሀል። ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ አፀድ ወጥተህ ማህብ ከጀመርክ ደግሞ የሐይል አሠላለፍህ ይታየሬል።

ህወሓት አንዳሰተማሪችን ከሆነ አሜሪካ እና የቀድሞዋ ሶህብረት የትግራይ ህዝብ ስትራቴጂክ ጠላቶች ናቸው። ጠላትነታቸው መጀም የሚቀየር አይደለም። ሌላው ቀርቶ በአንዚህ ሀገራት ረጅም አመት በትምህርትና በተለያየ ምክንያት ቀይተው የሚመጡ ሠዎች በጥርጣሬ የሚታዩ ናቸው። ብዙዎቹ ሲአይኤ እና ኬጂቢ የላካቸው ሲሆን ይችላሉ። እናም ሲትየሞን ኬጂቢ የላካት ትሆናለች በሚል ህወሓት ከስር መሰረቱ ማንነቷ እንዲጠና አደረጉ በማለት ተናገረ።

አተይ አልኮሱን ፉት እያለና አካባቢውን እየቃኘ፣

"ሲትየሞ እንደጠበቅናት የስለላ ተልዕኮ የመሸከም አቅም ያላት አይደለችም። ከጠዋት እስከ ማታ ሾድካ እየጠጣች አቅሷን የምትስት ናት። ካገኘቸውም ጋር ትሔዳለች። ይህ የተግባር እንቅስቃሴም ጥሩ ተሞክሮ እንድትጨብጥ አድርጓታል። እምበላደር ብርሃኑን ለማጥመድ ጊዜ ያፈጀባት ያካበተቸውን ልምድ በሙሉ አቋም መጠቀም ስለቻለች ነው። ብጹይ ብርሐኔን የማያውቀውን አለም አሳይታው ጣሰ ውሰጥ ከተተቸው። በአብዮታዊነት የተገባውን ቃልኪዳን አፈረሰ አለና ራሱን ነቅንቀ፣

"በሁኔታው የተበሳጨችው የእምባላደር ብርሐኔ ሚስት አድፍጣ እጅ ከፍንጅ ያዘቸው። አልሀ ስለገባች የፍቺና የንብረት መከፋፈል ጥያቄ አነሳች። ሴትየዋ ይሀንን ጥያቄ ያነሳችው አፈርች በአምባላደር ብርሐኔ ስም በ10 ሚሊዮኖች ፕንዘብ እንዳበቀመጠ ስለምታውቅ ነው። ቅድም እንደነገርኩህ የአፈርት ንገዘብ የሚቀመጠው በህወሓት አመራሮች የግለሰብ አካውንት ነው። እናም ሴትየዋ ሀሳቢን እንድታነሳ መለስ ሰዩም መስፍንን በአግላጅነት ላከው" በማለት ተናገረ።

በእድፍቶቱ አየኮመስትኩት፣

"እኔ ለኮ የሚገርመኝ የምትነግረኝ ታሪክ አይደለም። ከምንም በላይ በጣም የሚገርመኝ የአንተ የመረጃ ሶት ብዛቱ ነው። ከማውቃቸው የህዉሓት ጓዶች አንተን የሚስተካከል አላጋጠመኝም። መለሲም ይህን ሊያውቅም። እውነቴን ነው የምልህ ሰዩም መሰናን በአማላጅነት እንደመጣ ከአንተ ውጪ የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም። አልኩት።

እሸናፊት ባዘለ ድምዕት ውስጥ ሆኖ፣

"መቼ ጨረስኩህስ?_ ከላይ እንደጠቀስኩት ሰዩም የተሰጠውን መደብ ለመፈጸም አሜሪካን ሔደ። ሴትየዋም "እንጉቴን በካራ" አልታረትም አለችው። የፍቺና የንዝብ መካፈሉን ጥያቄ በሀግ መጪረስ እንደምትፈልግ እንቅጩን ነገረችው። በብጻይ ብርሃኔ ስም በባንክ የተቀመጠው ንዝብ የህወሓት እንደሆነ ቢነግራትም አሻፈረኝ አለች። እነ ግርታ የመሳሰሉ ሙግቶች እየጠራ በለምናትም የሚሆን አልነበረም። ጉዳዩን ወደ አሜሪካን ፍርድ ቤት መሠደቻው። የኒዮሊብራል ፍርድ ቤት ህዝባዊነት ስለሌለው ለአቧ እንደሚወሰን ተገመተ። የአገር ሽማግሌዎች በአግላጅነት ተሳትፉበት። መለሰ ራዕ አናገራት።በመጪረሻም ብዙዎች በምሳሌ ሲዋሾቋበት የሚናሩትን ንዝብ አቶፈሠችው" በማለት ተናገረ።

ሳያስበው ጠረጴዛውን በንዴት እየደበደበ፣

"የኤፈርት ንዝብ በዚህ መልኩ እየተብላ እስከመቼ ይቀጥላል?" በማለት ጠየቀኝ። የጠየቀው ራሱን በመሆኑ ምንም ልለው አልፈለኩም። ምንስ ልለው እችላለሁ?_ "ሊባን ሊባ ቢሰርቀው ምን ይደንቀው" ብዙ ልናገረው ወይስ "እሺ፣ አሚን፣ ልክ ነው፣_ በጣም ያናድዳል" በማለት ባንኮኒ ልደብድብ? እጆቹን እያወናጨፈ ወደ መፀዳጃ ቤት ጥሎኝ ሔደ።

አቶይ ያጫወተኝ የአምባሳደሩ ታሪክ በኢህአዴግ ቢሮ ካድሬዎች በሰፊው የሚወራ ቢሆንም በጣም ስለተደጋገመብኝ ጆሮ ሠጥቼው አለውቅም ነበር። በማት ብዙ እንደተከታተልኩት የአምባሳደር ብርሃነ ገ/ክርስቶስ ቢተሰባዊ ገድል በብዙዎቹ የኢህአዴግ ሠዎች የሚታወቅ ነው። በተለይም በህወሓት ካድሬዎች ዘንድ ማምታማ በመጣ ቁጥር የሚነሳ እጅጉን መሆኑን ተመለከትኩ። ከብዙ ዘመናት በኋላም የአምባሳደሩ የቅድሞ የትግል ጓደኛ የሆነው ንብሩ አስራት ጥያቄ በሚሞር መልኩ በመጽሀፉ ላይ ከታሰት ተመለከትኩ። አቶ ንብሩ አምባሳደሩ በሚሰቱ ላይ

ያደረሰውን በደል በለሆሳስ ቢጋልፀውም፣ ምን በደላት፣ አሷ ምን እርምጃ መሰደቸ የሚለውን ከመጥቀስ ተቆጥቧል።

አቶ ንብሩ አስራት "ሉአላዊነት እና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ" በሚለው መጽሐፉ የአምባሳደር ብርሃንን የስነ ምግባር ችሊት በገፅ 259 ላይ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፣

"ከዚህ ሰብስባ ሊላው ሂስ የቀረበበትና ካለው ሀገራዊ አንፃር አንዲነካ የተጠየቀው ብርሃን ንብርስቶስ ሃበር፣ በብርሃነ ላይ የቀረበው ሂስ በባለቢቱ ላይ ያደረሰውን በደል መካሪት ይደረጉ ሲሆን ምናው ሂስ ለቅሬቢም ሰዩም መሰናን ሃበር። ሰዩም ብርሃንን በተደጋጋሚ ብመከረውም ሊያዳምጠኝ ስላልቻለ መውጣት ሊለበት ብሎ ሲያሰብ ብርሃነ እና ሰዩም ከቶኖ ተጨቃቅጠው" በማለት ይገልጻል።

እነሆ ሊላ ዘመን አልፎ በሀገረ አሜሪካ ተሀኘሁ። አግሬ በረገጠ በሰምንቱ አንድ ወዳጄ ሚሪላንድ የምትባለውን የአሜሪካን ግዛት እያዞረ አስጎበኘኝ። በጉብኝታችን ወቅት አንድ ምድረ ገነት የሚመስል ቦታ ሊደርስ መኪናውን በዝግታ አየነዛ፣

"ይሔ አካባቢ ፖቶማክ ይባላል። የህብታሞች መኖሪያ ነው። የምታያቸው ቢቶች ዋጋ ለመጥራት ያስደነግጣል። በነገራችን ላይ የአንተ አምባሳደር ብርሃነ የቀድሞ ሚስት_

...

የለተይ ሾፈር ወደ ማደሪያዬ እየወሰደኝ የህወሓት ታጋይ ባለስልጣናት ባህሪያት ሪ ተደቃነ። እንድ ጊዜ የአዲስ አበባ ኢህአዴግ ከንቱ ስሚያዘጋጃት "ህዳሴ" ጋዜጣ ማህበራዊ አም ለማቅረብ የታጋይ ባለስልጣናትን ባህሪ ለማጥናት ተሞክሮ ነበር። ህላቡን ያመጣው የጋዜጣ ዋና አዘጋጅ መሠለ ገ/ሀይወት (የኢትዮጵያ ቴሌቭሽን ዜና እንባቢ) ነበር። ሐሳቡን በመ የጋዜጣዋ የበርድ አባላት የነበርን ስንደገፈው ተጋዳሊት ፍሬህወት አያሉው (በአሁን ሰ የኮሙንኬሽን ጽቢት ሚኒስትር ዲኤታ) ብቻ ተታወመችው። የፍሬ ተቃውሞ ግን ያሰበት ቢሆንም በቂ መከራከሪያ ማቅረብ ባለመቻሏ ሀሣቢ ተቀባይነት አላገኘም። ይሁን እንጂ የጥ ውጤቱ ተሠርቶ ከመጣ በኋላ ቢጋዜጣዋ "ማህበራዊ አምድ" ላይ የሚቀርብበት ሁኔታ በተገ መታየት እንዳለበት ተወሰነ። እኔ እና መሠለ ገ/ሀይወት በቅርቡ እንድንከታተለው ተመደ

የጥናቱ አካል መሆኔ ቢደሰደስተኝም ውጤቱ ግየለመሉት የአቸሊስ ተረከገሮ አሸንበታለው የሚል እምነት አልነበረኝም። ለማንኛውም ሊላኛው የህዉሓት ታጋይ ባለስልጣናት የአቸሊስ ተረከገ የሚከተለውን ይመስላል።

አጼ እና መሠለ ገለጀውት በዘረዘርነው ጥናት ከተካተቱት ውስጥ የታጋይ ባለስልጣናት የአልኮል ሱሰኝነት ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ተረልን ነበር። ይህንን የባለስልጣናት ባህሪ ማወቅ የቡደኑበት የተለያዩ መንስኤዎች ነበሩ። ከእነዚህ ውስጥ በዋናነት ቀድሞ የሚካ ታጋዮች የንበሩ ባላስልጣናት ካድሬዎች እየሞሉ ያሉት ከአልኮል ሱሰኝነት ጋር የተያያዘ መሆኑ ስለሚከረጠር ነበር። በተለይም በመጠጥ ግፉት ልቅ ወሲብ የመፈፀም እድላቸው አየሰፋ በመሔድ ስእርምት የሚሆን የውሳኔ ሀሳብ ለማምጣት በማሰብ ነበር።

ለአብነት ያህል በአዲስ አበባ ሙኖሪያ መዋቅር የተካሔደው ጥናት በቀበሌ ደረጃ በማካይ ሥላሳ የህወሓት ታጋይ ባለስልጣናት እንዲጠኑ ተደርጓል። እነዚህ ከሶስት ሺህ በላይ ታጋዮች ኮቶሰማሩበት ሰራ ከሚኒስተርነት ጀምሮ በካድሬ፣ ደህንነት እና ፖሊስ ሀላፊነት ነበር። የመኖሪያ መዋቅር የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ ባለስልጣናት በሚኖሩበት አከባቢ ሰለሚታወቁ እና የታቸኛው የድርጅት መዋቅር በቀላሉ ሊያጠናቸው እንደሚችል ታሳቢ የተወሰደ ነበር።

እናም የጥናቱ ውጤት አስገራሚ ግኝቶችን ይዘ መጣ። ከሠባ በመቶ በላይ የህወሓት ነበር ታጋዮች መጠጣት የሚጀምሩት ገና ጀንበር ማዘቅዘቅ ሰትጀምር መሆኑ ታወቀ። እነዚህ ታጋይ ባለስልጣናት በአብዛኛው ጠርሙስ ውስኪ በማውረድ የሚጠጡ ናቸው። በተለይ ከአከሰ ሰሊቶ በኋላ መጠጥ ቤቱ ለሌላ አገልግሎት እንዳይሰጥ አደርገው በዝጉብኝ ይጠጣሉ። ለመጠጥ ብቻ በቀን በአማካይ 300 ብር ያህል ገንዘብ ያወጣሉ። ይሔ የገንዘብ መጠን መንግስት ከሚከፍላቸው የወር ደሞዝ ከሶስት እጥፍ በላይ ነው።

እነዚህ የህወሓት ልማደኛ ጠጪዎች ምሽት በተጋመስ ቁጥር ያለገደብ የሚያወጡት አልኮል የተደበቀ አውነተኛ ባህሪያቸውን ፍንትው አድርጎ ያወጣል። ጀንበር እዘቅዘቃ እስከትጪርስ ድረስ እንደ እነሱ መዚቃ ወዳጅ የለም። በተለይም እንደአሮምኖ፣ ወላይትኛ፣ ጉራጊኛ እና አማርኛ የመሳሠሉ ዘፈኖች ሲመጡ አብሮ ሰመጪፈፈር ሁሉንም ያስገድዳሉ። በኢትዮጵያዊነት የሚችላቸው የለም። ሞቅታው አየጪመረ ሲሔድ ከላይ የተጠቀሱት የብሔረሰብ

ዘፈኖች እንዳይዘፈኑ ትእዛዝ ይሰጣል። በፍጋታው ትግረኛ ብቻ እንዲዘፈን ያስገድዳሉ። ወታቸው በሙሉ የኩራታቸው ምንጭ የሆነው ከትግራይ መወለዳቸው መሆኑን መናገር ይሆናል። አጠገባቸው ያለውን የሌላ ብሔረሰብ ተወላጅ ማሪፊያ ያጣቸው ወፍ ያደርጉታል። በሂደት ሰክሩ አየጋረጫቸው ሴሔድ ደግሞ ከትግርኛ ዘፈንም የበረሀ ዘፈኖች ብቻ እንዲሚሠሙ ጥብቅ ማሰጠንቀቂያ ይሰጣሉ። አሻቸውን እንደ ከላሽ ወደላይ ሠትለውና እግራቸውን አንደ ሂኒማር አያጠፋ እንባባ እንባባ ማለት ይጀምራሉ። አንደጉመሷ አየተቀጣጠሉ ጭራራውን ያጮሓታል። በነገራችን ላይ ይህንን ከበረሀ ጀምሮ ተቀጣጥሎ መሔድና "አርሆ" አያሉ ሲጨሩት ሠምቻለሁ።

በእነዚህ ታጋይ ባለስልጣናት ላይ የተካሔደውን ጥናት ያመለከተው ሌላ ቁምነገር አለ። ይኸውም መጠጡ አየጨመረ ሲሄድ የህይወት ቅራኔያቸው ፍንትው ብሎ ይወጣል። አሰቀድመው በደስታ ሲስቁና ሲጫወቱ የነበሩት ሙሉ ለሙሉ ተቀይር መባለጨት ይጀምራሉ። ወቅታዊው ከንበረው የመነናናት ሰሜት ወደ ራስንና ጓደኞን መውቀስ ይቸጋገራሉ። እንደ በተቀን ወፍ የበላያቸው ታጋይ ባለስልጣን ሲናገር የነበረውን ማጣጣል ይጀምራሉ። አልኮሉን በበረዶ አቀዝቅዞ መጠጣቱን በመተው በደረቁ ይጋቱታል። በባ ላይ ምግብ የመበላት ባህላቸው እንስተኛ በመሆኑ በቦዶ ሆድ የሚወሰዱትን አልኮል በአንድ ጊዜ ወደ ሚጋስሊታቸው ይወጣል።

ከዚህ በኋላ አተሰሶ የያዛቸው የመንፈስ ድህነት እርቃኑን መታየት ይጀምራል። በብርጭቆና ውስኪ ጠርሙስ ጠረጴዛ መደብደብ ይጀምራሉ። በስልጣን፣ በማዕረግና በደረጃ የሚበልጧቸውን የህወሓት የቅርብ አለቆች በስም እየጠሩ መሳደብ ይጀምራሉ። ከአለቆቻቸው አለመግባባታቸውና የልብ መሸፈታቸው ይገልጣል።

በእነዚህ የህወሓት ታጋዮች ላይ የተካሔደው ጥናት ያመለከተው ሌላ ቁምነገርም አለ። ይኸውም እነዚህ ታጋይ ባለስልጣናት የፓርቲያቸውን ሚስጥር እንደጪው የሚዙት በአብዛኛው በመጠጥ ቤት መሆኑን ነው። ፀሐይ ከማዘቅዘቋ በፊት የሥናፍጭ ስበሪ የምታክል የድርጅት ሚስጥር ለመናገር ፍቃደኛ አይደሉም። እንደውም ጪሞታቸው "ቦናፓርቲዝም የህይል አሠላለፍ፣ ፕሮ፣ ኪራይ ሠብሳቢ፣ ልማታዊ መንግስት፣ የቻይና እና ኮሪያ ተሞክሮ፣ የኮሚንታንግ ፓርቲ..." በሚል እንቲት እንጪት በሚሸት ድርጅታዊ ቃላቶች የታጀበ ይሆናል። በጪሞታ ወቅት ተጪማሪ ሀሣብ ማንሣት ከፈለን ደግሞ "መለስ እናዳለው፣ ድርጅቱ እንዳስቀመጠው፣ መደ... እንዳወረደው፣ የተሀድሶ መስመራችን ባስጪበጠን መሠረት" የሚሉ ድሪቶዎች ይደራርባሉ

የሚያቀርቡት መረጃ ትክክለኛ መሆኑን ለማስረገጥ ሲፈልጉ ደግሞ "ሲጋ ስውሀት፣ ...ስለ ስውሀት" የሚሉ ህወሓታዊ መሀላዎችን ያሰቀድማሉ። እንደባህሻ ከሆነ "ሲጋ ስውሀት" ማለት የትግል ጓዶቻቸው በሞቱበት ድርጅታዊ አላማ እንደማይቀጹ የሚያላየበት ነው። እንደዚህ አይነት መሀላዎች ያቀረቡት መረጃ እውነት መሆኑን ለማሳየት ስሜታዊ ልዕልና ይሠጣቸዋል። የመታመን አዳቸውን የበለጠ ያጠፋላቸዋል።

የሞቅታ መንፈሱ እየጨመረ ሲሔድ እነ "ሲጋ ስውሀት" ወደ ሠባባቸው ይሸሹ። "በና ፓርቲዝም" መፍለቂያው ወደ ሆነው የናፖሊዮን ቦናፓርቲ ትውልድ ሀገር ፈረንሳይ ይሸኛል። ተራን ጠብቆ በስነ-ስርአት መናገር ቀርቶ "እኔን ብቻ ስሙኝ" ማለት ይጀምራል። ቀስ በቀስ የፓርቲው ሚስጥሮች ሠፈድ ላይ ተነጥረው ይበጠራሉ። የሚቀርቡት ሚስጥሮች ከውስጠ ድርጅት አልፈው የታጋይ ባለስልጣናት የግል ህይወትን የሚጨምሩ ናቸው። የፊት መስመር የሚይዘው ደግሞ የአቶ መለስ ቤተሠብ ይሆናል። ይህ የሆነው ህወሓት ለህልት ከተሠንጠቀ በኋላ ነው። ከዛ በፊት የህወሓት ታጋይ ባለስልጣናት ከአቶ መለስ ይልቅ ስለ ተወልደ፣ ዓለምሰገድና ስዩ ማውራት ደሰ ይላቸዋል። የዘጠና ሦስቱ የህወሓት ስንጠቃ አቶ መለስ በግለሰብ ብቻ ላይሆን ቤተሰባዊ ድል የተቀዳጀበት ነው። የትኛውም ታጋይ ባለስልጣን ድርጅቱንና ቤተሰቡን እንደ መንደርደሪያ ካልተጠቀመ ማውራት አይችልም። ከሌላው ታጋይ የተሻለ አውቶት አንዳለው የሚለካውም በቤተመንግስት ዙሪያ ያለው መረጃ መጠን ነው።

88

የአቶ መለስ ቤተሠባዊ ሚስጥሮች የሚጀምሩት ከበረሀ ትዮት ትግሉ ጀምሮ ነው። እንደሚታወቀው ህወሓት በትጥቅል ትግል ከመን ወሲባዊ ግኑኝነት መፈፀም እንደሌለበት እቁጅ አውጥቶ ነበር። በወቅቱ ወሲብ ፈፅሞ የተገኘ የሠራዊት አባል በሞት እንደሚቀጣ ወሰኖ ነበር። በዚህ መመሪያ መሠረት በርካቶች ውሳኔው ተግባራዊ ሆናባቸዋል። ሆኖም ግን ይህ መመሪያ በአቶ መለስ ላይ ተግባራዊ አንዳይሆን ተደርጓል። መጽሀፉ "ህወሓቶች ሁሉ እኩል ናቸው፣ አንዳንዶቹ የበለጠ እኩል ናቸው" አንዲሉ ታጋይ መለስና ተጋዳሊት አዜብ የበለጠ እኩል ነበሩ። ወሲብ መፈፀም በሞት በሚያስቀጣ ሠአት ወሲብ እየፈፀሙ የማይቀጡ የእኩልነት ታጋዮች የበለጠ እኩሎች።

የአቶ መለስ ግለሰባዊ ሚስጥሮች ቤተመንግስት ከገባም በኋላ የቆሙ አይደሉም። "መለስ ስለሚበሳው ዘወትር ሚስቱን በጥፊ ይመታታል፣ በዚህም ምክንያት ልጃቸው ሠምሀል ለእእምሮ

ጭንቀት በመዳረግ የእደገሃቮር እፅ ተጠቃሚ ሆናለች" ከሚለው የቤተሰብ ወሬ ይጀምራል ለሠማነለ ሁሉ ነገር እሷን በአልጋ በሆነበት ሁኔታ እንደዚህ ባለና ጭንቀቷን ለመርሳት የገባችበት ሱስ ቀፍድዶ ስለያዛት እንደሆነ ይገመራል። የመጎጀት ሁኔታ ሰውን እስተዳደግ የሚፈጥረው ተጽእኖ እየተዘረዘረ ይገለጻል። ርግጥም ቡግንጮም ህብረተሰብ የፀጋ እስተዳደግ ሁኔታ በቤተሰብ ባህሪ መሠሠት የማይቀር ነው። አብዛኛውን ጊዜ ጥሩ ቤተሰ ለልጆች ጥሩ እስተዳደግ እንደ ቅድመ ሁኔታ ይታያል። በወላጆች መካከል ያለ ግጭትና ፍቺም ለህብረተሰብ ማንነትና ለነ-ልቦና ዋልታ ተደርጎ ይወሰዳል። የህ ልቦና ቀውስ ከቤተሰ ስለሚጀምር!

እቶ መለሰን ከመሠሉ ታጋዮች የጓዳ ታሪክ ቀነሱ የግል ወሲባዊ ወንች ይታወ ይረከባሉ። ታጋይ ባለስልጣናት ከወሀፈዎቻቸው ጀምሮ የአዲስ አበባ ተረከቦ ሎሞ ኮሪዳ እንዴት እንደሚያማግጡ ስማቸው እየተነቀሰ ይነገራል። አንዳንዶች ታጋይ የህቡ ባለስልጣ በመዲናይቱ የመታየት እድል እንዳያጋጥማቸው ከሀገር ውጪ ቆንጆችን ይዘው ይሔዳሉ። ይህ ቢሆን የራሱ ቅድመ ተከተል አለው። መጀመሪያ ኮረዳዎችን ወደ አስመጪና ላኪ ኩባንያ ያሸጋገሯቸዋል። በተጨማሪም እንደ እየር መንገድ ባሉ ተፈላጊ ቦታዎች ላይ የመቧቀሪ እንዲናራቸው ያደርጋሉ። ከአፈርት፣ ቻይና፣ ጁባይ፣ እሜሪካና አውሮፓ የሚመጡትን እንግ በአንዚህ እና ሌሎች ሱቆች የሚሸጡበት ሁኔታ ይመቻችላቸዋል። ሴት አሠቶቻቸን ወርታ የሚገጇንግ፣ ሽንጋይ፣ ጁባይና ፓሪስ የመሳሰሉ የአለም ብርቅዬ ከተሞች በሚገኙ ባለስ ሆቴሎች በመገኘት ይከፍላሉ። ታጋይ ባለስልጣናቱ፣ የደህንነት ፖሊሲና የጦር አዛ በቦርሳቸው የሞሉትን ቪያግራ እስኪጨርሱ ድረስ እንደ ቅሪላ ያለፋሉ።

በነገራችን ላይ ከላይ ቡተጠቀሰው ድርጊት ሰማቸው በሚነባር ቀደምት ከሚሰሩት ውስ እማቻሞቹ አርከበ አቁባይና ብርሃኔ ገ/ክርስቶስ፣ ...ስዩም መስፍን፣ ...አባይ ፀሐዬ፣ ሠሠን ቪ ...ጀነራል ሳዕረ" ...ኢሳያስ ወጊዮርጊስና ጓደኞቹ ፍሰሠ ዘሪሁን የቅድሚያ መከሰሩን ይደነ ርግጥ በህወሓት አመራር ውስጥ በእሁን ሠአት ባይኖሩም የሪፖርተር ጋዜጣ ባለቤት የሆ እማሬ አረጋዊ እና ሴኮ ቱሬ ጌታቸው የሁሉም ፊታውራሪ ናቸው።

ረእማሬ አረጋዊ ወደ ማይቀረው አሸር አየሔደ አንኳን አንፃልቨርደነት ይከናፈል። ሌላው ሪፖርተር ጋዜጣ ፀሀፊና ሴት ጋዜጠኛ ሲቃጥር አንደ ቅድመ ሁኔታ የሚሰቀምጠው ነገር አ

ይሽውም ለቶ አማረ በሚዲያ ኮሚኒኬሽን ሴንተር ቢሮ ሲያልፍ ለና ሲያገድም የሴቱ መልመጫ "ቾብ" ቦማድረግ... ጡታቸውን ለጋደ ካለ ኮሚደህልበለ ያልተጫነሥ መብት ይናደዳ ይህን ያልፈቀደች እገስት በሬፖርተር ውስጥ የመቁቦት ዜድኒ የመኝመን ንው። በከሬቻን ጎ የቅድም ታሽ አማረ አረጋዊ ሲሠኖ ባሀረ ከኢህአዴግ ለባለት ውጪ ሌሉች በር ሊትጽጽያውያን ኮሚያውቋት ንው። በቶላይም በጋዜጣና ሊሁች ሚዲያ ለካበቢ የተመንሩ መ በነውየው ሁኔታ ለንደ ጠኝ ያልሆነ ልከፍት ኮሚታይ ለንደሆን ይገልጻሉ። በዘርፉ የማረ ተመራማሪዎች ጥናት ቢሠሩበት ፍላጎታቸው ለንደሆን ይናገራሉ። ለንደ ሊጋግሚ ሆኖ በሬፖርተ ጋዜጣ ተቀጥሮው ሲሰሩ ከነበሩ ከለባት በላይ ጋዜጠኖች ጋር በተለያየ ጊዜ በነበረች ያሉናቸ ቶይታ ይሉንን የለማረ ንቅዘት ማረጋገጥ ችያለሁ። ሁሉም ጋዜጠኖች ሬፖርተር ለና ቢጋዜጣ የነበራቸውን ቶይታ ሲያነሱ የለማረን ቅንዝርንት ሳይጠቅሱ ለያልቶም። ከለዝህ ጋዜጠኖች ውጭ በተሳ ላይ የነሙቶኒከሽን ጽቢት ሀላፊ ከነበረው ሽመልስ ከማል ውጭ የተቆናት ከሀዝር ተመለ በለሚደባ ለና ለውሮፓ ይናሬሉ።)

የለማረ ለረጋዊ መዋረድና ከመፊት በታች መሆን ዘወትር የሚያስጨንቀው ቢሮ ሰምእን፣ ሠውየውን ለማዋረድ የቶየሳቸው ሴራዎች በርካታ መረሻዎች በእጅ እንዲኖረ አድርጓል። እማረ የትኖዋን የከተማ ተረከዘ ሎሚ ዱከም፣ ደብረዘይት፣ ሼሀንስበርግ፣ ሩባ ዋሽንግተን፣ ናይርቢ፣ አምስተርዳም... ወዘተ ይዘ እንደሔደ በሠእታት ውስጥ መረሻ እንዲደረ አድርጓል። አብዛኖዎቹ የመረጃ ምንጮቹ ደግሞ "በትልቁ ባለሀብት" ሀሪያ የተሠማሠት ሠዎ የኤርፖርት ደህንነትና ኮሚዩኒኬሽን ወኪሎች ናቸው። የትልቁ ባለሀብት የቤት ውስጥ ባሪዞ እማረን በሀገሀበ ፊት ለማጋለጥ የስውር ቪዲዮ ቀራጮች እስከ ማሠማራት ደርሠው ነበር። ከነ በተጨማሪም ሽመልስ ከማል የሪፖርተር የህግ ከፍል አዘጋጁን እንደ መረጃ ምንጭ ይጠቀማ ነበር።

የአተይ ሹፌር ማደሪያቸን ወደ ሆነው የማሰልጠኛ ጣቢያው የውጭ በር አመ ለደረሰኝ። የታዝኳትን የይለፍ ቢጫ ወረቀት አሳይቼ ወደ ውስጥ ገባሁ። ግቢው በየአስር ሜት ቀጥ ብለው ከቆሙት የፈደራል ፖሊስና ልዩ ሀይሎች ውጪ ጭር ብሏል። ሀንጻው ከሁለት ፎ በላይ ቱባ ባለስልጣናትን በአንድ ቦታ አፍኖ የያዘ አይመስልም።

ወደ ሀንጻው ውስጥ ስገባ የሁሉም ባለስልጣናት የውጭ በር ተከፍቷል። በአዳማ ያሰ ወበቅ እና የታፈነ አየር በርም ተከፍቶ የሚቻል አይደለም። የተወሰኑ ባለስልጣናት ፍሬሽቸ

በኮሪደር ላይ እንጥፈው እደጅ ተኝተዋል። ምድር ላይ በሚገኘው የቴሌቭዥን ከፍል ውስጥ ተረፍረፈው ከየጓቸው ውስጥ የለኔ ቡድን ውስጥ ያሉት ሦስ አንዳርጋቸው፣ ደመቀ መኮንን እና የማብርና ሚኒስትሩ ተፈራ ደርበውን ተመለከትኩኝ። ከአመሸሁበት ቦታ እያነዋርኩ ልዩነቱ ጀምሮኝ ሳይሆው በምድር ላይ ባለው ስምንት ተደራራቢ አልጋዎች በተደራረበበት ከፍል ውስጥ ሌሎች ባለስልጣናት የውስጥ ሱሪ እና ባለንሙድ ከእቴራ ለባበው ተመለከትኩ። ከባለስልጣናቱ እንዱ የሚሆሰው ማንኮራፋት ሀንጻውን የበጠበጠ በመሆኑ ትኩረቴን ሳበው። አንተን አበንብደ ስመለከት ሐይለማሪያም ደሳለኝ፣ ሽፈራው ሽጉጤ፣ ሚኒስትር አለማየሁ ተሾኑ፣ አረጋዊ ደግፌ በሳ እና አበዱላ ንመዳን ተመለከትኩ። ...ለካስ ሀንጻውን ያገቱጠቀጠው ከርርደ በጀግ ቅሴ ሲያሰማ የነበረው አባዱላ ንመዳ ሆኗል።

በልቤ "አባዱላ ታድሰሀ" አልኩኝ።

ለለሊስ አበባ ኢህአዴግ ከድራዎች ወደተሰጠን ማደሪያ ስደርስ ከሁሰት ከፍት ከሆኑ አልጋዎች ውጪ ሌላው ለጥ ብሎ ተኝቷል። ከፍት የገበረው አልጋ አንዱ የለኔ ሲሆን የተተረው ተጋላሊት ፍሬህይወት አያሌው ከሴቶች ባለስልጣናት ጋር ሙተኛ ደብርኛል በማስት እኛ ከፍል መጥታ እንድትተኛ ያሊያዘችው ትርፍ አልጋ ነበር። ሁኔታው ይበልጥ ስለከነከነኝ አራተኛ ሮት ላይ መኝታ ወደተሠጠው የሲኒኮሬ ጌታቸው ከፍል ሔድኩኝ። እንደ ፍሬህይወት ሁሉ ሲኒኮሬም የተመደበበት አልጋ ላይ የለም። በጭሬራ ቢቱ የተመለከትካቸው ሞንጂሮና እና ፍለህ መለሰ በለይነ ልቦናዬ መጥተው ተደቀንብኝ። "በአደባባይ ያልተነገረውና ያልተጻፈው ሴላኛው የበልጠና አለማ የፍትር ግረባ ነው" አያለ የሚናገረው አልቢትር ተስፋዬ አሚጋ ትከከል ሳይሆን አይቀርም።

ወደ አልጋዬ ተመልሺ በመምጣት ለመተኛት ብሞክርም እንቅልፍ እንቢ አለኝ። የረረደበትን ማስታወሻ አውጥቼ መከተብ ጀመርኩ። መጀመሪያ የተገለጠልኝ ኪታንይ አተይ ጋር ስናወራ ሞንጅሪኖን "እርሰም ይሞከሩት" በማለት የተናገረው ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ የህወሓት ታጋዮች ሰም ለመስጠት እና ለመሰጠፍ የሚችላቸው የለም። ብድግ አያደረጉ እንዳለ ጭታ ሲመርጉ ሠው ምን ይሰኛል የሚል ይሉኝታም የላቸውም። ከሁሉም የሚገርመው እርስ በራስ በሚለዳደፉት ስያሜ አለመብሸቃቸው ነው። ኩባረ-ነክ እና መረን የለቀቀ አንኳን ቢሆን ከመናገር ወደ ኋላ አይሉም። በተፈጥሮ እና ሠው ሠራሽ አደጋ እክል የደረሰበትን ጓደኛቸውን ሳይቀር ጉሳት ላይ የተመሰረተ ስያሜ ይሰጡታል። ከዚህ አንጻር ትቤት አስተማሪ በነበርኩ ሠአት ይጋውሚን አሰረባውም።

በዘመድ ህጻናት እምባ እንዲህ ክር የሆነው፡

ተደጋግሞ እንደተነሰነው የቀድሞ ታጋሾችን የአሁን የመከላከያ ጀነራሎችና ሲ
መኮንኖችን የለገደና ደረጃ ትምህርት ለማስተማር ገዛይ ህጻናት ሐጂ ክር። በዋቂት ቀ
እንደተመለከትነው ከመታደራዊ መኮንኖች ውስጥ በተለይ የህወሓት ሠራዊት አባላት ከሌ
ውስጥ ቁጥራቸው ቀላል ቦማይባሉት የአከል ጉዳት አጋጥሞቸዋል። የሚያነክሰ፣ እግርና እጅ
የተቆረጠ፣ እንድ አይናቸው የጠፋ፣ ሁለቱ አይናቸው ወደ መታወር ሚፍ የደረሱ በርካታ ናቸ
እነሱ በቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት ውስጥ ያሉ ባላንጣ ወንድሞቻቸውን ተከሥው የአከል ጉ
አንዳደረሱ ሁሉ፣ ራሳቸውም ላይ በርካታ የአከል ጉዳት አጋተሟቸዋል። ሰፍር ቁጥር የለሳ
የህወሓት ታጋሾች ወይ እጻቸው አሊያም እግራቸው ወላልዷል። የፊታቸው ጥላሸት መምሠ
መረነክስት የቀድሞ ጽልመታዊ ህይወታቸውን ያሳብቃል።

በዘዋይ ህጻናት እምባ የማስተማር ስራዬን የጀመርኩ የመጀመሪያው ቀን የከፍል ው
በሆንኩበት "ኔኖ " ከፍል አቴንዳንስ መያዝ እንዳለብኝ ይነገረኛል። እኔም ቡተስጠኝ መሠ
መሠረት "የተገኘ" እና "ያልተገኘ" ለማውቅ ሰም መጥራት ጀመርኩ። በዛውም እንደተዋወቃ
አየተነሱ ቆመው እገዚታዩ ነገርኳቸው። የተወሰኑ ተማሪ ሰም ከጠራሁ በኋላ "ኮ
አው_" በማለት ቀጣዩን ባልጨርሰው ተደናግጬ ዝም አልኩኝ።

መኮንኖቹ ሲታቸውን ለቀቁት።

ግራ መጋባቴን የተገነዘበው የከፍሉ አለቃ ጀነራል ገ/እግዚአብሔር አረጋሺ (የመከ
የዘመቻ መምሪያ ሀላፊ) አየሰቱብኝ እጁን አወጣ። የከፍሉ አለቃ የሚኖርበት መኖሪያ ክ
አጠገብ በመሆኑ አስቀድሚ ተዋውቁዋለሁ። ስሙ ገ/እግዚአብሔር ቢሆንም ሠራዊቱ የሚያውቀ
በበረሀ ("የፊረስ ስሙ") በሆነው "አረንሺ" ነው። እኛም ሲተዋወቀን "አረንሺ አባላለሁ" በማ
ነበር። አረንሺ ሳቁን አቁሞ ኮስተር በማለት አጨበጨበ።

ጀነራል አረንሺ ጉሮሮርውን ሰሱ፣

"መምህርነ_ አዚህ ከፍል ውስጥ አራት ፍሰሀዎች ከእነ አባታችው ተመላላይ የሆኑ አ
አንደኛው ፊትለፊት የምታየው "ፍሰሀ ቆሚጥ" ይባላል።_ "ፍሰሀ ቆሚጥ" እጅህን አወጥ
አሳየው!" በማለት ትዕዛዝ ሠጠ።

ግራ አድ የሌለው ሻለቃ እጁን አወጣ።

"መምህርነ_ ሁለተኛው መኮንን "ፍሰሀ አውሩ" ይባላል። በደንብ ማየት ስለማይችል ነው
እውሩ የተባለው። አቡን ፊትለፊትህ የተቀመጠው ነው።_ "እውሩ" እጅህን አውጥተህ አሳየው!"
በማለት ጀነራል አራንሺ ተናገረ።

እውሩ የተባለው ኮረኔል እጁን አወጣ።

"መምህርነ_ ሦስተኛው "ፍሰሀ ወርቅ አይኑ" ይባላል። ተማሪዎች "በወርቃይኑ"
ስለሚያውቁት አጉተንም እንደዛ ብለህ ጥራው። "ወርቃይኑ" ተነስና ቁም! በማለት ለሶስተኛ ጊዜ
ትእዛዝ ሰጠ።

ከተግ በኩል አንድ ሙሉ ኮረኔል እጁን አወጣ። የመኮንኑ ግማሽ ፊት ሙሉ ለሙሉ
ተቃጥሏል። በአይኑ አካባቢ ያለው የግንባሩ ስጋ ተቦርድቷል። ቀረብ ብዬ ሳየው አንድ አይኑ
ጠፍቷል። በምትኩ ከርቶት የምታበለጨልጭ አርቲፊሻል አይን ተተክሎለታል። ሠውየው
በቅርበት ሲመለከቱት በጣም ያስደነግጣል። የጥላቻ ስሜት ከፊቱ ላይ ይነበባል። የሠላምና
የመንፈስ ሪፍት አይታይበትም። ግንባሩን ሹብሸበ ተመለከተኝ። ከልቤ ፊራሁት። ሳላውቀው
ጠላሁት። ለነገሩ ካወቅኩት በኋላም አስቀድሚ መጥላቱ ትከክል እንደሆነ አረጋግጫለሁ።

ጀነራል አረንሺ ወደ ኋላ ዞር እየተመለከተ፣

"መምህርነ_ አራተኛው መኮንን "ፍሰሀ ቢቢሲ"ይባላል። ቢቢሲ የተባለበት ምክንያት ወሬ
በማናገኘ የሚችለው ስለሌለ ነው።_ "ቢቢሲ" የዚህ ግሥልጠኛ ተቋም አሸዥ ስለሆነ በስራ
መጽንታችሁ አይቀርም። በየሩብ አመቱ ግምገማ እያደረገ ውበግብ የሚሞላልህ እሱ ነው።_
"ቢቢሲ" "እንድ ጊዜ ቁም!" በማለት ተናገረ።

ቢሮ ሄጀ የቅጥር ደብዳቤዬን የሠጠሁት እሜር ሠውዬ ቆሞ ታየኝ። ቢቢሲን በቢሮው
ሳገኘው የደረደረልኝ በርካታ ጥያቄዎች በአይነ ህሊናዬ መጡብኝ። ግና በቅጡ ሳይተዋወቀኝ
"ብሔርህ ምንድነው?!_ የአባት እና እናትህ የተወለዱት የት ነው?!_ የኢትዮጵያ ህዝብ የትግራይ
የበላይነት እንዳለ ለምን ይናገራል?!_ አንተ የትግራይ የበላይነት አለ ብለህ ታምናለህ ወይ?!_

አሞኛ አለችህ፣ ወሲብ ፈጽማችሁ ታውቃላችሁ ወይ?_ በስንት ጊዜ "ወዘተ" የሚሉ ጥያቄዎችን ጠይቆኝ ነበር። እሁን የፈረሰ ስሙ "ቢቢሲ" መሆኑን ሰሙማ ሰምቼው ከባድ እንዳልሆነ ተረድቻለሁ።

የጊታው ሆኖ መጀምሪያ ሠሞኑን ተማሪዎች በሚጠሯቸው ስያሜ መጥራት ሀሊናዬን አልተቀበለውም ነበር። ርግጥም አጅ የተቆረጠ ፍጡር "ቆማጣ"_ ማየት የተሳነውን "አውሩ"_ አይኑ ተነስትሶ በአርቴፊሻል የተተከውን "ወርቅ አይኑ"_ የወፌ ትተራውን "ቢቢሲ" እያሉ መጥራት በተሳሳ የሚለመድ አይደለም። በተለይም በማህበረሠቦችን ስነ-ልቦናና መስተጋብር ተከትኩተን ሳደግን ሰዎቹ እንደወረደ መቀበል በጣም አስቻጋሪ ነበር።

ታሪክ ራሱን ደጀግማል እንዲሉ ከተቂት ወራት በኋላ ከ10 ሺህ በላይ ሴት ተጋዳሊቶችን ጦላይ ማሠልጠኛ ማቢያ ለማስተማር ስሔድ ተመሳሰይ ሁኔታ አጋጥሞኛል። በአብዛኛው ትከሻቸው የሰበጡት ተጋዳሊቶች እንደ ወንዶቹ ሁሉ የጎደላቸው ነገር አይጠፉም። በዛ ላይ ውርደትና የሞራል ድቀት የተሸከሙ በመሆናቸው በትንሹ ስሜት የሚደዙ ናቸው።_ ምንም እንኳን በአብሰ ወከፍ ከላሽንኮቭ፣ ማካሮቭ ሽጉጥ በታናቸው ቢኖርም መንፈሳዊ ሞታቸውን ተገንዘተዋል። በዚህም ምክንያት ቦግሰልጠኛ ተጂሙ የሚገኙ መምህራን በቅርብ እንደታዘብኩት ከሠሞ "ዲሞብላይዝድ" ከግሰት ይልቅ "ዲሞራላይዝድ" እያሉ ይጠሯቸዋል። "ዲሞራላይዝድ" ተጋዳሊቶች የመታሰል ስሜት የሚሠማቸውና ተሰፉ የቆረጡ ናቸው። በየቀኑ መሳሪያ የሚወለውሱ እና ጎራዴ የሚሰሉ ሆነዋል።

ታዲያ ሁኔታው በዚህ ደረጃ እያለ የሠውነት አካላቸውን መሠረት ባደረገ መልኩ መጥራት ከሞራል አንጻር መቀበል ያሥቸግራል። የአይን አይታዋ የተዛነፈውን ተጋዳሊት "አባዲት ሽውራሪት"፣ _በለምዕ የተመታችውን አባዲት ለምሣሊት"፣ _በጥይት እግሯ ተበሳስቶ በዱላ የምትሄደውን ደግሞ አባዲት እንካሲት" እያሉ ለይቶ መጥራት በጣም ይከብዳል። ጦላይ በቅርብ አንዳየሁት ለጋዲ ተጋዳሊት ከሴላ ተጋዳሊት ጋር አብረው ይተኛሉ። አንደኛዋ ባል፣ ሌላኛዋ ሚስት ናት። እናም እነዚህ የሰምንተኛው ሺህ ሙቅረብና የምዕዐት መድረስ ተምሳሌቶች መጠሪያቸው ተሰይቶ በወንድና በሴት መሆኑ ያስደነግጣል።

ያም ሆነ ይህ መሸቶ በነጋ ቅዮር ውስና አዳራችን ከተማሪዎቻችን ጋር በመሆኑ የሰለ ደረጃችን ወደ እነርሱ ወረደ። አካባቢው በፈጠረው ተጽእኖ እጃችን ተጠምዝዞ እነሱን ሆነን ባላሰብነው ጊዜና ውት ያሳሰብነውን ሆነን ተገኘን። አሰቀድመው ማኅበራዊና ተጋዳሊቶች የተቀላቀሉት መምህራን "ፍሰሀ ቆሚጥ"፣ "አባዲት ሽውራሪት" ሲሉ ተኖራችን ውስጥ ለመደ የምንርጠው ቀርቶ መደበኛ ስያሜ መሠለን። ነገር መምህራን ከተማሪዎቻቸው እንደመ ተቀብለው የሚያስተጋቡትን እኛም ተስማምተን በስራ ላይ እየዉልን። አሊስ ማንነት የሚ የቡድን ስነ-ምግባር ቡተግበር ተጋሊጠ። አንዳንዶቻችን ቀድሞ የነበሩትን በመተቢስና በላቀ ደ በማሻሻል እንካሲትዬ"፣ "ሽውራሪትዬ" በማለት በቁልምጫ መጥራት ጀመርን። "የሁኔታዎች ምርጫ ሳይሰጠን በእኛ ላይ ነገሠ። ያለምንም ችግር ዝዋይ እና ጦላይ የሚገኙ ታ ተጋዳሊቶች በእዲሱ ባህሪያችን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አሳረፉ።

ሴላው ቀርቶ በሳምንቱ የአረፍት ቀናት በመዝናኛ ቦታ ከተኛናንን እንደ ማዕረግ እያደጋምን እንጠራለን። በተለይ በሞቅታ ወቅት "ቺርስ አውሩ" ፣ "ቺርስ ወርቅ አይኑ"፣ ወዲ ባሪያ" ፣ "ቺርስ ወዲ ለማኝ" እየተባባልን የቢራ ጠርሙስ እናጋጫለን። እነ ቆሚጥ፣ ቢቢሲ ደስ ይላቸዋል። ቢራ በደርዘን በደርዘን እያመጡ ፊታችን ይደረድሩሉ። በተሐድሶ ከተጋዳሊቶች ጋር የሚኖረን ግንኙነት ተመሳሰይ ነበር። በእናት ሐገር ውሰጥ ዘጦች ተገልፃ ጋብኝና ወደ እልጋ ጎትቶ ወሳጅ ተጋዳሊቶች ናቸው። ከእኛ የሚጠበቀው አንድ ነገር ብቻ በረጠቡ የፍቅር ቃላት ማቆላመጥ_ አባዲትዬ እወድሻለሁ!_ ለምጻሚትዬ ጀግና እዩ_ ሽውራሪትዬ አፈቅርሻለሁ!_

ወግን ወግ ያሳሳዋልና የባህሪ ለውጥን ካነሳሁ አይቀር አንድ ከሀሊናዬ የማይፈለ ዘወትር ይታወሰኛል። ወቅቱ በመከላከያ ሚኒስቴር የትምህርት እና ስልጠና ከፍል በምሰራበት ጊዜ ነበር። የመከላከያ ትምህርት እና ስልጠና አዳሪና ተንቀሳቃሽ ትምህር ለመከፈት ሲያስብ የተለያየ አላማዎችን ለማሳካት በማሰብ ነበር። ከእነዚህ አላማዎ ግንባር ቀደሙ ከታጋይነት ተንደርድረው ወደ መከላከያ መኮንንነት እና የሙ የተቀየሩትን የህወሓት ታጋዮች ወደ ሀገሬው የደረሰበት ዘመናዊነት ደረጃ ላይ ማድረስ ነ

ለሁሉም እንደተገለጠው ታጋዮቹ ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ወደ ኋላ የቀሩ እጅግ የበዛው ህዝብ እነሱን ከመናቁም በላይ ያላግጥባቸው ነበር። የኢትዮጵያ አየር

ሂዩ በሚለላዲ "አስቂኝ ለውጦች" የተሞሳ ነበር። ከዚሁት "መሰከረም ኢንቨስትመንት" የሚባል ኩባንያ ለማቋቋም ተማሽ ሚሊዮን ብር አዋጥቷል ብሉ የመዘገበው "ጀነራል ሳዕር" ኮካ እና ፋንታ ለስላሳን የሚለሰው "ተቁር እና ቀዩ" በማሰት ነበር።.. በአሁን በዓት ከሰራው ቤት ኪራይ በወር ኔዕሺህ ብር የሚያገኘው ጀነራል ናሰው ኪዳነግሪያም (መንጂስ) "የታገሰኩት ሰደሞ! አይደለም" በማለት የወር ደሞዝ አልቀበልም በማለት አስቾኮር ነበር።.. ፍሰሀ መንጅስ መጀመሪያ ሠሞን "ለኪስ ገንዘብ ተብሳ በወር ከተሰጠው ፯ዐብር ውስጥ ጋዐብር ወጪ በማድረጉ በአባካኝነት ሂስ አውርዶ ነበር።.. "አበሳኝ ሆንሁ! በቀን ውስጥ ሁለት ጊዜ ተቁድን ስትጠጣ አይተንህል" የሚል ዓለ-ሂስም ቀርበበት ነበር።.. በአንድ ጊዜ አራት መታንታ በመግዛቷ የተፀፀተችው የጠላይ ማሠሪያው ባቢያ ቀና አሳሹ ተጋላሊት ኮረጌል በውዱ "ቀንላችኑትና የመኖር አርአያ ተምሳሌት መሆን" የሚል ሂስና ግስሂስ ተሰሂዶቢታል። ሁለት መታንታ አስቀርታ ሲላውን "በጓዳዊት" መርህ ለሌሎች ተጋላሊቶች እንድታከፋፍል ተደርጓል።

በመሆኑም እነዚህን የህወሓት ታጋይ የነበሩ የወራዊት አባላት ወደ ዘመናዊ ኑር እንዲሰጉዱ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኘ። ለዚህ ግብ መሳካት እንዲረዳ የተመረጡት መምህራን በሙሉ "ከተማ ቀመኛ" እንዲሆኑ ተደረገ። ከመምህርነት የመቅጠሪያ መስፈርቶች መካከልም "የአዲስ አበባ፣ የአዋሳ፣ የባህርዳር፣ የመቐሌ፣ የናዝሬት.. ወዘተ" ልጅ መሆን ተጨማሪ ነጥብ የሚያስተ ሆነ። መምህራኑ ተመልምለው ከተቀጠሩ በኋላ ከተሰጣቸው ስልጠና ከራሱ ታጋዮችን እንዴት "ማዘመን" እንደሚችሉ የሚያመላክት ነበር።

ስልጠናው ተጠናቆ መምህራን በሁሉም ከፍለ ጦሮችና አዳሪ ትምህርት ቤቶች ተመደቡ። የማስተማርና ታጋዮችን ሰልጡን የሚድረግ እደራ የተሸከሙት መምህራን በቁርጠኝነት ስራ ጀመሩ። ከከፍል ውጪ ነጭ ጋዋናቸውን ሲያወልቁ ሰፋቸውን ግጥም አድርገው በተማሪ መሀል መንሪደድ ጀመሩ። በረፍት ሠአት ቢራና እልኮል በቁንጥ እየጠጡ አሳየአቸው። ከኮካ እና ፋንታ በተጨማሪ "ስፐራይት"፣ "ፋንታ ቶኒክ"፣ "ሽዌፕስ" የመሳሠሉትን ለስላሳ መጠጦች በስም አስተማሩ። ታጋይ መኮንንኖቹ "ቀኖ"፣ "ጥቁሩ"፣ "የሚታነሳው"፣ "የሚጣፍጠው" የሚለውን አንሳለፅ በመተው ለስላሳ መጠጡን በስም መጥራት ጀመሩ። ኮካ እና ፔፕሲን፣ ሚሪንዳና ፋንታን ለይተው ማዘዝ ቻሉ። "አጭርና ረጅሙ" ማለት ትተው "ሚታ" እና "ቦደሌ ቢራ" ብለው መጥራት ቻሉ። ሊያደቆ ማጣጣም ጀመሩ። የስልጣኔ እና እውቀት ግብይቱ ተጠናክሮ በመቅጠል ተማሪዎች ገንዘብ ባንክ እንዴት ማስቀመጥ እንዳለባቸው፣ ከደምፅ ወያኔ ሬዲዮ በተጨማሪ ሌሎች

ሚዲያዎችን መስማት እና ማመን እንዳለባቸው አስተማሩ። ጋያደር ታጋይ መጎንጎፎ ዘመን መቆጀት ጀመሩ።

ትምህርት እና ስልጠናው ከተጀመረ ከሰኔት አመት በኋላ በየከፍለጦሩ የመጣውን የባህሬ ለውጥ ለመገምገም የመስከ ጉብኝት እንድናደርግ ለእዲሶቹ መምህራን መመሪያ ተሳለፈ። መምህራን በተማሪዎች ላይ ያመጡትን የባህሬ ለውጥ የምንመለከትበት መመዘኛዎች በርጋም ተሠርቶ ተሠጠን። እኔም ከአዋሳ መስመር እስከ ሱዳን ጠረፍ ወደተዘረጋው ኮር ሁለት ያቀፍኩት ከፍለጦሮች ከቡድኔ ጋር ተንቀሳቀስኩ። ወደ አከባ።

የሚገርም ነበር!

_ታሳት የሚገልፀው አይደለም።

ከእኔ ጋር ለተናት የተንቀሳቀሰው ቡድን ቅድሚያ ያደረግነው በተገኘንበት ከፍለጦር መምህራንን መሠብሠብ ነበር። በሁሉም ከፍለጦር ተመድበው የሚሰሩ መምህራን ሙሉ በሙሉ ተቀይረዋል። ፀጉራቸው ከመጠን በላይ እድጎ ተንጨፍርሯል። ኮንጎ ሚጣ ተሚምተዋል። እግራቸው ከመሠጎጣጠቁ ባሻገር ለወሪት ወሀ አንዳልነካው ያስታውቃል። የእንገት እና የኪሌታቸው አጻፋ ተቁር መስመር ሠርቶ ይታያል። ብዙዎቹ መምህራን በወገባቸው ሽጉጥ የታጠቁ ሲሆን ሁሉም በጎበስ መነፍ ከላሽንኩቲ በጀርባቸው አንግተዋል። አጠቃላይ ቁመናቸው የህይወት ድባባቸው ታተር ቁልቁል ወደ አስመናር እየሔዱ መሆኑን ያሳብቃል። ይህም ሆኖ በሙሉ ልባቸው ተቀብለውት ከወጂያ ወጂህ ይንጎግለላሉ። የሠጠሙበትን ድንዛዜ ሊያስቡት አይፈልጉም። ርግጥ አንዳንዶቹ የእኛን ቁመና ቢመለከቱ የመናደድና መቆጨት ስሜት ይሠማቸዋል።

የውጭ ገፅታ መመልከት እቁመን ግምገማ ስንጀምር መምህራን "እስኔድ"_ "ስኒ-ስርአት"፣ _"ኢንፎርሜሽን" በሚሉ ድርጅታዊ ቃላት አጣደፉን። እርስ በራስ በሚጋጩና በሚገፈታተሩ ሀሳቦች እናታችንን በጠበጡ። የብዙዎቹ የእኒጋር ዘይቤ ወደ ትግርኛ ተተይር ከእንደቢታቸው ሲወጣ በኩራት ሰግዩን እየቀዘፈ የሚበር ንስር ይመስል ነበር። በመጀናንተ ሰምናዳምጠው የቡድኑ አባላት የሕሊና መሸግቱት ፈጠረብን። ኽና ኮሌጅ በተሰን ጀግፊ መምህር እንደመሆናችን መጠን የነገ እጣ ፈንታችን ተመሳሳይ እንዳይሆን በፍርሀት ተቁተን። ሠብዓዊ ፍጡር እንደመሆናችን መጠን አካባቢያዊ ተጽእኖ አሸንፎን "አዲስ ማንነት" የማንፈጥርበት

አንዳችም ምክንያት አይኖርም። ማንነት ከሚቀርፅባቸው ቦታዎች አንዱ በአካባቢያችን ያለ ማህበረሰብ እንደመሆኑ መጠን አለመለወጣችንን በልበ ሙሉነት መናገር አይቻልም። የማንነት መልክት በደምና አጥንት ብቻ የተቋረጠ አይደለም። እንዲያውም ከደም ሀረግ ይልቅ በአካባቢያችን ያለው ማህበረሥብ የሚያሳድረው ተጽእኖ ለማንነታችን የበረታ ትርጉም አለው። የተወለድንበት፣ ያደግንበትና የየልንበት አካባቢ በባህሪያችን ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ትልቅ ነው።

ከሁሉም የሚገርም ነገር የተመለከትነው በሁሉም ከፍለጦሮች "ተሐድሶ" የሚባል የመዝናኛ ፕሮግራም በተዘጋጀ ሠአት ነበር። "ተሐድሶ" መጠጥ እየጠጡ የመጨፈር ስርአት ሲሆን ተግሪና መምህራን ቢጋራ የሚሳተፉበት ነው። እናም የነረመን ነገር ቢኖር የሚቀርቡት ሙዚቃዎች በብዛት የህወሓት የበረሀ ዘፈኖች ሲሆኑ ዘፈኑ ሲጀምር እየሮሁ ወደ መድረክ ቀድመው የሚወጡት መምህራን ናቸው። የመምህራን አጨፋፈርም እንደ ታጋዮች ከላሽ ወደ ላይ በማድረግ "እንድ እግር በመሬት" ከፍ ዝቅ በማለት ነበር።_ እምበር ተጋዳላይ_ ብሶት የወለደው የከተማ ሠራዊት!_ የሙዚቃው ንጉስ የለ_ የትግስታው ንጉስ የለ!_ "ፍቅር ይሻለኛል የለ!_ አስከ ንጋት ድረስ "እምበር ተጋዳላይ!!_ "ኮረኔል ማራኪ"_

98

በአጠቃላይ መልኩ የባህሪ ለውጡ በተቀመጠለት አላማ ሳይሆን ከታጋይ ሠራዊት ወደ "ኩተማ ቀመስ" መምህራን የፈሠሠ ነበር።

ምንም እንኳን ከአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ አዳማ፣ አዋሳ፣ ባህርዳር፣ መቀሌ፣ ጅማ...ወዘተ ለመምህርነት የተመለመሉት የተቃጠሉ የከተማ ወጣቶች የባህሪ ለውጥ አምጥተው የቀድሞ ታጋዮችን ቢመስሉም፣ ተግሪዎቻቸው አዲስ የባህሪ ለውጥ ማምጣት ችለዋል። የታገልነው ለዲሞክራሲ አና ነፃነት በመሆኑ ቁምጣ እና ኮንን ሚማችንን ቀይረን ወታደራዊ ዩኒፎርም እንለብሰም ብለው ያስቸገሩት ታጋዮች ተገልብጠው በወታደራዊ ማዕረግ አሠጣጥ ላይ ቁም ሲያያዙና ሲገዳደሉ ማየት ተቻለ። ከህወሓት የጋራ ዝንጠላ ወርደው አድዋ፣ አክሰም፣ መቀሌ_ ወዘተ በሚል መንደርተኝነት እየተባደኑ ተጠቃቀሙ። አስቀድመው የነቱት የተሠጣቸውን ማዕረግ ወደ ሊከኖሚያዊ ጥቅም ገለበጡት።

በዚህም ምክንያት በወታደርዊ የአመራር ስልጠና ታሪክ ያለምንም የአመራር ስልጠና የጀነራል መኮንንት ማዕረግ የሠጠች የመጀመሪያ የአፍሪካዊት አገር ኢትዮጵያ እንድትሆን በማድረግ "የአፍሪካ ንብርቦ" ሆንዋል። የትምህርት ዝግጅታቸው ከዓ/ኛ ከፍል በታች የሆኑ ወደ 130 የሚጠጉ ሌተናት፣ ሜጀር እና ብርጋዲየር ጀነራል ማዕረግ የተሸከሙ የጦር መሪዎች ተፈጠረዋል። በኢትዮጵያ የቀደምት መንግስታት (የንጉሱና ደርግ) ስርአት ውስጥ አንድም "ሙሉ ጀነራል" በለለበት ሁኔታ በዘመነ መለስ "ፐሮፌሰር ጀነራል" የሚባል የህወሓት የጦር መሪ መፍጠር ተቻለ። "ፐፐሮፌሰር ጀነራል" ማዕረግ የተሠጣቸው የህወሓት ታጋይ ሐውልታቸው ተቅርጾ በቬሐራዊ ሙዚየም በማስቀመጥ ሌላ አዲስ ታሪክ ተሰራ።

አዲሱ ታሪክ በዚህ ብቻ አላቆመም። በትግል ተፈትነው ያለፉት የህወሓት ተጋዳሊቶች "ሴት እህቶቻችን አንዳይንዳ፣ ይልቁንም መብቱና ጥቅሙ ተከብሮላቸው እንዲኖሩ" የህወሓት ተጋዳሊት ጀነራል መፍጠር ተችሏል። ባል ሜጀር ጀነራል_ ሚስት ሌተናት ጀነራል_ አዲስስቲ ኢትዮጵያ! ህወሓት የቀረው የክፍተኛ የጦር ማዕረግ "ፊልድ ማርሻል" ብቻ እንዲሆን አድርጓል። አቶ በረከት ስምኦን በመጽሐፉ ላይ "የኢህአዴግ አመራር ባህርይ ሁሉም ለመግር ዝግጁ መሆኑ ነው" ቢልንም በተታራኒ "ትምህርት-ጠል"፣_ "እውቀት-ጠል"፣_ "ህገ-ጠልና ወደ ኋላ የወደቀ" ታጋዮች የጄነራል ማዕራግ እንዲሸከሙ ተደረገ። እደደለም ከለለም ህዝብ ከኢትዮጵያ በውስኗ ካመቸው የታሪክ ጓዳ መሚር ፍላጎት የሌላቸው የህወሓት ጀነራሎች የኢትዮጵያ ወታደራዊ ሰልጠና ገጽታን ከግበላሽታቸው በላይ መተፎ የታሪክ ጠባሳ ጣሉ። እነሱም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያም ወደ ኋላ ወደቀች። እባሯን አራግፋ መነሳት እቅታት።

***

የህወሓት የጦር መኮንኖችን ሰናሰተምርበት የነበረው ዝሞይ ህጻናት እምባ በየሰበቡ ውሱ ለእንድ ሳምንት ያህል ለእረፍት ይዘጋል። አብዛኞቹ የጦር መኮንኖች ወደ ሻሸመኔ እና አዋሳ በማሩፐ ሆነው ይሄዳሉ። እንደ ትልቅ መዝናናት እና እረፍት የሚቆጥሩት አካባቢ መጎብኘት አሊያም ሀገር ማወቅ ሳይሆን ከቡና ቤት ሴት እህቶቻችን ጋር መተኛት ነው። ከእረፍት ወደ ትምህርት ቤት ሲመለሱ ለተራዘመ ቀናት ጨዋታና ብሽሽቃቸው ባወጧቸው ሴተኛ አዳሪዎች ብዛትና ውበት ላይ የተመሰረተ ይሆናል። እንደኛው የተኛትን ሌላኛውም አነፍንፎ በለሚተኛት ሴቶቹን የሚያውቋቸው በሆቴል ቤቱ ስም፣ በመልክ፣ በአድሚያቸውና በሰውነታቸው ቅርጽ ነበር።

ከሷቶቹ ጋር የነበራቸውን የመቀራረብ ደረጃ ሊያወሩ እንኳን ጭላ ያለችው፣ ትንሿ መቀመ
ትልቋ ነበር።

እናም ከእሁታት በፊንቱ የእረፍት ጊዜ ከሀገር መኮንኖቹ ጋር ለማሳለፍና ገድላቸ
በማህታመ ለመስተብ አበራያቸው ሽሽመጌ ሄደኩኝ። ወደ ሻሽመጌ ይዘውኝ የሄዱት በ
ማረግ የነበራቸው የጠበቀትና ብልጫን ታጋዮች የነበሩ ናቸው። አንድ የአጎ ቢጤ መምህን
አብርሃ ክፍሬ ሻሽመጌ ስንደርስ ከተማዋ በተማሪዎቻቸን ተጨናንቃ ልትፈነዳ ደርሳለች። ሆ
ቤቶቹ በመሉ ለእንድ ሳምንት ተይመዋል። በየሆቴል ቤቱ ያለው ሽርጉድና መስተንግዶ የወታደ
ወደ ከተማው መግቢያችውን የሚያሳታወቅ ነበር።

ሽሽመጌ በስተምን ሰሉተኛ ቀን አመሻሽ ላይ ከመምህር ጓደኛዬ ጋር ሆነን ወደ አንደኛ
የምስት ቤተ ጉራ ለልን። ኛ ከመቀመጣቸን የቤራ መኦት ጠረጴዛቸንን ሞላው። ከማናወቃ
ቦታ በማስቹ ተጨናንቅን። በሸጠረጴዛው ከቡና ቤት ሴቶቹ ጋር ተተምጠው ማስፕሮ
የሚለከልን ተማሪዎቻቸን ነበሩ። በማያጽርጠው ማብዣ ግራ የተጋቡት ሴተኛ አዳሪ
ባለልማን እድርው ሳይሞቱን አልቀረም። እይናቸውንም ከእኛ ላይ መንቀል አልቻሉም።

ከበሉታት በኋላ እንዲት ሴት አራት ቢራ ይዛ መጣች። እንዳትከፍተው እና ሲ
መውሀድ ከፈለንች እንድትወሰድው ነገርናት። ሊጋባዦቻቸን እንዳትንግራቸው አስጠነቀቅናት
ተማሪዎቻቸን ጋብዘውን እምቢ ማለት የናትናቸው አድርገው ስለሚቆጥሩት ያቁሙብናል። በተለ
ለለንዱ ፍታደኛ ተከሶ ለሊላው እንቢ ካልን ባልጠበቅነው መንገድ ሁሉ ሊመጡብን ይችላ
ስለዚህ እንዲ ከተጀመረ ሁሉንም እቺ ግለት የውዴታ ግዴታ ይሆናል።

ቢራውን የስጠናት እንስት በድጋሚ ስድስት ጠርሙስ ይዛ መጣች። ከአንማን እንደሆ
ሰንጠይቃት በተግ የተቀማጡትን ሶስት ተማሪዎቻቸንን አሳየችን። ሶስት የህወሓት ታጋይ የሆ
ሻለቆች ናቸው። የቡና ቤት ሰራተኛዋ በድጋሚ እንደትወሰደው ስንጋብዛት ግሙን አልቻለችም
ሊላወን ወሰዳ እንዳን ከፍታ አጠገባችን ተቀመጠች

"ደትርታ ባለሰልጣናች ናችሁ" በግለት ወደ አኔ ዞራ ጠየቀችኝ።

"ለምን ባለስልጣናች አልሸን?_ እንመስላለን ?" አልኳት።

የለበጣ ሳቅ እየሳቀች፣

"ከተጎላትኩ ይቅርታ። ሁሉም ሲጋበዝችሁ ሳይ ባለስልጣን መሰላችሁኝ። እኛ ሀገ
እንደዚህ የሚጋበዘው ባለስልጣን እና ትራፊክ ፖሊስ ነው" አለች።

"ባለጊዜም፣ ትራፊክ ፖሊስም አይደለንም። የጋባዦቻችን አስተማሪዎች ነን..የፊ
አስቆጣሪዎች፣" አልኳት።

በድጋሚ ከት ብላ ሲቃ፣

"አስተማሪም ውግ አገኘ እንዴ፣ ታዲያ ምነው እዚህ ከተማ ያሉ አስተማሪ
የሚጋብዛቸው የለም? _ስራችሁ ፊደል ማስቆጠር ከሆነ ለምን እኔንም ሌታስቆጥረኝም። ሁ
ደረሻ ጨርሻለሁ" አለችኝ። እጅቼን እንሰታ መስቀል በመስራት በጥሬ መታቸው።

"እንዴ የጠቀስሻቸው መምህራን ስራ የሌለው ተማሪ ነው የሚያስተምሩት
አለቆቻችንን ነው የምናስተምረው። በስልጣንም፣ በደሞዝም ይበልጡናል እነሱ ቅጣሪዎ
አባራሪዎቻቸን ናቸው" አልኳት። የተናገርኩት ለራሴ ነበር።


ከአይናቿ ላይ እንዳመነችኝ እነበብኩ። ጨዋታችንም በዛው ልክ ወደ እውነት
ሆነ። ከተማሪዎቻቸን የሚመጣውን የቢራ ግብዣ ባትጠይቀን ለራሷ ገቢ ማድረግ ጀ
ወቅታቸን እና የሰጠናት ክብር ይበልጥ እንድታምነን እና የውስጢን እድትናገር አደረጋ
ሰሚ በየለድስት ወር እንደሚለዋወጥ ነገረችን። የዚህ መንፈት ሰሚ ማርታ እንደሆነም
ነገረችኝ።

"እንዴት ደከሞኛል መሰለህ? ያለፉት ሶስት ቀናት በጣም ስራ በዝቶብኝ ነበ
ለሊትም እረፍት አላገኘሁም አለች። እስከትላም "ጄረ፣ ተመስገን ነው። ተማሪዎች
ያግባልን። የቀጣይ ሶስት ወር ቀሰቤንና ቤት ኪራይ አግኝቻለሁ።"

"ማርታ ቀን ምን ታደርጊያለሽ?" አልኳት።

የመሰዳ ፅቃቂት

ኤርምያስ ለገሰ



EFFORT